## <u>ሰንበት ትምህርት</u>

ሰንበት ትምህርት

1/ <<<¤ ክርስቲያን አይሳደብም ¤>>>
=>ክርስቲያን አይሳደብም:: ስድብ የዲያብሎስ ነውና:: (ራዕ. 13:5)
+ጠላትንም እንኳ ቢሆን "እግዚአብሔር ይገሥጽህ" ከማለት በቀር ተጨማሪ ነገር እንድንናገር አልተፈቀደም:: (ይሁ. 1:9)
+አፍን እና ብዕርን አለማረም . . . ይቅርና በክርስትና በሰብአዊ መድረክም ያስተቻል::
+በየገጹ በመናፍቃንና አሕዛብ ላይ ስንሰነዝረው የነበረውን ስድብና ዘለፋ ከሰሞኑ ለክርስቲያን ወገኖቻችን አድርገነው አረፍን::
+ይህንን መመልከት እጅግ አሳፋሪ ቢሆንም ስህተቱ ግን የዛሬ አይደለም:: ትናንት በባዕድ የተለማመድነውን ስድብ እነሆ በቤተሰብ ላይ እየዘራ ነው ይገኛል::
+በእውነት በዚህ ወቅት ከዚህ ፌስ_ቡክ ከሚባል ገጽ መራቅ ሳያስፈልግ አይቀርም::
+ምንም ለውጥ ያላመጣንበት # ቅዱስ_ቃሉ ለከንቱ እየፈሰሰም ይመስላል::
+ስለ መድኃኒታችን # ኢየሱስ_ክርስቶስ : ስለ
# እመ_ብርሃን ንጽሕት # ድንግል_ማርያም እና ስለ
# ብርሃናተ_ዓለም_ቅዱሳን ከገደደን በላይ የለባስያነ ሥጋ ጉዳይ እንዲህ እንደሚያንገበግበንም ግራ ነው::
+እስኪ ከየትኛውም ክርክር በፊት:-
¤ንስሃ እንግባ:: (ማቴ. 3:2)
¤ሥጋ ወደሙን እንቀበል:: (ዮሐ. 6:53)
¤ፍቅርን እንስበክ:: (1 ቆሮ. 13:1)
¤አንደበታችን እንግዛ:: (ያዕ. 3:6)
¤ሌላው ከዚያ ይከተላል::
<< ኧረ እባካችሁ እናስተውል!
ወደ መንፈሳዊ ቀልባችን እንመለስ! >>
<<< አምላከ ቅዱሳን . . . እባክህን ከጭፍን ጐዳና አውጥተህ ወደ አባቶቻችን የቀናው ጐዳና መልሰን??? >>>

Miko ZE Ethiopia

2/ ፍቅር በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ በጥቂቱ፥-

ሚኮ ዘ ኢትዮጵያ

1. ትንቢተ ሆሴዕ 11፥4

በሰው ገመድ በፍቅርም እስራት ሳብኋቸው፤ ለእነርሱም ቀምበርን ከጫንቃቸው ላይ እንደሚያነሣ ሆንሁ፥ ድርቆሽም ጣልሁላቸው።

2. የማቴዎስ ወንጌል 24፥12

ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች።

3. የዮሐንስ ወንጌል

13፥35

እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።

15፥13

ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም።

4. ወደ ሮሜ ሰዎች

1፥31

የማያስተውሉ፥ ውል የሚያፈርሱ፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ምሕረት ያጡ ናቸው፤

5፥5

በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም።

5፥8

ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።

8፥35

ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን?

8፥39

ከፍታም ቢሆን፥ ዝቅታም ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን

ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።

13፥10

ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው።

5. 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

13፥1

በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሽዋሽዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ።

13፥2

ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ።

13፥3

ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፥ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም።

13፥4

ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤

6. ወደ ገላትያ ሰዎች

5፥22

የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው።

7. ወደ ዕብራውያን

6፥10

እግዚአብሔር፥ ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአቸው፥ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና።

10፥24

ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፤

8. የዮሐንስ ራእይ 2፥4

ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና።

ሥራህንና ፍቅርህን እምነትህንም አገልግሎትህንም ትዕግሥትህንም ከፊተኛውም ሥራህ ይልቅ የኋለኛው እንዲበዛ አውቃለሁ።

Melaku Gebremichael Hirphasa
3/ የክርስትና ህይወት ለሳምንት ወይም ለወር ብቻ ቢሆን
ኖሮ ብዙዎቻችን ከንፍ እናወጣ ነበር። ልባችን በወንጌል
የተሰበረ በመሰለን ሳምንት ሁላችንም ለእግዚአብሔር
የማንሆነዉ የለም ስንል እንደመጣለን እኛ ብቻ ለእግዚአብሔር
ስምና ክብር ጠበቃ የሆን ያክል ይሰማናል አንዳንዴም ለእግዚአብሔር ለራሱ ከእርሱ በላይ ስንጠነቀቅለት እንታያለን። ነገር ግን ጊዜዉ ሲረዝምና ክርስትናም እስከ ህይወት ሕቅታ ድረስ የምትዘልቅ መሆኗን ስናውቅ እንዘናጋለን፣ ይሰለቸናል፣ ይደክመናል፣ እናሳርፈዋለን፣ ይከብደናል፣ እንጥለዋለን። የሰው ልጅ ከክርስትና ሲወጣ ቀስ በቀስ እነዚህ ባህሪያት ይታዩበታል...
☞ ሞትና ህይወትን ማስታወስ የእግዚአብሔርን ስም መጥራት
ይተዋል
☞ መሳለም ማስቀደስ ያቋርጣል መፆምና መፀለይ ይተዋል
☞ንስሃ አባቱን ወይም መንፈሳዊ ወንድሞቹን ሲያይ ይሸሻል
ይደበቃል
☞ መዋያዉን ይቀይራል የሰዉን መንፈሳዊ ህይወት መንቀፍ
ይጀምራል
☞ ቀስ በቀስም ኃጢአትን ይለማመድና እየፈፀመው ጻድቅ
መምሰል ይፈልጋል።
☞ ሲገፋም ግልፅ ያወጣዋል ከዚያም ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን
ያፋልሳል ቅዱሳንን ያንቋሽሻል ይክዳል።
✿
<< አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸዉን ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን መልካሙንም የእግዚአብሔር ቃልና ሊመጣ ያለዉን የዓለም ኃይል የቀመሱትን በኋላም የከዱትን እንደ ገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነዉ. ✿ ዕብ 6÷4-6
መ.ር ሰሎሞን ፋንቱ: 2. የክርስትና ህይወት መሰረቷ ማን ነዉ?

4/ የክርስትና ህይወት መሰረቷ ማን ነዉ?
ሥር ለመስደድ የተለያዩ ፀሃፍት በተለያየ መንገድ መግለፅ ቢችሉም በዚህ ፅሁፍ ግን ከዚህ እንደሚከተለዉ እንመለከታለን።
2. የክርስትና ህይወት መሰረቷ ማን ነዉ?
ምዕመናን በክርስትና ህይወት ስር መስደድ አለባቸዉ ሲባል ስለ ክርስትና ህይወት ምንነት ከመረዳታቸዉ በፊት ስለ ክርስትና መስራች ወይም መሰረት እና እንዴት እንደተመሰረተች ማወቅ ቀዳሚ ነዉ።
የቤተክርስቲያን መስራ„ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን የክርስትና ህይወት ፅኑ መሰረ~ም እርሱ ነዉ።
ኢየሱስ ወደ ፊልጶስ ቂሳርያ በደረሰ ጊዜ ደቀመዛሙርቱን ሰዎች የሰዉን ልጅ ማን እንደሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቃቸዉ። እነሱም በዚያን ጊዜ ሰዎች ክርስቶስን ማን እንደሆነ እንደሚሉት ነገሩት ኤልያስ ነህ፣ ኤርሚያስ ነህ ወይም ከሙታን አንዱ እንደሆንክ ይሉሃል አሉት። በሩቅ ያሉ ኑሮአቸዉን ትተዉ መረባቸዉን ዘርግተዉ ያልተከተሉኝ
እንዲህ አሉ እናንተ የተከተላችሁኝ እኔ ማን እንደሆንኩ ትላላችሁ፤ ማነዉ ብላችሁ ተከተላችሁኝ አላቸዉ። በዚህ ጊዜ ከደቀመዛሙርቱ ፈጥኖ ጴጥሮስ # አንተ
ዉእቱ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያዉ$ አንተ
ክርስቶስ የህያዉ እግዚአብሔር ልጅ ነህ ባለዉ ጊዜ
ክርስቶስም መልሶ እንዲህ አለዉ # የዮና ልጅ ስምዖን
ሆይ በሰማያት ያለ አባቴ እንጂ ስጋና ደም ይህን
አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ። እኔም እልሃለሁ አንተ
ጴጥሮስ /አለት/ ነህ በዚህች ዓለት ላይ ቤተ
ክርስቲያን እሰራለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም ›› አለው ማቴ 13÷19
በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያን እሰራለሁ
ሲል በደቀ መዝሙሩ በጴጥሮስ ሰዉነት ላይ
እንዳልሆነ ግልዕ ነዉ። ይልቁንም ጴጥሮስ
በተናገረዉ ቃል እምነት፣ ምስክርነት ላይ እንጂ
ይህም የህያዉ እግዚአብሔር ልጅ በሚለዉ ፅኑ አለት እምነት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ ማለቱ ነዉ።
ለዚህም ነዉ፤ የቤተክርስቲያን የምዕመናን አንድነትና

ህብረት እንዲሁም የክርስትና ህይወት መሠረቱ
ክርስቶስ ነዉ የሚባለዉ፡፡
ሐዋርያዉ ቅዱስ ጳዉሎስም ለቆሮንቶስ ሰዎች
መልዕክት በፃፈ ጊዜ ሁሉም በክርስቶስ ላይ
ራሳቸዉን እንዲያንፁ ሌላ መሰረትም እንደሌለ አበክሮ
የፃፈላቸዉ፡፡
# እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንዲያንፅ
ይጠንቀቅ ከተመሰረተዉ በቀር ማንም ሌላ መሰረት
ሊመሰርት አይችልምና እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነዉ
$ 1 ቆሮ 3÷10-15
መሰረቱ ክርስቶስ በደሙ በዋጃትና ባነፃት
የእግዚአብሔር ልጅነቱና መሲህነቱ በሚገለፅበት
ትምህርት ላይ ቤተክርስቲያኑ እንደሚመሰረት
መግለፁ ነዉ፡፡
# በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን
ቤተክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን
ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋዉ ሁሉና ለራሳችሁ
ተጠንቀቁ $ ሐዋ 20÷28
ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ደም ፈሳሽነት
የተመሰረተች፣ የጠራችና የነፃች እምነት ናት፡፡ ሁሉም
በክርስቶስ መሰረትነት ላይ ራሱን ያንፃል፣ ህብረት
ይፈጥራል፣ የእግዚአብሔር ቤተሰብም ይሆናል፣ እንደ እግዚአብሔር ፍቃድም
ይመራል፡፡
# እንኪያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋራ
ባለሃገሮችና የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናችሁ እንጂ
እንግዶችና መፃተኞች አይደላችሁም፡፡ በሐዋርያትና
በነቢያት መሠረት ላይ ታንፃችኋል የማዕዘኑም ራስ
ድንጋይ ኢየሱስ ክርስቶስ ነዉ፡በእርሱም እናንተ
ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን
በመንፈስ አብራችሁ ትሰራላችሁ፡፡ $ ኤፌ

2÷19- 22
በሐዋርያትና በነቢያት ላይ ታንፃችኋል ሲል
ሐዋርያት ስለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማሩት
የእዉነት ትምህርት ላይ ታንፃችኋል ማለቱ ነዉ።
የሐዋርያትና የነቢያት ትምህርት ኢየሱስ ክርስቶስ
በእዉነት የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ለሰዉ ልጅ
ድነት ሲል በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት
እንደተወለደ በየጥቂቱ እንዳደገ ለሰው ልጅ ኃጢአት ያለ በደሉ ተላልፎ እንደ ተሰቀለ እግዚአብሔርም የሞትን ጣር አጥፍቶ እንዳስነሳው የሚያስረዳ እውነት ነው።
ጴጥሮስ ከመንፈስ ቅዱስ መዉረድ በኋላ የወይን
ጠጅ ጠጥተዉ ሰክረዉ ለመሰሏቸዉ አይሁድ
ያስረዳዉም ይህንን እዉነት ነበር # አይሁድ
በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ሁላችሁ ይህ በእናንተ
ዘንድ የታወቀ ይሁን ራሳችሁ እንደምታዉቁት የናዝሬቱ
ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል
ባደረገዉ ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም
ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰዉ ነበር።
እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነዉ አሳቡና በቀደመዉ እዉቀቱ ተሰጥቶ በወንበዴዎች /
አመፀኞች/ እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት እግዚአብሔር
ግን
የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሳዉ። ሞት ይይዘዉ ዘንድ
አልቻለምና$ ሐዋ 2÷14 - 25
ሐዋርያዉ ጴጥሮስ እንደገለፀዉ ክርስቶስ ዘመኑ
በደረሰ ጊዜ በቤተልሄም በተናቀ ቦታ ተወለደ
በየጥቂቱም አደገ በሰላሳ ዘመኑም ተጠመቀ
ወንጌልን አስተማረ ህሙማነ ስጋን በተአምራት
ህሙማነ ነፍስን በትምህርት አዳነ ለዕዉራን ማየት
ለታሰሩ መፈታትን ለተጠቁ ነፃነትን ሰበከ ነገር ግን
በምኩራብ አገልጋዮች በአይሁድ ሊቃነ ካህናት ክስ

ቀረበበት የክርስቶስ ሞት የስርየት እንጂ የቅጣት ሞት
አይደለምና ይሙት በቃ የሚያሰኝ ኃጢአት
ባይገኝበትም በጲላጦስ አደባባይ በዋለዉ ችሎት
ይሙት በቃ ተፈረደበትና በመስቀል ላይ ተሰቀለ ነገር
ግን በግፍ አጣድፈዉ ለሰቀሉት የሰዉ ልጆች
ምህረትን ለመነ # አባት ሆይ የሚሰሩትን አያዉቁምና
ይቅር በላቸዉ እነሱ ለእርሱ ካላቸዉ ጥላቻ ይልቅ እርሱ ለእነሱ ያለዉ ፍቅር በልጦ ምሕረት
በለመነላቸዉ ጊዜ አዳም ከበደለ ጊዜ ጀምሮ የሰዉ
ልጆች እንዳይገቡበት ተዘግቶ የነበረዉ የገነት በር
ተከፈተ በሰይጣን ቁራኛነት ተይዘዉ ለነበሩ ነፍሳት
በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ግዕዛነ ነፍስን /ነፃነት/
ሰበከላቸዉ በዚህ ጊዜ የምዕመናን አንድነት መሰረት
ተጣለ ይህችዉም የክርስትና እምነት /ቤተ ክርስቲያን/ ናት በዚህ እውነት ላይ ያልተመሰረተ
ክርስትና በአሸዋ ላይ እንደተሰራ መሰረት እንደሌለዉ
ቤት ነዉ። ንፋስ ነፈሰ ዝናብም ዘነበ ጎርፍም ጎረፈ
ቤቱንም ገፋዉ ቤቱም ወደቀ አወዳደቁም የከፋ ሆነ።
ማቴ 7÷27

3. የክርስትና እምነት ምንነትን መረዳት

የክርስትና እምነት ምንድን ነዉ; ብዙ ሰዎች
ክርስቲያን እንደሆኑ ያምናሉ ይናገራሉ ብዙዎችም
በዚህ ስም ይጠራሉ። ለመሆኑ የክርስትና እምነት
ሲባል ምን ማለት ነዉ;
እምነት በራሱ በእኛና በእግዚአብሔር በማዳኑና
በመዳናችን መካከል ያለ የዉል ስምምነት ቃል ነዉ።
የዉል ስምምነት በሁለት ሰዎች መካከል ለተገባቡት
ቃል እማኝ ማሰሪያ ነዉ። ቤት የሚገዛና የሚሸጥ
ሰዉ በቤቱ ላይ ላላቸዉ ባለቤትነትና ሻጭነት ወይም
ገዢነት የፅሁፍ ስምምነት ያደርጋሉ። የዉል ስምምነት

ወይም ዉል ይባላል። እንዲሁም በእኛና
በእግዚአብሔር መካከል በማዳኑና በመዳናችን
መካከል ያለ የዉል ስምምነት ቃል እምነት ነዉ።
እመን ትድናለህ እንዳለ እኛ ልናምን እሱ ሊያድነን ! ።
ክርስቲያን ወይም ክርስቲያንነት በኢየሱስ
ክርስቶስ ላመኑ ምዕመናን አህዛብ ያወጡላቸዉ ስም
ነዉ። ክርስቶሳዉያን
የክርስቶስ ተከታዮች ክርስቶስን አማኞች ለማለት ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ
በአንጾኪያ ክርስቲያን
ተባሉ። ሐዋ 11÷26
ስለዚህ የክርስትና እምነት በክርስቶስ ታምነን በእርሱም ተደግፈን የምንኖረው ለደቂቃ
የማያቋርጡት ደክሞኛል ላሳርፈዉ ከብዶኛል
ልጣለዉ የማይሉት እስከ ሕይወት ህቅታ ድረስ የምንኖረው ህይወት ነዉ።
የክርስትና ህይወት የነፃነት ህይወት ነዉ።
በአምላካችን ተደግፈን በህይልና በብርታት
የምንኖረዉ የነፃነት ህይወት በነፃነት ልንኖር ክርስቶስ
ነፃ አወጣን እንግዲህ ፀንታችሁ ቁሙ ገላ 5÷1
ትካዜህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል እርሱም
ይደግፍሃል መዝ 54÷22
የክርስትና ህይወት እንደተለጎመ ፈረስ ወደፊት
ብቻ እያየን ከዓለም ሸምጥጠን የምንወጣበት
ህይወት አይደለም ይልቁንም በዓለም ዉስጥ ሆነን
እንደ ዓለም የማንኖርበት ህይወት እንጂ ።
ኖህ ገና ስለማይታየዉ ነገር ተረድቶ
እግዚአብሔርን
እየፈራ ቤተሰቦቹን ለማዳን መርከቡን በእምነት
አዘጋጀ በዚህም ዓለምን ኮነነ በእምነትም
የሚነገኘዉን ፅድቅ ወራሽ ሆነ ዕብ 11÷7
በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህንን አለም
አትምሰሉ ሮሜ 12÷2

ከክፉ እንድትጠብቃቸዉ እንጂ ከዓለም
እንድታወጣቸዉ አልለምንም። እኔ ከዓለም
እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉም ዩሐ 17÷16
የክርስትና ህይወት የሚመጣዉን ሰማያዊዉን
መንግስት በመጠባበቅ ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ
ዉስጥ የምንቆይበት ህይወት ነዉ። # በልዑል
መጠጊያ የሚኖር ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ
ዉስጥ ያድራል መዝ 90÷1
የክርስትና ህይወት በሞተልን በአምላካችን
ተደግፈን በበጎነት፣ በእምነት፣ በቸርነት፣ በፍቅር
የምንኖርበት ህይወት ነዉ። እንዲህ ባለ ታላቅ
የመንፈስ ልዕልና የምንኖርበት መልካም ህይወት
እንጂ የብዙ ሰዎች ስምምነት አይደለም። ይኸኛዉ
ይሻላል እንያዘዉ ያንኛዉ ይከብደናል እንጣለዉ
ብለዉ በጋራ እንደመተዳደሪያ ደንብ የቀረፁትና
የተስማሙበት
አይደለም።
ክርስትና እንደ ህገመንግስት ድንጋጌ በፓርላማ
ተነስቶ፣ ጉዳዩ ተመርምሮና ድምፅ ተሰጥቶበት
ምዕመናን በዚህ ይተዳደሩ ተብሎ የፀደቀ አይደለም።
የክርስትና እምነት የምናምንበት ብቻ ሳይሆን
የምንኖረዉም ህይወት ነዉ በዚህ ህይወት ዉስጥ
ማለፍ የመንፈስ ልዕልናን ያቀዳጃል የአዲስ ህይወት
አዲስ አኗኗር ነዉ። ሁሉም በአንድነትና በፍቅር
ተስፋዉን እየተጠባበቀ የሚኖርበት ህይወት ነው።
ሐዋርያት በተጠሩበት ጊዜ የተሰበሰቡት ከአሥራ ሁለቱም ነገድ ነዉ። የክርስትና
መስራች ኢየሱስ
ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ሲጠራ ከየነገዱ እንደሆነ
ሁሉ እኛ ወደ ክርስትና ስንጠራ ከየነገዱ ተጠርተን
በአዲስ ህይወት በአዲስ ነገድ የምንኖርበት ህይወት

ነዉ። ስምዖንን ሳይሆን ጴጥሮስን ሳውልን ሳይሆን
ጳዉሎስን ሆነን ምንኖርበት አዲስ ህይወት ነዉ።
<<በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን
መንግስትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው>> ።
ራእ 5÷ 9-11
ይህ የአዲሱ ህይወት ኑሮ ያልገባቸዉ ጥቂት
ግለሰቦች በዚህ ህይወት ዉስጥ ጎሳን ወንዘን
ሲከተሉ ሲሰብኩ እንመለከታቸዋለን።
አሁን አሁንማ በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን
ዉስጥ ከሌላ አካባቢ የመጣ መጤ እንግዳ
ማስቀደስ እንኳን የማይቻልበት ደረጃ እየደረሰ
የመጣ ይመስላል። የእነ ወ/ሮ እገሌ የእነ አቶ እገሌ
ቦታ ነዉ ተብለዉ ሊያስቀድሱ በቆሙበት በግልምጫ
የሚገረፉ በክርን የሚገፉ ብዙዎች ናቸዉ። አንድ
ወቅት የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ በስርዓተ ተክሊል የሚያገባ ሰው የጋብቻ ስነ ስርዓት ላይ በተገኘ ጊዜ
ለሙሽራዉና ሚዜዎች እንኳን ቦታ አለቅም ያለ ሰዉ
አጋጥሞታል። ከቤተክርስቲያንም በግልመጫ
ተባረርኩ የሚል ሰውም ዛሬ ዛሬ ቁጥሩ እየበዛ ነው።
ቢያስቀድሱም ባያስቀድሱም የራሳቸዉ የሆነ ቦታ
የራሳቸዉ የሆነ መቋሚያ ያላቸዉ ቀድሟቸዉ ለመጣ
ግን ቦታም መቋሚያም የሚነፈገዉ ሰዉ ዛሬ ብዙ
ነዉ። ሊስተካከል ይገባዋል።
ክርስትና በሁለት ተደራዳሪ ወገኖች መካከል
ይሄን አትለፍ
አንተ በዚህ ኑር እኔ በዚህ እኖራለሁ ተብሎ የተደረገ
የዉል ስምምነት አይደለም። ክርስትና እንደ ጊዜዉ
ሁኔታ የሚመራ የጥንቱ ዉሳኔ የዛሬን ነባራዊ ሁኔታ
ያላገናዘበ በመሆኑ እንደ ወቅቱ ይቀረፅ ተብሎ

ለድርድር የሚቀርብ አይደለም።
የክርስትና ህይወት ክርስቶስ በደሙ ፈሳሽነት
የዋጃት ያነፃት ምዕመናን ሁሉ ለነፍሳቸዉ ዕረፍትን
ሽተዉ የሚኖሩባት የማታቋርጥ ህይወት ናት።
በዘመናችን በምንኖርበት የክርስትና ህይወት
ተደማጭነትና ተሰሚነትን ያገኘን ጥቂት መምህራን
ክርስትናን /ወንጌልን/ እኛ እንደተመቸን ብቻ
የምናስተምር በመሆኑ ከጊዜዉ እድገትና ስልጣኔ
ጋር ለመጓዝ የልባቸዉ ምኞት የሆነ ጥቂት ምዕመናን
በተለይም /ወጣቶች/ እጅግ በጣም ጥቃቅን በሆኑ
የእምነት ድንጋጌዎች ላይ ሲያተኩሩ እና ከእምነት
ሲርቁ እንመለከታቸዋለን ለምን እንዲህ እንደሆነ
በቦታዉ ቆየት ብለን እንመለስበታለን።
የክርስትና ህይወት ለሳምንት ወይም ለወር
ብቻ ቢሆን ኖሮ ብዙዎቻችን ክንፍ እናወጣ ነበር።
ልባችን በወንጌል የተሰበረ በመሰለን ሳምንት
ሁላችንም ለእግዚአብሔር የማንሆነዉ የለም ስንል እንደመጣለን እኛ ብቻ
ለእግዚአብሔር ስምና ክብር
ጠበቃ
የሆን ያክል ይሰማናል አንዳንዴም ለእግዚአብሔር
ለራሱ ከእርሱ በላይ ስንጠነቀቅለት እንታያለን። ነገር
ግን ጊዜዉ ሲረዝምና ክርስትናም እስከ ህይወት
ሕቅታ ድረስ የምትዘልቅ መሆኗን ስናውቅ እንዘናጋለን፣ ይሰለችናል፣ ይደክመናል፣
እናሳርፈዋለን፣ ይከብደናል፣ እንጥለዋለን። የሰው ልጅ ከክርስትና ሲወጣ ቀስ በቀስ
እነዚህ ባህሪያት ይታዩበታል
§ ሞትና ህይወትን ማስታወስ የእግዚአብሔርን ስም
መጥራት ይተዋል
§ መሳለም ማስቀደስ ያቋርጣል መፆምና መፀለይ
ይተዋል
§ ንስሃ አባቱን ወይም መንፈሳዊ ወንድሞቹን ሲያይ

ይሸሻል ይደበቃል
§ መዋያዉን ይቀይራል የሰዉን መንፈሳዊ ህይወት
መንቀፍ ይጀምራል
§ ቀስ በቀስም ኃጢአትን ይለማመድና እየፈፀመው
ጻድቅ መምሰል ይፈልጋል።
§ ሲገፋም ግልፅ ያወጣዋል ከዚያም ሥርዓተ ቤተ
ክርስቲያን ያፋልሳል ቅዱሳንን ያንቋሽሻል ይክዳል።
<<አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸዉን ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን መልካሙንም የእግዚአብሔር ቃልና
ሊመጣ ያለዉን የዓለም ኃይል የቀመሱትን በኋላም
የከዱትን እንደ ገና ለንሰሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል
ነዉ $ ዕብ 6÷4-6
ስለዚህ በማስተዋል መራመድ ይገባል የክርስትና
ህይወት ወይም እግዚአብሔርን የማግኘት ህይወት
እስከ ህቅታ
ድረስ የማያቋርጡት የህይወት ጉዞ ነዉና። በንጉሥ
ዳርዮስ የንግስና ዘመን በባቢሎን የነበረዉ የታላቁ
ነቢይ የዳንኤል ታሪክ የሚያስረዳን ይህንኑ ነዉ።
ዳርዮስ በመንግስቱና በመሳፍንቱ ላይ ሦሥት
አለቃ ሲሾም አንዱ ዳንኤል ነበር። ዳንኤልም
መልካም መንፈስ ስለነበረዉ ንጉሱ ከመሳፍንቱ
በበለጠ በመንግስቱ ይሾመዉ ዘንድ ወደደ በዚህም
መኳንንቱ ነገር ያሴሩበት ዘንድ ወደዱ። ነገር ግን እግዚአብሔርን ከማምለኩና ከአምላኩ ህግ በቀር
ዳንኤል ላይ ምንም ሰበብ ሊያገኙ አልቻሉም። ስለዚህም ወደ ንጉሱ ገብተዉ በዚህ ወር ከአንተ
በቀር ማንም ወደ አምላኩ እንዳይፀልይ ማንም
ከአምላኩ በፀሎት እንዳይገናኝ፤ ይህን ያደረገ ግን
በአንበሳ ጉርጓድ እንዲጣል ህግና ትእዛዝ እንዲወጣ
እንደማይለወጥም እንደሜዶንና እንደ ፋርስ ህግ

እንዳይለወጥ ትዕዛዙን አፅና ብለዉ የትእዛዙን
ፅህፈት አፃፉት። ዳንኤልም ይህ ህግ እንደተፃፈ
ባወቀ ጊዜ አዘነ። ነገር ግን እግዚአብሔርን የማግኘት
ህይወት የማይቋረጥ የህይወት ጉዞ ነዉና ወደ
እልፍኙ ገብቶ ቀድሞ ያደርግ እንደነበረዉ በየእለቱ
ሦሥት ጊዜ በጉልበቱ ተንበርክኮ በአምላኩ ፊት
ፀለየ፤ አመሰገነም፤ ነገር ሰሪዎቹ ቀድሞውንም
ዳንኤል አምላኩን ሳያመሰግንና ሳይፀልይ
እንደማያድር ያዉቁ ነበርና ወደ ንጉሱ ገብተዉ
ከሰሱት። ዳንኤል ወደ አምላኩ ፀልዩዋል፤ ትዕዛዝህ
የማይሻር ነበር ዳንኤል ግን
ሽሮታል ህግህን ተላልፏል አሉት። ንጉሱም ዳንኤልን
ይወደዉ ነበርና በጣም አዘነ፤ ሊያድነዉም ሞከረ፤
አልቻለም። ንጉሱም ዳንኤልን አለዉ ላድንህ ፀሃይ
እስክትገባ ድረስ ጣርኩ ግን አልቻልኩም ሁልጊዜ /
ዕለት ዕለት/ የምታመልከዉ አምላክህ ያድንህ አለዉ በአንበሳ ጉድጓድም እንዲጣል
ፈረደበት። ንጉስ
ዳርዮስ በንግስና ባለበት በክብሩና በስልጣኑ አንዲት
ነፍስ እንኳ ማዳን አንደማይቻለዉ እለት እለት
የሚመሰገን የሚመለክ የልጆቹ አባት እግዚአብሔር
ግን እንደሚያድን፤ የእግዚአብሔር የማዳኑ ሃይል
ነፀብራቅ በልቡ ተረጭቶ ነበርና እኔ አልችልም የንጉስ
ህግ ሳትፈራ ለአንበሳ ጉድጓድ ሳትደነግጥ እለት
እለት በየጊዜዉ የምታመልከዉ አምላክህ ያድንህ
ብሎ ተወዉ። እለት እለት ያለማቋረጥ የሚያመልከዉ
አምላኩ በአንበሳ ጉድጓድ ተጥሎ ሳለ መልአኩን ልኮ
የአንበሳዉን አፍ ዘግቶ ዳንኤልን አዳነዉ።
<<ዳንኤልም ከጉድጓድ ወጣ በአምላኩም ታምኖ ነበርና አንዳች ጉዳት አልተገኘበትም>> (ዳን 6÷4 - 23)
ብዙ ጊዜ በአለም የምንኖርና በሃሳባችን

ከንቱ የሆነን የሚፈራ ባለስልጣን የቀበሌ መሪ
ባለሀብት ወገን ከከበበን ከሁሉ የሚታደገን ከሁሉ
የሚያወጣን መስሎ ስለሚሰማን ከእግዚአብሔር
ይልቅ ስንመካበት እንስተዋላለን። አንዳንድ ጊዜ
ሰዎች ስንባል መሪ የሚጨብጥ ሹፌራችንን ያክል
እንኳ
በእግዚአብሔር የማንታመንበት ጊዜ አለ። ሹፌሮች
መሪ ከያዙልን የምንፈልገዉ ቦታ እንደሚያደርሱን
በመታመን ያለሀሳብ እንቅልፋችንን የምንተኛ ብዙዎች
ነን። ነገር ግን ሁሉን የሚችል አምላክ መጠጊያና
አምባ መሆኑን አዉቀን በእግዚአብሔር
የምንታመንነና ለነፍሳችን እርፍትን ሽተን በጥላዉ
የምናርፍ በከንዱ የምንታመን ጥቂቶች ብቻ ነን።
በሳምንት እሁድ ስናስቀድስ ወይም በወር
አንድ ጊዜ ግፋ ቢልም በአመት አንድ ጊዜ ለአመት
ንግስ ብቻ እግዚአብሔርን ለማግኘት የምንጓጓ
ሳይሆን እለት እለት ያለ ማቋረጥ የምንታመንበት
ከሆነ እግዚአብሔር እኛን ለማዳን የታመነ አምላክ
ነዉ።
የክርስትና ህይወት ሳያቋርጡ
እግዚአብሔርን የማግኘት ህይወት ነዉ። እስከ
ህይወታችን ህቅታ ድረስ።
4. የተጠራንበትን ጥሪ ማወቅ
ይቆየን

5/ ፀሎትና ስራ
************

► ሰውየው ትዳር ፈላጊ ነው ፤ ያው መልካም ሴት ደግሞ የምትገኘው

ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው ይላልና መፅሀፉ ፤ እሱም ቤተክርስቲያን እየተመላለሰ ፀሎት ወደ እግዚአብሔር ያቀርብ ጀመር ምላሽ ግን አላገኘም። •ታዲያ አንድ ቀን አንድ አባት ጋር ሄዶ እንዲህ ይላቸዋል“ አባቴ ለትዳር የምትሆን ሴት እንዲሰጠኝ እግዚአብሔርን ብጠይቀው ሊሰጠኝ አልቻለም፤ ምናልባት ፀሎቴን ያልሰማበት ምክንያት ይኖር ይሆን?”

► እሳቸው :—ልጄ እውነት እንዳልከው በደንብ በፀሎት ለትዳር የምትሆንህን ሴት እንዲሰጥህ እግዚአብሔርን ለምነኸዋል?

► ሰውየው: — አዎ በደንብ ለምኜዋለው አባቴ

► እሳቸው: — እንደው ለምሳሌ በሳምንት ስንት ግዜ ወደቤተክርስቲያን እየመጣህ ፀሎት ታደርጋለህ?

► ኸረ አባቴ እኔማ እየው ከሰኞ እስከ እሁድ ቤተክርስቲያን ነኝ ቢላቸው ፈገግ ብለው እንዲህ አሉት “ ልጄ ችግሩ ያለው ከአምላክህ ሳይሆን ካንተው ነበር እግዚአብሔርን ስጠኝ ያልከውን ሴት አንተ ሳምንቱን ሙሉ ቤተክርስቲያን ተቀምጠህ ማን ይፈልግልህ? ስለዚህ ስድስቱን ቀን ብትፀልይ አንዱን ቀን ደግሞ የፀለይክላትን ሴት ፈልግበት ” ፀሎታችን ያለእኛ ጥረት ዋጋ የላትም ብዙዎች መፅሀፍ ቅዱስ የሰማይ ወፎችን እዩአቸው አይዘሩም አያጭዱም ይላል ይሉናል ስራ ላለመስራት፤ ልክ ነው ይላል ግን ደግሞ በጥልቀት ከመረመርነው አይበሩም የሚል አናገኝም መብረር ስራቸው ነውና ።

*በሌላም ቦታ ላይ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ነፃ ካወጣቸው በኋላ ከሰማይ መና ቢያወርድላቸውም በአፍ በአፋቸው አላጎረሳቸው ወይም ደግሞ ዝም ብሎ አላጠገባቸውም ለነሱ የተተወ ስራ ግን ነበር ለቅሞ መብላት።

እግዚአብሔር ሁሌም ለሚሰጠን ነገር ከኛ ጥቂት እርምጃ ይፈልጋል ብዙ አሳ ለማጥመድ ጥቂት አሳን ማሳየት ግድ ነበርና፣ በራችን ላይ ቆሞም ሲያንኳኳ ተነስቶ መክፈት ለኛ ተትቷልና።

ምን ለማለት ፈልጌ ነው

እኛ ያሰብነውን ነገር እናድርግ የቀረውን እግዚአብሔር ይጨምርበታል።

Yordanos Haile

2 ተኛ ጴጥሮስ 3፥17

6/ ወዳጆች ሆይ፥ ይህን አስቀድማችሁ ስለምታውቁ፥ በዓመፀኞቹ ስሕተት ተስባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ ፲
ክርስትና በመከራ ውስጥ የሚታለፍ የተጋድሎ ሀይማኖት ነው።
ቤተክርስቲያን አስቀድሞ በአይሁድ ከዚያም አምልኮ ባዕዳንን አፅንተው ይዘው በነበሩ አህዛብ መከራን ተቀብላለች። በዚህም ፅኑ መከራ ውስጥ እንደ ወርቅ ተፈትና የጌታችን መድሐኔታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነትና ጌትነት ከፅንፍ እስከ ፅንፍ መስክራለች። በመንፈስ ቅዱስ ረድኤት ከቤተልሔም ዋሻ እስከ ታላቁ የሮማውያን ቤተመንግስት የተንሰራፋው ክርስትና በአምልኮተ በአዳን ላይ ባገኘው መንፈሳዊ ድል እረፍት ባገኘበት በንጉስ ነገስት ቆስጠንጢኖስ ዘመን ከውስጡ በበቀሉ እንክርዳዶች መልሶ መታወክ ጀመረ። እነዚህ መናፍቃን ከሚዘሩት የክህደት ትምህርት ሌላ ጥላቻና ፀብን በሊቃውንቱና በምእመናን መካከል እንዲሰፍን በማድረጋቸው ከፍተኛ ቀውስ በቅድስት ቤተክርስቲያን ውስጥ ተከስቶ ነበር።
« ምክራቸውን ጥልቅ አድርገው ከእግዚአብሔር ለሚሰውሩ፥ ሥራቸውንም በጨለማ ውስጥ አድርገው። ማን ያየናል? ወይስ ማን ያውቀናል? ለሚሉ ወዮላቸው!» ኢሳ 29፥15
ተንኮል ያሰቡና እኩይ አላማ የሰነቁ ክፉ ሰወች በግልጥ ስማቸውንና አላማቸውን ተናግሮ እኔ እገሌ ነኝ፣ የመጣሁት ለዚህ ነገር ነው ብለው ከሚመጡበት ጊዜ ይልቅ ተንኮላቸውን እንደ ጂራት ከሗላቸው አድርገው ብቅ የሚሉበት ጊዜ ይበዛል። በዚህም ላይ ላዩን ብቻ ተመልክተው ፊት ብቻ አይተው የሚፈርዱ የዋህንንና አውቀው ለመታለል ዝግጁ የሆኑትን ለማታለልና የጥቃታቸው ሰለባ ለማድረግ ይሞክራሉ።
በጌታችንና በመድሐኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ራሳኒቸውን የእርሱ ጠላቶች አድርገው ከፈጣሪያቸው ጋር ሲታገሉ የነበሩ ፈሪሳውያንና ሌሎችም ግብረ አበሮቻቸው ይሔዱ የነበረው በዚህ የተንኮል መንገድ ነበር።
ማቴ 9፥ 10-14
የቤተክርስቲያንን አስተምህሮ ለማስቀረት አላማቸውን ምኞታቸውን በተለያየ ዘዴና ስልት ይጠቀማሉ ለአብነት፦
የመጀመሪያው ስልት፦ ለክርስቶስ ክብር የተጨነቁ በመምሰል ወደ ደቀ መዛሙርቱ በመቅረብ በእነርሱ አማካኝነት ተልዕኮቻቸውን መፈፀም ነበር።
አካሔዳቸው ካለፉት ጥቂት አስርት አመታት ወዲህ ቀስ በቀስ ተቋቁመው የቤተክርስቲያኔቱ ወቅታዊ ፈተና በመሆን ላይ የሚገኙ ራሳቸውን ተሐድሶ ብለው

የሚጠሩት መናፍቃን ናቸው። የኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሀገሪቱን ቋንቋና ባህል በማያውቁ የውጪ ሀገር ሰወች ስትሠራ በመኖሯ ብዙ ችግሮች የደረሱባት በራሷ ልጆች ለመተዳደር ገና እንግዳ በመሆኗ አስተዳደራዊ / የአሰራር ማሻሻያ / ያስፈልጋታል። ይህም ቢሆን አስተዳደሯ ገና በምስረታ ላይ ያለና መቶ አመት እንኳን ያልሞላው በመሆኑ ከመባል ይልቅ መሠረት መጣል ቢቻል የሚቀል ነው፣ ከዚህ ባሻገር ግን ከሐዋርያት የተቀበለችውን አስተምህሮ ትለውጥ ማለት በ«ተሐድሶ» ስም የሚደረግ ስውር አላማ ያለው የመናፍቃን እንቅስቃሴ ስለሆነ ተቀባይነት የሌለው ነው።

ዲያቆን ሔኖክ ሐይሌ በሐመር ተዋሕዶ መፀሀፍ ላይ የተሐድሶወች እንቅስቃሴ ከትናንት እስከዛሬ በማለት ያስቀመጠውን ሎዩ አተታ አብረን እንመልከት፦ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም በኬንያ በኩል አሎፍሬድ ባክስተን በሚባል ሰው የሚመራ CMS { church missionary society } የተሰኘ የመናፍቁ ቡድን ወደ ኢትዮጲያ ገባ።

በአመቱ በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ላይ የሚዘምት ቡድን አቋቋመ በቤተክርስቲያናችን የትምህርት ተቋማት በስውር የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች በድብቅ ማስተማር መጀመራቸው ትልቅ ጉዳት አድርሰዋል። በወቅቱ የተነሱበት አላማ በ 20 አመታት ውስጥ ቤተክርስቲያንን ተረክበው አዳራሽ ለማድረግ ነበር።.......

የተሐድሶ ዘመናዊ የማንሸራተት ስልቶች፦

«ተሐድሶ»ወች ባለንበት ዘመን የመናፍቃንን አስተምህሮ ወደ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን አስርጎ የማስገባት ተልዕኮቸውን የሚፈፅሙት በግልጥም በስውርም መንገዶች ነው።

እነዚህ መንገዶች ቀስ በቀስ ምዕመኑን በማንሸራተት ወደ መናፍቃን አዳራሽ የመግፋት ስልት ነው። የሚያስፈፅሙበት ዘመናዊ መንገድ ደግሞ እንደሚከተለው ነው፦

የቤተክርስቲያኒቱ የአገልግሎት ምንጮች ላይ ሰርጎ መግባት፦ «ተሐድሶ»ወች ከቅርብ ጊዚያት ወዲህ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያንን በግልፅ ከውጪ ሁኖ ከመቃወም ይልቅ ቤተክርስቲያኒቱ አገልጋዮችን ወደ ምታሳድግባቸው የአገልግሎት ውስጥ ሰርጎ በመግባት እንደ አንድ መንገድ በማድረግ እየተንቀሳቀሱ ነው። የቤተክርስቲያኒቱን # ዶግማና ቀኖና ከመንቀፍ ይልቅ እንደ ቤተክርስቲያኒቱ ምዕመናን፦ በመፆም፣ በማስቀደስ፣ ነጠላን በስርአት በቤተክርስቲያን በመልበስ፣

በልዩ ልዩ አገልግሎቶች በመሳተፍ፣ ለቤተክርስቲያን ተቆርቋሪና አለሁልሽ ባይ በመምሰል በምዕመናን ዘንድ ተአማኝነትንና ተሰሚነትን እስኪያገኙ ይሰራሉ።
ለዚህም ነው ስማቸው በኑፋቄ ሲነሳ ለምን ተነኩ ብሎ ከእነርሱ በላይ የሚሟገትላቸውን ሰው ይፈጥራሉ። ለምሳሌ ከመካዳቸው በፊት እያለቀሱ ስለ ድንግል ማርያም ሲያስተምር ሰምተናቸው ነበር የሚባልላቸው መናፍቃን ናቸው።
ከአመታት በፊት በትሪኒቲ መፅሔት ላይ የወጣውና «በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ሆኘ ጌታን ከተቀበልኩ አምስት አመታት አለፉኝ ብሎ የወጣው ዲያቆን ለዚህ ምሳሌ ነው / ትሪኒቲ ቁጥር 4፣ 2002 /።
የአብነት መምህራንንና ሊቃውንትን የምታመርትባቸው ገዳማትና የአብነት ትምህርት ቤቶች፣ የአስተዳደርና የስብከት ወንጌል አገልጋዩችን የምታፈራባቸው የነገረ መለኮት መንፈሳዊ ኮሌጆች፣ ህፃናትና ወጣቶችን የምታሳድግባቸው ሰንበት ትምህርት ቤቶች ዋነኞች የአገልግሎት ምንጮች ናቸው።
«ተሐድሶ»ወች በእነዚህ የቤተክርስቲያን ዋነኛ ምንጮች ላይ አስተምሯቸውን የማስረግ ስራን በመስራት ምንጩን በመበከል ወንዘን የሠበከል ስልትን ለመጠቀም ይሞክራሉ።
እንዲሁም በተዘዋዋሪ የቤተክርስቲያን ልጆችን በማህበር ሊገኙ የሚችሉባቸውን ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የፅዋ ማህበራትን ለተልኮቸው ማስፈፀሚያ ለመጠቀም ይጥራሉ። በአንዳንድ አካባቢ ያሉትን አድባራት ከቤተክርስቲያኒቱ አስተዳደር እይታ ውጪ ለማድረግ ከደብርነት ወደ ገዳምነት እንዲቀየሩና ተመልካች እንዳይኖራቸው ማድረግ የዚሁ ስልት አካል ነው።
በገዳማትና በአብነት ትምህርት ቤቶች ያሉ የቤተ መቅደሱን እድሜ የሚያራዝሙ የነገ ተስፋወችን ወቅታዊ የገንዘብና የቁሳቁስ ችግሮችን በመፍታት ለ«ተሐድሶ» የኑፋቄ ትምህርት መምህራን ማድረግ የመጀሠሪያው እርምጃ ሲሆን ተምረው ሲወጡና በቤተክርስቲያኒቱ የሐላፊነት ቦታወች ሲቀመጡ ከውስጥ ሁነው የማዳከም ተልእኮ እንዲፈፅሙ የሚደረጉ ናቸው። በአሁኑ ወቅትም በቤተክርስቲያኒቱ አስተዳደራዊ ሐላፊነት ላይ ተቀምጠው የቤተክርስቲያኒቱን አገልግሎት በማዳከም ከ«ተሐድሶ»ወች የአመፅ ደሞዝ የሚቀበሉ እንደ ብሉዩ ኪዳኑ ይሁዳ እንደነቢዩ በለአም እንደ ኤልሳዕ ሎሌ እንደ ግያዝ የተቀበሉትን ተቀብለው ምንም እንደማያውቁ በጌታ ፊት የሚቆሙ ብዙወች ናቸው።
በአብነት ትምህርት ቤቶች አልፈው ለ«ተሐድሶ»ወች የሚሰሩት ቅጥረኞችም፦

:::: መርጌታ
:::: ሊቀ ጠበብት
:::: ቀሲስ፣ ዲያቆን ወዘተረፈ
የሚሉት የመአረግ ስሞች በመጠቀም የኑፋቄ ትምህርታቸውን እንዲያስተምሩ ተልዕኮ የተሰጣቸው ናቸው። በመጨረሻም ይህንን ድብቅ እኩይ ተግባር የሚያሳየውን የፓስተር ተሾመ እና የውስጥ አገልጋዮች የክሕደት ስራ በመጋበዝ የዛሬ ፅሁፌን ላጠቃል፦ ማንኛውም ሰው በኢንተርኔት ድረገፁ የተኩላው ለምድ ሲገፈፍ ቁጥር 2 በማለት ይመልከት።
::::: ይቀጥላል :::::

ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ added 2 new photos .
የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ ኑዛዜ
❀❀❀......✝......❀❀❀
7/ እኔ አባታችሁና መምህራችሁ ነኝ ፣ ሁላችሁ ልጆቼ ትእዛዜን አዳምጡ በቅድስት ሥላሴ ማመንን እንድትከተሉና እንድትጸኑ እነግራችኋለሁና።
.
የተወደዳችሁ ልጆቼ እርስ በእርሳችሁ በእውነተኛ ፍቅር ትዋደዱ ዘንድ እለምናችኋለሁ!
.
የተወደዳችሁ ልጆቼ እለምናችሁዋለሁ በፍጹም ሰብአዊነት መልካምን አድርጉ እለምናችኋለሁ!
.
የተወደዳችሁ ልጆቼ እለምናችኋለሁ ዓለም እንድታታልላችሁ አትፍቀዱላት እለምናችኋለሁ!
.
የተወደዳችሁ ልጆቼ እለምናችሁዋለሁ በእግዚአብሔር አገልግሎት ዳተኞችና ቸልተኞች አትሁኑ ብዬ እለምናችኋለሁ!
.
የተወደዳችሁ ልጆቼ ያለማቋረጥ እና ያለ መታከት እንድትጸልዩ እለምናችኋለሁ!

.

የተወደዳችሁ ልጆቼ መለያየትን ከሚያመጣ ንግግር አንደበታችሁን እንድትጠብቁ እለምናችኋለሁ!

.

የተወደዳችሁ ልጆቼ የተጠመቃችሁባትን ቅድስቲቱን ጥምቀት እንድትጠብቋት እለምናችኋለሁ!

.

የተወደዳችሁ ልጆቼ ሰውነታችሁን ለጌታ ንጹሕ አድርጋችሁ እንድትጠብቁ እለምናችኋለሁ!

.

የተወደዳችሁ ልጆቼ መብራታችሁ ፈጽሞ እንዲጠፋ አትፍቀዱ ይልቅስ ብርሃንን እንዲሰጥ እንድታደርጉት እለምናችኋለሁ!

.

የተወደዳችሁ ልጆቼ እግዚአብሔር የሰጣችሁን ትእዛዝ እንድትጠብቁ እለምናችኋለሁ!

.

የተወደዳችሁ ልጆቼ እግዚአብሔርን መፍራት ከእናንተ ጋር እንዲሆን እለምናችኋለሁ!

.....

የተወደዳችሁ ልጆቼ ልጆቼ እኔ እስከ መቼም አልተኛም ... በማንኛችሁም ላይ ቅሬታ የለኝም ... ከእግዚአብሔር ትእዛዛት መካከል ለእናንተ አንዲቱንም ከመናገር እንዳልሸሸግሁ እግዚአብሔር ምስክር ነው። የነገርኳችሁን ሁሉ ከጠበቃችሁ የዕባቡንና የዘንዶውን ራስ ትቀጠቅጣላችሁ። እናም ያልኳችሁን ካደረጋችሁ የምድርን በረከት ትበላላችሁ። ያልኳችሁን ካደረጋችሁ ብርሃናዊያን ኪሩቤል ይጠብቋችኋል። ያልኳችሁን ካደረጋችሁ ሰማያዊ ጸጋ አይጎድልባችሁም።

.............

የተወደዳችሁ ልጆቼ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ስለ ነፍሴ ጸልዩልኝ ፤ ሳልፈቅዳቸውም ሆነ ካለማወቅ የሠራኋቸውን መተላለፎቼን እንዳይቆጥርብኝ እና በፊቱ ዕረፍትን ይሰጠኝ ዘንድ ጸልዩልኝ።

አፀደ ማርያም

8/ ይድረስ ለቤተክርስትያኒቱ ልጆች

ይህ በ ፖስተር የምትመለከቱት ዘማሪ ዮሐንስ ይመር የተሃድሶ ዋና ተላላኪና ጉዳይ አፈፃሚ ነው።

07/02/08 በነበረው ፍኖት ተዋህዶ ማህበር ላይ አጠቃላይ ይዘቱ ሰላማዊ በሆነ መንገድ በተለያዩ ሀገር ለነበራችሁ የቤተክርሰትያኒቱ ልጆች በሰካይቢና በዋትሳብ ሲተላለፍ የበረውን ፕሮግራምን ጉባኤ በመቃወም ታላቅ ሁከት እንዲነሳ እጣረ ያለ የተሃድሶ ጉዳይ አፈፃሚ መሆኑን 16 ደቂቃ በፈጀ ንግግር ሲሳደብና የቤተክርሲቲያኒቱን አገልጋዮች አሸባሪ እያለ ሲሳደብ ሰምታችኃል ለመሆኑ ዮሐንስ ከተናገራቸው ንግግር ለምሳሌ

1 እነ በጋሻው በፀጋ ስለበለጡ ነው

2 አገልጋዮቹ ለቢዝነስ ነው

3 ተሃድሶ የሚባል የለም

4 ሲኖዶስ ማለት የጳጳሳት ክምችት ነው

5 የተሰበሰቡት መምህራን አይደሉም

6 የተሰበሰቡት ለገንዘብ እንጂ ለቤተክርስትያኒቶ አዝነው አይደልም

7 አሸባሪና አልቃይዳ ናቸው በማለት በግልጽ ተናግሮል

እውን በጋሻው የተሰበሰቡት አገልጋዮች በምንድን ነው የሚበልጣቸው በትምህርት ወይስ በክህደት ይህን መልክት ለምታነቡ ሁሉ ዮሐንስ ማነው የሚለውን በድምፁ የተናገረው የተቀዳ ስላ ምንም መወሻሸት የልም። ከዛሬ ጀምሮ ቃላዋዲና ታኦሎጎስ ላይ እንጂ በአውደምህረት ላይ ሰባኪን ወይም ቤተክርስትያንን የምታገለግሉ አገልጋዮች እያላችሁ ይህንን የመናፍቅ ተላላኪ በአውደምህረታችሁ ላይ እዳይቆም በመጨረሻ ለኮምቦልቻ ምዕመንና አገልጋዮች ባዘጋችሁት ጉባኤ ካዘመራችሁት ፍርዱን ከቅዱስ ሚካኤል ታገኙታላችሁ

.........

October 19 at 3:17pm · Public

More

14 people like this.

Zemad Bekele

ይድረስ ለቤተክርስትያኒቱ ልጆች

ይህ በ ፖስተር የምትመለከቱት ዘማሪ ዮሐንስ ይመር የተሃድሶ ዋና ተላላኪና ጉዳይ እፈፃሚ ነው።

07/02/08 በነበረው ፍኖት ተዋህዶ ማህበር ላይ አጠቃላይ ይዘቱ ሰላማዊ በሆነ መንገድ በተለያዩ ሀገር ለነበራችሁ የቤተክርሰትያኒቱ ልጆች በሰካይቢና በዋትሳብ ሲተላለፍ የበረውን ፕሮግራምን ጉባኤ በመቃወም ታላቅ ሁከት እንዲነሳ እጣረ ያለ የተሃድሶ ጉዳይ እፈፃሚ መሆኑን 16 ደቂቃ በፈጀ ንግግር ሲሳደብና የቤተክርሲቲያኒቱን አገልጋዮች አሸባሪ እያለ ሲሳደብ ሰምታችኋል ለመሆኑ ዮሐንስ ከተናገራቸው ንግግር ለምሳሌ

1 እነ በጋሻው በፀጋ ስለበለጡ ነው

2 አገልጋዮቹ ለቢዝነስ ነው

3 ተሃድሶ የሚባል የለም

4 ሲኖዶስ ማለት የጳጳሳት ክምችት ነው

5 የተሰበሰቡት መምህራን አይደሉም

6 የተሰበሰቡት ለገንዘብ እንጂ ለቤተክርስትያኒቶ አዝነው አይደልም

7 አሸባሪና አልቃይዳ ናቸው በማለት በግልጽ ተናግሮል

እውን በጋሻው የተሰበሰቡት አገልጋዮች በምንድን ነው የሚበልጣቸው በትምህርት ወይስ በክህደት ይህን መልክት ለምታነቡ ሁሉ ዮሐንስ ማነው የሚለውን በድምፁ የተናገረው የተቀዳ ስላ ምንም መወሻሸት የልም። ከዛሬ ጀምሮ ቃላዋዲና ታኦሎጎስ ላይ እንጂ በአውደምህረት ላይ ሰባኪን ወይም ቤተክርስትያንን የምታገለግሉ አገልጋዮች እያላችሁ ይህንን የመናፍቅ ተላላኪ በአውደምህረታችሁ ላይ እዳይቆም

በመጨረሻ ለኮምቦልቻ ምዕመንና አገልጋዮች ባዘጃችሁት ጉባኤ ካዘመራችሁት ፍርዱን ከቅዱስ ሚካኤል ታገኙታላችሁ

Like . እንየዉ ታዬ

ምደረ ሌባ እናውቃለን ዋኖቻችሁ የተ ገቡ እናተ ኩቦልቻ የምትህዱት

Like . Wendye Ze Tewahido

# Zemad አትጨነቅ ስለዚህ ሐራዋቃ ተሐድሶ የተለያየ መረጃ ብቻ ሳይሆን ማስረጃም ጨምር በእጀ ገብቷል ከሰሙኑ ይለይለታል።

እመነኝ በከፈታቸው ሁለት ግሩፖች ከ 125 በላይ ሰወችን ሰብስቧል ተጨማሪ

ፋይሎቹን ሳገኝ ለህዝበ ክርስቲያኑ የሚዘምረውን መዝሙር በራሱ ድምፅ አስደግፈን ሰውን እናሳያለን። አሁን የማልናገራቸው ብዙ ስራወቹ በጀ ውስጥ ገብተዋል።
ተዋህዶ ብረሳሽ ቀኝ ትርሳኝ።

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖት መልስ አላት
ኦርቶዶክሳውያን እኛ ከምንቀበለው ፹፩ አሀዱ ከመፅሐፈ ሲራክ ላይ ሚካኤል ዘየካ ይመክረናል ያስተምረል።
ብልህ ሰው መጽሐፍ መስማትን ይወዳል
9/ ሲራ 36 : 2 እንዳለ ከጠቃሚ ምክሮች ውስጥ ጥቂቱን ጽፌልሃለሁና ወዳጄ ምክሩን ስማ !
+
[ ዝም ስለሚልና እንዳገኘ ስለሚናገር ሰው ]
እንዲህ አለ ፦
፨ " እያወቀ ዝም የሚል ሰው አለ ፤ ብዙ ነገር ከመናገሩ የተነሣ ራሱን የሚያስጠላ ሰው አለ " ሲራ 20 : 5
፨ " የሚመልሰውን አያውቅምና ዝም የሚል ሰው አለ ፤ ጊዜውንም እስኪያገኝ ድረስ ዝም የሚል ሰው አለ ፤ አዋቂ ሰው ጊዜውን እስኪያገኝ ድረስ ዝም ይላል ሰነፍ ደፋር ሰው ግን እንዳገኘ ይናገራል " ሲራ 20 : 6 - 7
፨ " እንዳገኘ የሚናገር ሰው ራሱን ያስጠላል ለቃሉም መወደድ የለውም " ሲራ 20 : 19
፨ " ባገኘበት ቦታ ነገሩን የሚናገር ሰው በለቅሶ ቤት መሰንቆ እንደሚመታ ሰው ነው " ሲራ 22 : 6
+
[ የሆነ ያልሆነ ነገር ስለ ሚቀባጥር ሰው ]
እንዲህ አለ ፦
፨ "እምትነግረው እንዳለ ለባልንጀራህ ንገረው ፤ የምትነግረው ነገር ከሌለ ግን እጅህን ባፍህ ላይ አድርገህ ዝም በል ፤ መከበርና መዋረድህ ከቃልህ የተነሣ ነውና " ሲራ 5 : 13

፨ " ፍጻሜዋ ይጎዳሃልና በምንም በምን ሁል ጊዜ ሐሰትን አትውደድ ... ብዙ ናቸው ብለህ ከኃጢአተኞች ጋር አንድ አትሁን "
ሲራ 7 : 13 - 16
፨ " ፍምን እፍ ብትላት ትነዳለች ፤ ትፍም ብትልባት ትጠፋለች ሁለቱም ካንድ አፍ ይወጣሉ " ሲራ 28 : 12
+
[ ፍሬ በሌለው ወሬ ባልንጀራቸውን ስለሚያደክሙ ሰዎች ] እንዲህ አለ ፦
፨ " የሰነፍ ሰው ነገሩ በሩቀ ጎዳና እንዳለ እንደሚከብድ ሸክም ነው " ሲራ 21 : 16
፨ " የድቡሽት አቀበት ሽማግሌዎችን እግራቸውን እንደሚያደክማቸው ፤ ቀባጣሪ ሴትም እንደዚሁ የዋህ ሰውን ታደክመዋለች " ሲራ 25 : 20
+
[ ነግረኸው አስተምረኸው ስለማይሰማ ሰው ] እንዲህ አለ ፦
፨ " ለሰነፍ ሰው የሚነግር ሰው ለተኛ ሰው እንደሚነግር ሰው ነው ፤ ነግረኸው ከጨረስክ በኃላ ምን ተናከርክ ? ይልሃል " ሲራ 22 : 8
+
[በማን መደሰትና ለማን ማዘን እንደሚገባ]
ሲናገር እንዲህ አለ ፨ " ጥቅም የሌላቸው ብዙ ልጆችን አትውደድ ፤ በክፉ ልጆችም ደስ አይበልህ እግዚአብሔር መፍራት ከሌለባቸው ቢበዙም በእነሱ ደስ አይበልህ ... ከሺህ ልጆች አንድ አዋቂ ልጅ ይሻላል ፤ ክፉ ልጅ ከመውለድ ሳይወልዱ መሞት ይሻላል ፤ አዋቂ በሆነ ባንድ ልጅ አገር ትጸናለችና በኃጢአተኞች ልጆች ብዛት ግን አገር ትጠፋለችና " ሲራ 16 : 1 - 4
፨ " ተድላ ደስታው አልፏልና ለሞተ ሰው አልቅስለት ፤ አእምሮው ጠፍቷልና ለሰነፍ ሰውም አልቅስለት ። ከሞተ በኃላ አይመለስምና ለሞተ ሰው ታለቅስለት ዘንድ አግባብ ነው ፤ ከመሞቱ መኖሩ ይከፋበታልና ለሰነፍ ሰው ግን በሕይወት ሳለ አልቅስለት ፤ ለሰነፍ ኃጢአተኛ በሕይወት በኖረበት ዘመን ሁሉ አልቅስለት " ሲራ 22 : 9 - 11
+
[ ስለ ምክርና ከማንስ ጋር መማከር እንደሚገባ] ሲናገር እንዲህ አለ ፦
፨ " ያለ ምክር የምትሰራው ሥራ አይኑር ነገር ግን ሥጋዊን ደማዊን ሁሉ አትመነው

" ሲራ 30 : 38
፨ " የሰልፍን ነገር ከፈሪ ሰው ጋር አትማከር ፤ የትርፍን ነገር ከቅርብ ነጋዴ ጋር አትማከር ፤ የምጽዋትንም ነገር ከንፉግ ሰው ጋር አትማከር የሃይማኖትህንም ነገር ዋጋህ እንዳይቀርብህ ከመናፍቅ ጋር አትማከር ፤ ጨክኖ የመሥራትንም ነገር ከምንደኛ ጋር አትማከር " ሲራ 37 : 11
፨ " ሃይማኖት እንዳለው ከምታውቀው እግዚአብሔርንም ከሚፈራ ልቡናውም እንደ ልብህ ከሆነ ከእውነተኛ ሰው ጋር ምክርህን ተናገር " ሲራ 37 : 12
፨ " ከመምህራን ጋር ተማከር ፣ ጉዳይህም ካዋቆች ሰዎች ጋር ይሁን ፣ ነገርህ ሁሉ በእግዚአብሔር ሕግ ይሁንልህ " ሲራ 9 : 14 - 15
+
[ ሚስጢርህን ከማይጠብቅ ሰው ጋር አትማከር ] ሲል እንዲህ አለ ፦
፨ " ቀሊል ሰው የሰማውን ነገር እስኪያወጣ ድረስ አእምሮውን ያጣል ፤ ልጅ የምትወልድ ሴት በምጥ እንደምትጨነቅ እንደዚያ ይጨነቃል" ሲራ 19 : 11
፨ " የተወጋም ሰው ጦሩን ከላዩ ይነቅል ዘንድ እንዲቸኩል ቀሊል ሰውም የሰማውን ቃል ያወጣ ዘንድ እንደዚያ ይቸኩላል " ሲራ 19 : 12
፨ " የሰማውን ነገር ሁሉ ማስቀረት አይችልምና የቀሊል ሰው ልቡና እንደ ሰባራ ማድጋ ነው " ሲራ 21 : 14
፨ " የሰማውን ነገር ማስቀረት አይችልምና ከቀላል ሰው ጋር አትማከር " ሲራ 8 : 17
+
[ ስለ ገንዘብ ]
እንዲህ አለ ፦
፨ " ገንዘብህን በከንቱ አትበትን ፣ ገንዘብ በቃኝ አትበል " ሲራ 5 : 1
ወዳጄ መናፍቃኑ አቃንተው ከመረዳት ይልቅ ቃሉን አጣመው ያልሆነ ትርጉም ሰተው መጽሐፈ ሲራክን ላለመቀበል ከሚያቀርቡት ምክንያት አንዱ ይሄ ጥቅስ ነው ፤ ሲራክ ገንዘብህን በከንቱ አትበትን ሲል ፦ የጠፋው ልጅ ገንዘቡን ለአዝማሪና ለአመንዝሮች በትኖ እንደጨረሰ አንተም ጽድቅ ልትሸምትበት መክሊት ልታተርፍበት ካልሆነ በቀር ለኃጢአትና ለበደል ገንዘብህን በከንቱ አትበትን ሲል ነው ። ገንዘብ በቃኝ አትበል ሲል ፦ ሰግብግብና ለገንዘብ ሟች ሰው ሁን እያለህ አይደለም
የሴፍ በረሐቡ ዘመን ቤተሰቡን ያተረፈው በጥጋቡ ዘመን በሰበሰበው እህል እንደሆነ

፤ አንተም ባገኘህበት ( በጥጋቡ ዘመንህ ) ካላወከበት ፤ ባጣህበት ( በርሐቡ ዘመንህ ) ለራስህም ለድሆችም አተርፍም አትሆንም ሲልህ ነው ።
ሙሉውን የመጽሐፉን ሐሳብና ትምህርት ሳይረዱ ለመቃወም ብቻ ሲሉ አንዲት ጥቅስ አንጠልጥለው ለሚሮጡ መናፍቃን
ሲራክ ገንዘብህን በከንቱ አትበትን በቃኝም አትበል ያለው ስለምን እንደሆነ ? የበለጠ ግልጽ እንዲሆንላቸው ከተናገረው ውስጥ ጥቂቱን እንይ ፦
፨ " ልጄ ድኃውን ምጽዋቱን አትከልክለው ከሚለምንህ ከድኃውም ዓይኖችህን አትመልስ የተራበች ሰውነትን አታሳዝን ያዘነ ሰውንም አታበሳጭ ... የሚለምንህን ሰው አልፈኸው አትሒድ ... በልቦናው አዝኖ ቢረግምህ ፈጣሪው ልመናውን ይሰማዋልና " ሲራ 4 : 1 - 5
፨ " የድኃ ሕይወቱ ምጽዋት መለመን ነው እምቢ ያለው ሰው ግን ነፍሰ ገዳይ ነው " ሲራ 31 : 25
፨ " ንስሐ ገብቶ የሞተ ፣ ሕጉንም የጠበቀ ፣ በገንዘቡም ያወቀበት ሰው የተደነቀ ነው " ሲራ 14 : 20
፨ " የምትነድ እሳትን ውኃ ያጠፋታል እንደዚህም ሁሉ ምጽዋት ኃጢአትን ታስተሰርያለች ፤ ምጽዋትን ለሚሰጥ ሰው በፍጻሜ ዘመኑ እግዚአብሔር ዋጋውን ያስብለታል በመከራም በተሰነካከለ ጊዜ የሚድንበት ረድኤት ያገኛል " ሲራ 3 : 28
+
[ ቃሉን እያወቀ ስለሚያጠፋ ደፋር ሰው ] እንዲህ አለ ፦
፨ " ሁሉን የሚማር ፣ ብዙ ምስጢርም የሚያውቅ ሰው አለ ነገር ግን ሰውነቱን መጥቀም አይችልም " ሲራ 37 : 19
፨ " መንፈሳዊ ጥበብን ያገኘ ደግ ሰው ነው ነገር ግን ይህንን እግዚአብሔርን መፍራት ( ፈሪሃ እግዚአብሔር ) ይበልጠዋል ፤ እግዚአብሔርን መፍራት ከሁሉ ትልቃለች እሷን የጠበቀ ሰውን የሚመስለው የለም " ሲራ 25 : 10 - 12
+
ሁሉን ተምሮ ፣ ብዙ ምስጢር አውቆ ፣ ለሌላው ጠቅሞ ነገር ግን ራሱን መጥቀም የማንችል የእውቀት እንጂ የእምነት ሰው ያልሆነ ፤ የተጣለ ሰው ከመሆን እግዚአብሔር ይሰውረን ።
የደጋግ አባቶቻችን የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን ።
ሰውን ወዳጅ የምሕረት አማላጅ ቅዱስ ሚካኤል አይለየን ።

+ ሚካኤል ዘየካ +

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖት መልስ አላት
ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ (ዶ/ር) - እመኝ ገጽ ፱፷፪-፱፷፯
10/ "በአፍላ ትጀምራላችሁ በወረት ትተውታላችሁ። ያወቃችሁትን ትረሳላችሁ፤ ያላወቃችሁትን ለማወቅ ትጥራላችሁ፤ የያዛችሁትን ትረግጣላችሁ፤ የረገጣችሁትን ትይዛላችሁ። ምኞታቸሁ ልክ የለውም፤ አምሮታችሁ ብዙ ነው። የአማራችሁን ስታገኙ ወዲያው ይሰላቻችኋል። ተው የተባላችሁትን ትሽራላችሁ፤ የተከልከላችሁትን ትደፍራላችሁ፤ የተፈቀደላችሁን ችላ ትሉታላችሁ። ቤተ መቅደስ እንዳትገቡ ብትከለከሉ ወደ ፊት ቤተ መቅደሱን በመስታዎት ሠርታችሁ መቅደስ ባትገቡም እንኳን ሁሉን ከውጪ ሆናችሁ ማየት ትፈልጋላችሁ። ሁሉን ማወቅ ትፈልጋላችሁ፣ በአንዱም ግን አትጠቀሙበትም። ሁሉ አላችሁ፤ ግን ባዷችሁን ናችሁ። ሃይማኖት እንጅ እምነት የላችሁም!" ...
"መድኃኒት ነው ያልከው?! መቀመሚያውን ነግሬህ ማርከሻውን ሳልገልጥልህ መጀመሪያውን ብቻ ሞጭልፈህ ትተኸኝ ትሄዳለህ። ጥበብን "ሀ ግእዝ" ብዬ ላስተምርህ ብሞክር፣ መንደር ውስጥ በቃረምካት ዕውቀት ተመክተህ በመሰልቸት "ሆ ሳብዕ" ብለህ ቀድመህ ትዘጋዋለህ። የግል ታሪካችሁ ቢታይ ወጥነት የጎደለው ከዚህም ከዚያም የተለከፈከፈ የተማሪ ኮፋዳ ውስጥ ያለ እህል ይመስላል። ተምራችሁ እውቀት ስታገኙ፣ ሠርታችሁ ሀብት ስታፈሩ፣ ከላይ የሆናችሁበትን ሀገር ለቃችሁ፣ ሰፋ ወዳለው እንሒድ ብላችሁ እንደገና ከታች ትጀምራላችሁ። ትቀጥላላችሁ፣ በመጨረሻ ከጀመራችሁበት ትገኛላችሁ። ቸኩላችሁ ትወስናላችሁ ወዲያው ትጸጸታላችሁ። በጽኑ ታማችኋል!"
ከታሪክ ፍቅርንና ልማትን ሳይሆን ጥላቻንና ጥፋትን ለይታችሁ ትቆፍራላችሁ። ከዚያም ቀጥላችሁ የከበረ ማዕድን እንዳወጣችሁ ሁሉ በኩራት ደረታችሁን ነፍታችሁ ሳትመርጡ ሁሉን በአደባባይ ትዘሩታላችሁ፤ እናም ወደ ኋላ ስለታሪካችሁና ስለ ቅርሳችሁ ባሰባችሁ ቁጥር ፍርሃትና ሃፍረት ይሰማችኋል። ስለሆነም ከኋላ ታሪካችሁና ክብራችሁ እየራቃችሁ መጣችሁ። የአሸናፊነትንና የተሸናፊነትን ትርጉም በአንድ ላይ የያዙ ሃውልቶችን ታቆማላችሁ። ለግልጽነትና ለነጻነት እያላችሁ በምታደርጉት ሽኩቻ ዕርቃን ወደ መሆን ወረዳችሁ።

ቅቤ ላይወጣችሁ ትናጣላችሁ። በዚህ ዓለም ጥድፊያ ታማችኋል። ሀገራችሁን ትንቃላችሁ፣ ጥላችሁ ለመሄድ ትፈልጋላችሁ፤ ከሄዳችሁ በኋላ ደግሞ አፍታ ሳትቆዩ አገሬ ናፈቀኝ ትላላችሁ። በቁማችሁ የናቃችሁትን የሀገራችሁን አፈር በሞታችሁ ልትለብሱት ትናፍቃላችሁ። ለሀገሬ አፈር አብቃኝ ብላችሁ በድናችሁን ልካችሁ የወገኖቻችሁን ልብ ትሰብራላችሁ። ግብዝነታችሁ መጠን የለውም። ሁለት ሀገር እንዲኖራችሁ ትፈልጋላችሁ፤ አንዱን በደም ሌላኛውን በመታወቂያ ታስባላችሁ። ከአንዱም ግን በአግባቡ አትኖሩም። ዘመናችሁም በምልልስና በመዋተት ያልቃል። ምን እንደምትፈልጉ አታውቁም እናም ፍለጋችሁ አያልቅም!"

በዚህ የተነሣ ምሥጢር ለመካፈል ቅርስ ለመረከብ የሚያስችል ሰብእና አልገነባችሁም። እኛ የመገናኛውን ድልድይ ስላልሠራንና ከእናንተ ስለራቅን ሳይሆን ስለማታዩት ወይም ማየት ስለማትፈልጉ አለበለዚያም እንደ ልቦለድ ገጸ ባሕርይ የራሳችሁን ያሸበረቀ አስረካቢ ፈጥራችሁ እውኑን ሳይሆን ምናባችሁን መረከብ ፈልጋችሁ ስለምታጡት ነው። እኛ ደግሞ እናንተ ታዩን ዘንድ አላሸበረቅንም፤ ማሸብረቅም አንፈልግም። በዚህ ምክንያት ለእናንተ ምሥጢር ለመንገር፣ ቅርስ ለማውረስ እጅግ ከባድ ሆኗል። እኛ አባቶቻችንን እናምናለን። በእነርሱም ደስ ይለናል። የነገሩንን ተቀብለን ቃል ኪዳናቸውን ጠብቀን እንኖራለን።

"ጽላተ ሙሴ አክሱም ጽዮን እንዳለች ሲነግሩን መጋረጃ ገልጠን፣ ሳጥን ከፍተን እንይ አላልንም፤

ጌታ የተሰቀለበትን የግማደ መስቀሉ ክፋይ ግሼን ማርያም አለ ሲሉን ቆፍረን አውጥተን እንመልከት አላልንም፤

ቅዱሱ ጽዋ መንዝ ውስጥ አለ ሲሉንም ዋሻ እናስስ አላልንም።"

"አባቶቻችንን አምነን፤ ሀገራችን የበረከት ምድር መሆኗን ተረድተን፤ የጌታችንን የጸጋ ስጦታ ተቀብለን በእምነት እንኖራለን። ምንም የለንም፤ ሁሉ ግን የኛ ነው። ድሆች ብንባልም ባለጸጎችም ነን። የተራቆትን ብንመስልም የጸጋ ልብስ አለን። ሐዘንተኞች ብንመስልም ደስተኞች ነን። ስለ ሀገራችን መባረክ፣ ቅድስት ሀገር መሆን፣ ቅዱስ ቅርስ በእጃችን እንዳለ ዓለም እንዲያረጋግጥልን አንፈልግም። የሌለንን አለን፣ ያልተሰጠንን ተቀበልን ብልን የምንኮፈስ ግብዞችም አይደለንምና። የሌለን ነገር ለመጠበቅና ለመታመን ስንል ሥጋችንን እየኀሰምን በገዳም ለመኖር የምንወስን ጅሎችም አይደለንምና"።

በንግግሬ ብርታት የእርሳቸውን ኀሊና አሸንፌ የምንፈልገውን ለማግኘት ብዬ

በተናገርኩት መልስ ምክንያት ሳላስበው ከእርሳቸው የወጣው የንግግር ጎራዴ አእምሮዬን ይሸረካክተው ጀመር። የሚናገሩት ነገር በሙሉ እውነት በመሆኑ የምሟገትበት አቅም አልነበረኝም። ነባራዊ ሀቅ ነውና። በራስ መተማመንን ተላብሰን ድህነታችንን አሸንፈን በዓለም አደባባይ ላይ ቀና ብለን ሀገራችን መሳብ አልቻልንም። ብርቅዬዋን ቅርስ ሉሲን እንኳን አሜሪካ ድረስ የወሰድን፣ ጎብኝ ወደ ቅርስ ይመጣል እንጂ ቅርስ ወደ ጎብኝ ሄዶ የማያውቀውን አዲስ ደካማ ልምድ ያስመዘገብን ሆነናል። ስለግል ኑሮአችን ብቻ የምንኳትን ምስኪኖች ነን። የእኔ የራሴ ሕይወት ምስክር ነው። ቀዳዳ በርሚል የመሙላት ጥድፊያ መሆኑን አውቃለሁና። የእኔ ጎሊና የህፍረት ካባውን ለብሶ ቢመለስም አባ ግን ንግግራቸውን ቀጥለዋል።

"አንተ ደግሞ ፍለጋው የማያልቀው የዚህ ትውልድ ናሙና ነህና አምነህ ሄድ ብለህ አትቀበለኝም። እንደ ቶማስ በዐይንህ ካላየህ፣ በእጅህ ካልዳሰስከው አትረካም። የትውልዱ ሕመም ይህ ነው። አንተም የዚህ ሕመም ተጠቂ ትውለድ ምሳሌ ነህና ጫፉን ነግረንህ በእምነት እንድትኖር ችላ ብንልህ እንኳን ፈልፍለህ ለማወቅ ትዳክራለህ። ያወቅከውን ደግሞ ትዘራዋለህ። አንተ የትውልዱ ጥሩ ናሙና ነህ። አንተን ሊያቆምህ የሚችለው የመንገዱ ማለቅ ብቻ ነው። ሩቅ መንገደኛ የሚያቆመው አንድም መንገዱ ሲያልቅ አለበለዚያ መንገደኛው ራሱ ሲያልቅ ነውና።"

Miko ZE Ethiopia

## 11/ ክርስቲያንና ስነ - ምግባሩ

እስራኤል ከግብጽ ምድር ከባርነት ቀንበር ነጻ ከወጡ በኋላ በምድረ በዳ ሳሉ ማጉረምረማቸውና ፈጣሪያቸውን ማስቆጣታቸው የታወቀ ነው። በዚህም ምክንያት በሙሴ በኩል ሕዝቡ የሚመሩበት ፈቃደ እግዚአብሔር የሚፈጸምበት ሕግ በደብረ ሲና ተራራ ተሰራ። ሙሴም ሕዝቡ ፈጣሪያቸውን የሚያመልኩበት ከኃጢአት ርቀው የሚጠብቁትን ሕገ ኦሪት ከእግዚአብሔር እጅ ተቀብሎ ለሕዝቡ አውጆአል። ሕዝቡም ይህም አምላካዊ ሕግ ተቀብሎ ሲጠብቀውና ሲመራበት መኖሩ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ አመጸኞች ሲቀጡበት ሕግ ፈጻሚዎች ሲመኩበት ሲመሰገኑበትና ከአምላካቸው ዘንድ በረከትን ሲቀበሉበት ኖረዋል። ይህም ሲወርድ ሲዋረድ እስከ ዘመነ ወንጌል ደርሷል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የሕግ ፈጻሚ እንደመሆኑ መጠን ለሙሴ የተሰጡትን አስሩን ትእዛዛት በስድስቱ ቃላተ ወንጌል የረዘመውን በማሳጠር የላላውን በማጥበቅ በማሳጠርና በመጠቅለል ለተከታዮቹ አስተምሯቸዋል። በዚህም ሕጉም ፍጹም ሊሆን ችሏል። ለተከታዮቹም ከወደዳችሁኝ ሕጌን ጠብቁ በማለት አዝዞአቸዋል። በዚህ መልኩ የሱ ተከታይ የሆነ ሁሉ ይህን ሕግ መጠበቅ ይገባዋል። እንግዲህ ማመን ከመረዳት የተነሳ ነው። መረዳትም ከመማርና ከማንበብ የተነሳ ነው። እንደተባለው ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማንበብና ለመማር አመቺ ይሆንልን ዘንድ ይህን ክርስቲያናዊ ስነምግባር የሆነውን አምላካዊ ሕግ የሆነውን አስርቱ ቃላትንና ስድስቱ ቃላተ ወንጌልን አስሩ አንቀጸ ብጹአንን እንዲሁም አንቀጸ ምጽዋትን አንቀጸ ጸሎትንና አንቀጸ ጾምን በቅደም ተከተሉ መሰረት እንማረዋለን። ይህ ቃል ለጊዜው ለተወሰኑ ሰዎች ቢሰጥም ፍጻሜው ግን በአለም ዙሪያ ለሚገኙ ሰዎች ነው። ይህም ክርስቲያናዊ ስነምግባር በሦስት ክልሎች ይከፈላል።

አንደኛው ክፍል አስርቱ ቃላት ወይም ኦሪታዊ ሕግ የሚባለው ነው።

ሁለተኛው ክፍል ስድስቱ ቃላተ ወንጌል /ሐዲስ ሕግ/ የሚባለው ሲሆን

ሦስተኛው ክፍል አንቀጸ ብጹአን በመባል ይታወቃሉ።

አንደኛ ክፍል ክርስቲያናዊ ስነምግባር በሁለት ክፍል ይከፈላል። ከአንድ እስከ ሦስት ያሉት አንቀጾች የአምላክን ሕልውና ቅዱስነት ክቡርነት እንዲሁም አምልኮታችንን ተገዢነታችንን ለአምላካችን ለእግዚአብሔር የምናሳይባቸው መንገዶች ሲሆኑ የቀሩት ስድስቱ አንቀጾች ግን ማንኛውም ሰው ለሁሉም የሰው ልጅ ሴት ወንድ ትልቅ ትንሽ ሳይል የሚያደርገውና የሚፈጽመው ሕግ ነው። እነዚህም አንቀጾች ሰው ከሰው አብሮ የመኖርን ዘዴ የሚያስተምሩ ሰላምና ፍቅር አንድ እምነት መተሳሰብ የሚገኝባቸው የሰው ልጅ ሁሉ ተባብሮ ሊጠብቃቸውና ሊፈጽማቸው የሚገባው መሆኑን የሚገልጹ ናቸው። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ሕገ መንግስት አውቀን ኑሮአችን የሰላምና የጤና የፍቅር ኑሮ ይሆንልን ዘንድ ቃሉን ማጥናትና በቃሉ መኖር በተማርነው ትምህርት መጽናትና መመላለስ ይኖርብናል። እግዚአብሔር ዓይነ ልቦናችንን ይክፈትልን አይነ ልቦናችንንም ያብራልን አሜን።

ከእኔ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ

በእግዚአብሔር ሕገመንግስት እና በክርስቲያናዊ ስነምግባር ትምህርታችን በመጀመሪያው አንቀጽ የምንማረው ስለ አምልኮተ እግዚአብሔር ይሆናል። ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ በላይ በሰማይ በዚህም በምድር እንደሌለ

እንረዳለን እሱ እራሱ እግዚአብሔር ዘላለማዊና በማይሻረው ቃሉ ተናግሯል። እግዚአብሔር አምላክ ይህን የአምልኮት ስርአት የሰጠው ለአብርሃም ዘሮች ለእስራኤል ነው። እስራኤልን ከግብጽ ምድር በብዙ ድንቅ የተአምር ስራ ከባርነት ቀንበር ነጻ ካወጣቸው በኋላ የሚሄዱበት አገር በተለያየ የጣኦት አምልኮ የረከሰና የተበከለ ስለሆነ በዚህ አይነቱ አምልኮ እንዳይረከሱና እንዳይበከሉ አስቀድሞ ይህን የአምልኮ ስርአት ሰራላቸው በቀድሞ ግዜ እንደዛሬው ሁሉ የኃጢአት አይነቱ ስራውም ሳይበዛ ዋናው ኃጢአት አመልኮ ባእድና እውነተኛውን አምላክ ቸል ማለት ነበር።

በሌላ ባእድ አምልኮ ጣኦት እንዳይሰናከሉ ከፍተኛ መመሪያ ሰጣቸው ነገር ግን እስራኤል እውነቱን በሐሰት አምላክነቱን በጣኦት በመለወጥ አሳዘኑት ስለዚህ እኔ እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ ነኝ ሲል ማስጠንቀቂያ ሰጠ ዛሬም ቢሆን ይህን ትእዛዝ የማይፈጽሙትን ሕጉን የዘነጉትን ሰዎች እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ ከእኔ ሌላ ባእድ አምላክ አታምልኩ ወደ እኔ ተመለሱ ይላቸዋል እግዚአብሔር አምላክ በሌላ አጉልና ከንቱ ልማድ እንዳይጠመዱ አስቀድሞ ይህን የመሰለ ሕግ ከሰጣቸው በኋላ አታምልኩ ያላቸውን ጣኦት አመለኩ አታድርጉ ያላቸውን ምስል በፊታቸው አደረጉ በዚህ ምክንያት ቀጣቸው። እንግዲህ እኛም ክርስቶስ ከኃጢአት ቀንበር ነጻ ካወጣን በኋላ በደሙም ካጠበና ከቀደሰን በኋላ እንደገና ተመልሰን የኃጢአት ተገዢዎች ብንሆን እንደ እብራውያን መሆናችን እስራኤልንም መምሰላችን ነው። ዘጸ 32፡1-8። ምክንያቱም አንዱን ልባችንን ለሁለት ከፍለን በሁለት ልብ እግዚአብሔርን ማምለክ እና እንደ እግዚአብሔርነቱ ልናመሰግነው አንችልምና ዘጸ 34፡12-15። ከአንድ ምንጭ መራራና ጣፋጭ ሊቀዳ አይችልም። ዘጸ 23፡13 ያዕ 3፡11። ስለዚህ በእኛም ልብ ውስጥ አምልኮተ ባእድና አምልኮተ እግዚአብሔር መቀረጽ የለበትም እግዚአብሔር እንዲህ አይነቱን አምልኮ አይቀበለውምና። 1ኛ ቆሮ 10፡21-22።

እንግዲህ የእግዚአብሔርን ክብር ምስጋና ውዳሴ እንወቅ እንረዳ እንደ እግዚአብሔርነቱም ልናመሰግነው ልናከብረው ልናወድሰው ከፍ ከፍ ልናደርገው ውለታውን ልናስታውስ ይገባናል።

ማር 12፡30 እውነተኛ አምልኮተ እግዚአብሔርን በፍጹም ልባቸው በፍጹም ሐሳባቸው መውደድ ነው። ማቴ 7፡21 ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት የምንችለው ፍቃዱን ስንፈጽም ነው። ዮሐ 4፡22-24 እውነተኛ አምልኮ በልብ

ዝንባሌ እንጂ በቦታ አይወሰንም። ዘጸ 23፥19 የተመረጠውን መልካም የሆነውን ለአምላክ መስጠት ከሱ ተገኝቷልና። ዘጸ 19፥10-11 የምናመልከው ሁሉ በአካልም በኑሮም ንጹሕ ሕልውና ሊኖረን ይገባል።
ቀናተኛ አምላክ ነው ሕዝ 8፥3-18 በቤተመቅደስ ውስጥ የቆመውን ጣኦት ለሕዝቅኤል እግዚአብሔርን አሳየው። 2 ዜና 33፥1-17 ምናሴ ሰሎሞን በሰራው ቤተመቅደስ ውስጥ ጣኦት በማቆሙ እግዚአብሔርን አስቀና። መዝ 77፥55-64 የእስራኤል ልጆች እግዚአብሔርን አስቆጡት እንደ ጠማማ ቀስትም ተገለበጡ። 1ኛ ነገ 18፥21 እስከመቼ ድረስ በሁለት ሐሳብ ታነክሳላችሁ።
የምታመልኩትን ምረጡ ኢያ 24፥15
1ኛ ነገሥት 19፥10-14 ለሰራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀንቻለሁ ቃልኪዳንህን ትተዋልና 14 ቁ።
የአምላክህን ስም ከንቱ አታድርገው ዘጸ 20፥7
ስመ ማለት ግብርን ጸባይን ሁኔን የሚገልጽና የሚያንጸባርቅ ነው። የእግዚአብሔር ስም ይህንኑ ነው የሚያስረዳው። ስለዚህ ቅዱስና ክቡር ከስም በላይ የሆነውን ስሙን በከንቱ እንዳንጠራ በክርስቲያናዊ ስነምግባር ትምህርታችን አምላካዊ ሕግ ያስተምረናል። አንደኛው አምልኮተ እግዚአብሔር ቀጥሎ ይህ ሁለተኛ አንቀጽ በውስጡ የያዛቸው ፍሬ ነገሮች ማንኛውም ሰው ስመ እግዚአብሔርን በከንቱ ጠርቶ እንዳይቀጣ እንዳይቀሰፍ ሁሉን ቻይ የሆነውን እግዚአብሔርን እንዳላዋቂ ምንም እንደማያይ እንደማይሰማ ቆጥሮ እውነቱን በሐሰት እንዳይለውጥ የእግዚአብሔርን ስም ከስም በላይ መሆኑን እንዲያውቅና እንዲረዳ ያስጠነቅቃል። ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ስም ከንቱ ያደረገ ሳይቀሰፍ አይቀርምና። ዘጸ 20፥7።
አንድ ሰው ሥጋዊ ሐብትን ለማትረፍ ሥጋዊ ፍቃድን ለመፈጸም ወይም እውነተኛ ለመምሰል ውሸቱን ሐሰቱን እውነት አስመስሎ ያወራል። ዮሐ 5፥3-9 በዚህም ጊዜ የፈጣሪውን ስም በከንቱ ይጠራል ማለት ነው።
ከሰው ወገን የባልጀራውን ስም ያጠፋ እንደሚፈረድበት በማቴ 5፥22 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሮናል። እንግዲህ ለሰው ስም የሚጠነቀቅ የሰውን መብት የሚጠብቅ እግዚአብሔር ለራሱ ስምማ ምን ያህል ይቀና ይሆን? ክብሩን ለሌላ እንዳንሰጥ ስሙን በከንቱ እንዳንጠራ ይህ ቃል ያስተምረናል። በነብዩ አማካኝነት ክብሬን ለሌላ አልሰጥም ብሏልና። ኢሳ 42፥8። የእግዚአብሔርም ስም በቀልዱ በባልቱ በውሸቱም በሐሰቱም መጥራት ክርስቲያናዊ ስነምግባር አይደለምና

እንደበታችንን መግታት አለብን። በዚህም ላይ እንደ መዝሙረኛው ዳዊት አቤቱ ለአፌም ጠባቂ አኑር የከንፈሮቼንም መዝጊያ ጠብቅ ብለን መጸለይን የዘወትር ተግባር እናድርግ። አንድ ሰው ስሙን በከንቱ ሲጠራ ብናገኘው አላዋዊ ከሆነ ማስተማርና ይህን አንቀጽ ጠቅሰን ማስረዳት አለብን። ግን ሆን ብሎ አድርጎት ከሆነ ማስተባበያ ቃል ልንሰጥበት ይገባል።

በስሙ ታላቅ ኃይል ያደርጋልና ኢሳ 52፡5-6 ይህን ባናደርግ ግን እኛም በነቀፋ እነዳለንበት ይቆጠራል። የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ በምስጋና በጸሎት በውዳሴና በዝማሬ ጊዜ ከዚህም ሌላ በበረከት ጊዜ እውነቱን ከሐሰት ባልተለየበት ጊዜ መጥራት ይገባል። ቅዱስ ጳውሎስ የክርክር ፍጻሜው በመሐላ ያልቃል ይላል። ዕብ 6፡ 16 ስሙን ላከበሩት ምን ያህል በረከትና ክብር እንዳገኙ እንደተደሰቱ ቅዱስ ስሙን በከንቱ የጠሩ የናቁና ያቀለሉ ምን ያህል መርገምና ውርደት እንደደረሰባቸው ከታች ከጥቅሶቹ መሠረት መመልከት ይጠቅማል። ስለዚህ እንደአምላክነቱ እናመስግነው ስሙን ቀድሰን ክብሩን እንውረስ።

የአምላክህን ሰነበት አክብር ዘጸ 20፡8-11

ሰንበት ማለት የቃሉ ትርጉም መተው ማቆም ማለት ነው። እስራኤል ሰባተኛውን ቀን ለእግዚአብሔር የሚቀድሱት እንዲያከብሩት በአስርቱ ቃላት በሦስተኛው አንቀጽ ታዘዋል። ዘጸ 20፡8-11 እስራኤል ስድስት ቀን ሥጋዊ ስራቸውን እየሰሩ ሰንብተው በሰባተኛው ቀን ግን እረፍት የሚያደርጉበት እለት ነበር። በዚህ እለት እንኳን ሰው ይቅርና ከእንስሳት ሳይቀር ሰንበትን እንዲያከብሩ ይህ አምላካዊ ቃል /ትእዛዝ/ ያዛል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከስራው ሁሉ በሰባተኛው ቀን አርፏልና ሰንበትንም ባርኮ ቀድሷታልና። ዘፍ 2፡2-3

እንግዲህ ይህቺን እለት አምላክ ከሰራው ሁሉ ያረፈባት የቀደሳትና የባረካት እለት ስለሆነች በዚህች የእግዚአብሔር እለት መንፈሳዊና በጎ ስራ ልንሰራባት እንጂ ስጋዊ ወይመ ዓለማዊ ተግባርን ልንፈጽምባት እንደማይገባ ከቃሉ መረዳት ይቻላል። ሆሴ 6፡ 6

በሰንበት ቀን መልካም ሥራ መስራትና መንፈሳዊ ስነምግባር መፈጸም እንደሚገባ ጌታ በቅዱስ ወንጌል በሰንበት ቀን ብዙ በሽተኞችን በመፈወሱ ተቃውሞ ቢደርስበትም ለተቃዋሚዎቹ መልስ ሲሰጥ በሰንበት ቀን መልካም ስራ መስራት ተፈቅዷል ነው ያላቸው። ማ 12፡12

ከጥንትም ጀምሮ ሰንበት በመባል የምትታወቀው በእብራውያን ዘንድ የምትከበረው

እለተ ቅዳሜ ነበረች። ኤር 17፥19-27 ከቅዳሜ ይልቅ እሁድ እንድትከበር የሆነበት ምክንያት ጌችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ የተነሳባት ደቀመዛሙርቱም የተገለጠባትና ሰላምን የሰጠባት እለት በመሆኗ ነው። ዮሐ 20፥ 19-22 እንዲሁም በየሳምንቱ እሁድ እየተገለጠ ዘወትር ያጽናናቸው ነበር። በተነሳ በአምስተኛው ቀንም መንፈስ ቅዱስን የሰጠበት እሁድ ቀን ነው። ዮሐ 2፥1-4 ከዚህም ቀን ጀምሮ ዋናዋ ሰንበት እሁድ በመሆን ተከበረች።

ደቀመዛሙርቱም በየጊዜው እሁድ እሁድ አንድነት እየተሰበሰቡ አገልግሎታቸውን መንፈሳዊ ተልእኮአቸውን ይፈጽሙበት ነበር። የሐዋ 20፥7 ምክንያቱም ጌታ አስቀድሞ የሰንበትን ንባብ ከነትርጉሙ አስረድቶአቸዋልና። ሰንበት ለሰው ልጅ ተፈጠረ እንጂ ሰው ለሰንበት አልተፈጠረምና። ማር 2፥27 በዚህ መልኩ የተቀደሰችውን እለት ለተቀደሰ ተግባር ማዋል ይገባናል። የቀደሙትን ክርስቲያኖች መምሰል አለብን። የሐዋ 11፥29-33 የሰንበት አክብሮት ማለት በሽተኞችን መጠየቅ ችግረኞችን መርዳት የአዘኑትን ማጽናናት መሆን አለበት። በዚሁም ሁኔታ እለቷም ሰንበት ትባላለች። እኛም በስም ብቻ ሳይሆን በስራም ክርስቲያኖች እንባላለን። የሐዋ 2፥44-47 11፥29-30 ለሥጋ ብቻ አልተፈጠርንም ከመንፈስ የተወለድን መንፈስ ቅዱስም በውስጣችን ያለ የመንፈስ ቅዱስ ልጆች ነንና። ዮሐ 1፥12-13። ቲቶ 3፥4-7 ይመልከቱ። ስለዚህ መንፈሳዊ ስራ መስራት ክርስቲያናዊ ስነምግባር መሆኑን አንዘንጋ።

እናትና አባትህን አክበር ዘጸ 20፥12

ከእግዚአብሔር በታች ልናከብራቸው የሚገባን ወላጆቻችንን ነው። በእነሱ አማካኝነት ወደዚህ ዓለም መጥተን ከቁጥር ገብተናል። ስለዚህ ውለታቸውን በሚገባ ልንመልስላቸው ይገባናል። ወደ እግዚአብሔር አባትነትም የሚያደርሱን እነሱ መሆናቸውን አንዘንጋ። ምክንያቱም መክረው አስተምረው አስፈላጊውን እንክብካቤና አስተዳደግ በማድረግ ነው። ወደ እግዚአብሔር ልንቀርብ የምንችለው ውለታቸውን ጠንቅቀን ያወቅን እንደሆን ነው። ማንኛውም ሰው ለወላጆቹ መልካም ስራና በጎ ተግባር ሊሰራና ሊያደርግ ይገባዋል።

ያለዚያ ይህንን መልካም ስራና በጎ ተግባር ለሌለው ሰው እንዴት ሊፈጽም ይችላል? እግዚአብሔር ሰውን ከሌላው ፍጥረት ለይቶ ስለወደደው እና ስላፈቀረው ከሱ ቀጥሎ ሁለተኛውን ደረጃ በመያዝ እንዲከበር አደረገው። ሰው ከሌሎች ፍጥረታት የሚለየውና ክብር የሚያስጠው ወላጆቹን በሚገባ ስለሚያከብርና ስለሚያገለግል

ነው። ስለዚህ የወላጆቹን ትምህርት ተግሳጽና ምክር በደስታ ሊቀበል ይገባዋል። ማቴ 19፡18 ኤፌ 6፡1-3 ምሳሌ 1፡8-9 ልጆች ወላጆቻቸውን እንዲያከብሩ ያስተምራል።

አትግደል

በእግዚአብሔር መንግስት በአምስተኛው አንቀጽ ሰው በማንኛውም ምክንያት የሰውን ነፍስ እንዳይገድል፣ እንዳያጠፋ አትግደል ሲል ያውጃል። ህይወትን ለማሳለፍ ስልጣንና ችሎታ ያለው ልዑል እግዚአብሔር ብቻ ነውና። 1ኛ ሳሙ 2፡6። ሰው እንኳን በሌላው ነፍስ ይቅርና በራሱ ነፍስ እንኳን ስልጣን የለውም። የአባት ነፍስ የእኔ ናት የልጅም ነፍስ የእኔ ናትና ይላል። ሕዝ 18፡4። ለሞት ምክንያት የሚሆኑትና የሰው ነፍስ ሊጠፋባቸው የሚችሉ መሳሪያዎች ከዚህ እንደሚከተሉት ተዘርዝረዋል።

ቁጣ ብስጭት ዘፍ 4

ቅናት ምቀኝነት ዘፍ 37

የራስን ጥቅም ብቻ በመፈለግ 1ኛ ነገሥት 20፡1-25

በቂም በበቀል 2ኛ ሳሙ 1፡28-29 ከዚህም ሌላ ስካርን አለመጠንቀቅ እብደትን ያጠቃልላል።

በነዚህ የተለያዩ ምክንያቶች የሰው ነፍስ ይጠፋል። ከእንግዲህ ያለው አጉል ጠባይ የሰው ልጆች እንዲርቁና እንዲጠነቀቁ ይህ ክርስቲያናዊ ስነምግባር አምላካዊ ቃል አትግደል ሲል ያስተምረናል። እንኳን መግደል ቀርቶ ወንድሙን የተሳደበና ያሳዘነ የገሐነም ፍርድ እንደሚገባው ጌችን በማቴዎስ 5፡21-24 አስተምሮናል። እንኳን የእግዚአብሔርን ስራ ማበላሸት ቀርቶ አንድ ተራ ሰው የሰራውን ማበላሸት እንዴት ያሳዝናል። ሰው ለሰው እረዳቱ እንጂ እንቅፋቱ እንዲሆን አይገባውም። ሰው ለሰው ክብሩ እንጂ ውርደቱ መሆን የለበትም። ማንኛውም ሰው ያለ ሰው ሊኖር አይችልምና። ዘፍ 2፡18 አንድ ክርስቲያን ሊገላቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ። እነዚህም ምኞትን መተው /መግደል/ ክፉ ፍላጎትን ከልብና ከመንፈሳዊ ህይወት ማራቅና ማሸሽ /መለየት/ ሮሜ 8፡13 ቆላ 3፡5 ይመልከቱ። በቀል የኔ ነው ስለሚል እግዚአብሔርን መበቀል አይገባንም። 2 ሳሙ 22፡48 ቂምን በመያዝ ፋንታ ጠላቶቻችንን እንድንወድ ታዘናል። ሮሜ 12፡20 ሰው የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ስለሆነ ለቤተመቅደሱ መጠንቀቅ ይገባል። ማንም ቤተመቅደሱን ቢያፈርስ ይፈርሳልና። 1 ቆሮ 3፡16 ይመልከቱ።

ስለዚህ ይህን አምላካዊ ቃልና ትምህርት በህይወታችን እንስራበት። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ስለዚህ ትእዛዝና ሕግ የሚያስተምረን አለ። ሰው ከትዕዛዛት አንዱን አፍርሶ የቀሩትን ቢፈጽም ሁሉንም እንዳፈረሰ ይቆጠራል ካለ በኋላ ምክንያቱን ሲያስረዳ አታመንዝር ያለ ጌታ እንዲሁም አትግደል ብሏል። ባታመነዝርም እንኳ ከገደልክ ሕግን አፍርሰሃል። ያዕ 2፡8 1-13 በዚህ ቃል መሰረት ከክርስቲያኖች የሚጠበቀው ሰውን መጥላት ሳይሆን ሰውን መውደድ ሕግን መተላለፍ ሳይሆን ሕግን መፈጸም መግደል ሳይሆን ጠላትን ሳይቀር መውደድና ማፍቀር ምህረት ማድረግ የክርስቲያን ሁሉ ዋና ተግባሩ ሊሆን ይገባል። ያዕቆብም የሚያስተምረን ይህን ነው። ጭካኔን ሳይሆን ምህረትን እናድርግ ምክንያቱም ምህረትን ለማያደርግ ምህረት አይደረግለትምና። ሆኖም ምህረት ፍርድን ያሸንፋል ምህረትን አንለማመድ እግዚአብሔር ይርዳን።

አታመንዝር

በእግዚአብሔር ሕገ መንግስት በ6ኛው አንቀጽ ክርስቲያናዊ ትምህርታችን ሰው ሁሉ የጋብቻን ሕግ ማፍረስ እንዳይገባው ሲያጠይቅ አታመንዝር ሲል ያውጃል። አመንዝራ ማለት የራስ ያልሆነውን መፈለግ ነው እንጂ ግዴታ ጾታዊ ግንኙነትን ብቻ የሚያመለክት አይደለም። እግዚአብሔር በጥንተ ፍጥረት አንድ ወንድ ለአንድ ሴት አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ ሰጥቶ መፍጠሩን ጋብቻ ክቡር መሆኑን የሚያስረዳ ነው። ይህንንም በአዳምና በሔዋን ተፈጥሮ እንረዳዋለን። ለአዳም የሚያስፈልገውን እንደሰጠው ዘፍ 2፡24 መመልከቱ ይጠቅማል እግዚአብሔር ጋብቻን ሲመሰርትላቸው እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱ እንጂ አንዱ ለአንዱ ሸክም እንዲሆን አይደለም ይህም ዕድል ለሰው ልጅ ብቻ የተሰጠ ስለሆነ የጋብቻን ክቡርነት ያስረዳናል። ዕብ 13 የጋብቻ አላማው ልጅ ለመውለድና ዘር ለተመካት ኑሮንም ለማሻሻል ሁሉንም በየድርሻው ፈቃደ እግዚአብሔርን መፈጸም አለበት። ከዚህ ሌላ በተለያየ ምክንያት ልጅ ላለመውለድ የሚፈልግ ሰው ግን ከተቃራኒ ጾታ መራቅና ለብቻው መኖር አለበት። ዝሙት ይሆንበታልና። ዘማዊ ሰው ግን በነፍሱ ከሚቀጣው ቅጣት አስቀድሞ በሥጋው ይቀጣል። በስንት ወርቅ የማይገኘውን አካሉን ለዘማ ይገብራል። ኃይሉን ይቀንሳል። አእምሮውን ያሳንሳል ጤንነቱን በበሽታ ይለውጣል፣ ትእግስቱን ያጣል። ሰው ተብሎ የሚገመትበትን የክብር ወሰን ያፈርሳል። በዚህ ዓለም ሊከበር የሚገባው አንዱ ክርስቲያናዊ ስነምግባር ጋብቻ ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ባርኮ ሰጥቶአቸዋልና። ማቴ 19፡3-6። ዮሐ 2፡1-11። የጋብቻ 2ኛ ሕግ ንጽሕና ነው። ስለዚህ ክርስቲያኖች በንጽሕና ልንመላለስ ይገባናል ምክንያቱም ከዚህ

የወጣ የሰይጣን ሕግ መሆኑን ማወቅ አለብን። የሰይጣንም ስራ የሰውን የድል በር መዝጋት ደረጃውን ማዋረድ ተፈጥሮውን ማርከስ መሆኑ ግልጽ ነው። ሮሜ 1፥24-27። ዘፍ 19፥4-9 ይመልከቱ። ብዙ በማግባት ዘር ሊበዛ አይችልም 1ኛ ነገሥት 11፥1-13። ሆሴዕ 4፥10። ከዚህ ሌላ ከእግዚአብሔር ርቆ ጣኦት ማምለክ ትእቢተኛ አሉተኛ መሆን በእውነት መንገድ አለመመላለስ አምንዝራ ያሰኛል። ይህንንም በሚቀጥለው ጥቅስ መመልከት ይጠቅማል። ኤር 3፥6-10 ሕዝ 23፥1-49 ማቴ 12፥39 ማርቆስ 8፥38 ይመልከቱ። እግዚአብሔር ሕጉን ያስተምረን አይነ ልቦናችንን ያብራልን። በተጨማሪም የእግዚአብሔር ፈቃድ ከዝሙት እንድንርቅ ነው። 1ኛ ተሰሎ 4፥3። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱም ይህን የመሰለ ቃል እናገኛለን። ሥጋ ግን ለጌታ ነው እንጂ ለዝሙት አይደለም። በማለት ከጌታ ጋር ሕብረት እንዳላቸው በመግለጽ አሳስቦአቸዋል። በመቀጠልም ከዝሙት ሽሹ ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከስጋው ውጪ ነው። ዝሙትን የሚሰራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሰራል ይላል። 1ኛ ቆሮ 6፥18-18 ይህ የጳውሎስ ቃል ለእኛም ሕይወት ያስፈልገናል። ማንኛውም ሰው ኃጢአት በሚሰራበት ጊዜ ከሥጋው ውጪ መሆኑን ተመልክተናል። ዝሙትን የሚሰራ ሰው ግን ሥጋውን እንደሚበድል እንደሚጎዳ ሐዋርያው ያስተምረናል ከዚህ አይነት ስጋንና ነፍስን ጎጂ ከሆነ ሥራ ሁሉ መራቅ ተገቢያችን ነው።

አትስረቅ ዘጸ 20፥15

በእግዚአብሔር ሕገ መንግስት በሰባተኛው አንቀጽ በክርስቲያናዊ ስነምግባር ትምህርታችን ማንኛውም ሰው ከራሱ ገንዘብ ንብረት በስተቀር የሌላውን ሰው ገንዘብ ንብረት እንዳያባክን እንዳይቀንስ እንዳይነካ አትስረቅ ሲል ያውጃል። ሌላው የደከመበትን ገንዘብ ሐብት ንብረት መቀነስ አካሉን እንደማጉደል ነውና ምክንያቱም ሐብት ገንዘብ የሕይወት ምንጭ የደምስር ነውና። የስርቆት ምክንያቱ ስልቱ ብዙ ነው። ግና ስርቆት ይባላል።

1. በግልጽ በማስፈራራት በማስገደድ በሐይል የሚወስዱት ስርቆት ይባላል ግን ይህ አየነቱ ንጥቂያ፣ ቅሚያ፣ ዝርፊያ፣ ውንብድና ይባላል። ሰው የሚወጣበትን የሚገባበትን ቦታና ጊዜ ጠብቀውና አጥንተው ይህን ስራ አድርገው ሲዘርፉ ሲነጥቁና ሲቀሙ ይኖራሉ። ስለዚህ አትስረቅ ያለውን ሕግ አፈረሱ ማለት ነው። ሉቃ 10፥30
2. ጨለማን ተገን አድርገው በስውር የሚሰርቁ አሉ። ይህም አይነት ስርቆት ንቃት፣

ትጋት፣ ቅልጥፍና የኑሮ ዘዴ መስሎአቸው እንደ ታላቅ ስራ ይቆጥሩታል። ሌላው አቅቶት የተወው ለእነሱ ብቻ የተሳካላቸው ይመስላቸዋል። ወንጀል መሆኑንም አያውቁትም።

3. ማታለል፣ ማጭበርበር፣ ስፍር ማጉደል ሚዛን ማቅለል ነው። ይህም ስርቆት መሆኑን ማንም ሳያውቀው እንደ ኃጢአትም ሳይቆጠር ገዢውም ሆነ ሻጩ የሚፈጽሙት ወንጀል ነው። ገበያ ወጥቶ ይህን የማይፈጽም ማንም የለም። ግን ይህን ሰራሁ ብሎ ንስሐ የገባ የለም።

4. ጉቦ መቀበል ነው። ይህም ታማኝነትን ማጉደል ሕዝቡ ይሰራልና ያገለግለናል በማለት መርጦት ሳለ ሕዝቡን ሲያታልል ገንዘቡን ሲበዘብዝ መገኘት ምን ያህል አሳዛኝ ነው።

5. በምትሐት ያልያዙትን እንደያዙ አስመስለው የሚሰርቁትና የሚቀሙት ነው። የሰውን ንብረት ለመውሰድ የሚደረግ ዘዴ ስለሆነ ስርቆት ይባላል። ይህ ሁሉ የስርቆት ስልት ያታላይነት ስራ መሆኑን እያወቀ ይሰርቃል ያታልላል። በዚህም ሁኔታ እንዳለ አቅሙን ሳያውቅና ንስሐ ሳይገባ ከነኃጢአቱ በዚህ ዓለም ይኖራል ብዙ ትርፍ የሚገኘው በመስረቅ በማጭበርበር ይመስለዋል። ግን ያለውን በተወሰነ ዋጋ ቢሸጥ ቢለውጥ ኃጢአት ሳይሰራ ንግዱም ሳይቀር ሁለት አይነት ትርፍ አተረፈ ማለት ነው። ሌላው የአፍ ሌባ ነው። ምሥጢር የሚሰርቅ በድብቅ የሚቀረውን ነገር እንደ መርዶ ነጋሪ የሰማውን በቶሎ ለማውራት የሚቸኩል ማንኛውም በእግዚአብሔር ዘንድ አጸያፊ ነው። ስርቆት ጸያፍ ነው። የሁላችንም ጥብቅ እርምጃ ፍቅር ሰውን ለመጥቀም ይሁን እንጂ ሰውን የሚጎዳ እነዳይሆን መጠንቀቅ ይገባናል። ለስራ እንስለፍ ለስራ ዘወትር የነቃን እንሁን እራሱ እግዚአብሔር ሰራተኛ ነውና። ያለውን ሁሉ ሰርቶ እንጂ ከማንም ቀምቶ ለራሱ አላደረገም። ታማኝነትን እናሳይ የክርስቲያን ስራ ይህ ነውና።

በሐሰት አትመስክር ዘጸ 20፡16

የክርስቲያናዊ ስነምግባር በ8ኛው አንቀጽ ማንኛውም ሰው በሐሰት መመስከር እንዳይገባው በባለንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር ሲል ያውጃል። በሐሰት መመስከር ማለት ጥቅም የሚገኝበት መስሎት እውነቱን ነገር በሐሰት ለውጦ ሐሰትን መናገርና በአደባባይ በሐሰት መማል ነው ወይም ወዳጁን የጠቀመና ጠላቱን የጎዳ መስሎት የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት ሐሰት ይናገራል። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ሐሰት መሆኑን ያውቃል። ስለዚህ ሆን ብሎ ይሰራዋልና በአንድ ጊዜ ሁለቱንም ሕግ አፈረሰ። ከእውነት የወጣው ሁሉ የሰይጣን የግብር ልጁ ነው። ሰይጣን እራሱ የሐሰት አባት

ነውና።
ዮሐ 8፡44 ሰው በሚናገረውም ሆነ በሚሰራው እግዚአብሔርን ምስክር ማድረግ ይገባዋል። እውነትንም መለማመድና ማዘውተር ይኖርበታል። ሐሰት ከሆነ ሐሰት እውነት ከሆነ እውነት እንድንል በቅዱስ ወንጌል ታዘናል። ማቴ 5፡37 የሰው ልጅ መርዝነቱን ሳያውቅ የተጎዳበት ሐሰት ነው። ዘፍ 3፡4-5 የሚያስደንቀው ነገር የሰው ልጅ እባብ ሲያይ ይሸሻል። ሐሰትን ሲናገር ግን ወደ ኋላ አየልም። መርዙ እኔንም ሆነ ሌላውን ይጎዳል ብሎ አያስብም። ክርስቲያን የሆነ ሰው ግን ከእንዲህ አይነቱ የሰይጣን ስራ እጁን ማስገባት የለበትም። በአፉም ሐሰት አይናገርም በቃሉም ውሸት አይናገርም አይገኝም።
የባልንጀራህን ሐብት አትመኝ
በእግዚአብሔር ሕገ መንግስት በክርስቲያናዊ ስነምግባር ትምህርታቸን በዘጠነኛው አንቀጽ ማንኛውም ሰው ከሐብቱ በቀር ሌላ እንዳይመኝ የባለንጀራህን ሐብት ቤት አትመኝ በማለት ያስተምረናል። ምክንያቱም መጥፎ ሐሳብ መጥፎ ስሜት ወደ ማድረጉ ያመራናልና። አንድ መጥፎ ስሜት ያለው ሰው ወዲያውኑ ከልቡ ካልጣለው ከዋለ ከአደረ ዘንድ በሥራ በድርጊት መገለጡ አይቀርም። ከስራውም ዘንድ ሕግ አፍራሽ ይባላል። ኃጢአት በሦስት አይነት መንገድ ይሰራል
በማሰብ
በማየትና በመናገር
በመስራትና በማድረግ ነው።
በዚህ ሁኔታ ሐሳብ የኃጢአት ሁሉ መሰረት ነው ማለት ነው። ሐሳብ ሲመጣ ሲፈጠር ሊመነጭ የሚችለው ስራ ከመፍታት ዋዛ ፈዛዛ ቀልድ በማብዛት እንደሆነ ግልጽ ነው። ስለዚህ ሐሳብ የኃጢአት ሥርና መሰረት ስለሆነ የመጥፎ ነገር የክፋት ምንጭ መሆኑ ከታወቀ በዚህ አይነት ሐሳብ እንዳንጠመድ ሥራን ማዘውተር ይኖርብናል። አንድ ሰው መጥፎ ሐሳብ ሲመጣበት ወዲያውኑ ስመ እግዚአብሔርን መጥራትና ገጹን በመስቀል አምሳል ማማተብ አለበት። ሁለተኛ እንዳያስበው ካላደረገ ኃጢአት አይሆንበትም። በልቡ አላዋለውም አላደረገውምና። ከልብ የተረፈውን አፍ ይናገራል እንደተባለው። ቀንና ሰአት ሳይለይ በየጊዜው የሚአስበውና የሚአሰላስለው ለመስራት ኃይልና ጊዜ አጥቶለት ነው እንጂ የቆየ እንደሆነ ምንም ሳይሰራው ኃጢአት ይሆንበታል። የሰው ልብ ዘወትር ከሐሳብ የማይለይ ስለሆነ ደጉን መልካሙን ጥሩ ጥሩ የሆነውን ነገር መመኘትና ማሰብ ይገባናል። እግዚአብሔር የሚወደውን

መልካም ነገር እንዲገልጽልን እንደ ዳዊት አቤቱ ንጹህ ልብ ፍጠርልኝ ብለን ልንጸልይ ይገባናል።
ባልንጀራህን እንደ እራስህ አድርገህ ውደድ ዘሌዋውያን 19፥16-18
በዚህ የሕግ ሁሉ ማሰሪያና መደምደሚያ በሆነው ክርስቲያናዊ ስነምግባር ትምህርታችን በአሥረኛውም አንቀጽ ሰው ሁሉ ባልንጀራውን እንደራሱ አድርጎ እንዲወድ ያስተምረናል፣ ይመክረናል። ባለእንጀራ ሲባል በቅርብ የሚታወቅ ብቻ አይደለም። በተፈጥሮ የሰው ልጅ የሆነ ሁሉ ለሰው ልጅ ወንድም ባለንጀራ ነው እንጂ እንደራስህ አድርገህ የሚለው አንድ ሰው ለራሱ ክብር ለራሱ ኑሮ መሻሻል ለራሱ ሕይወት ጤንነት የሚጠነቀቀውን ያህል ለባለንጀራውም ሊጠነቀቅና እንደራሱ ሊወደው ይገባል። ማቴ 7፥12 በዚህ ሁኔታ ባለንጀራችን እንደራሳችን እንድንወድ ይህ ቃል ያሳስበናል። እግዚአብሔርን ለመውደዳችን መለኪያ ሚዛኑ ይህ ነውና። 1 ዮሐ 5፥21። የመጀመሪያው አምላካዊ ሕግና ይህ የመጨረሻው ክርስቲያናዊ ስነምግባር መጀመሪያና መጨረሻ ስለሆነ ኦሪትም ነብያትም በነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት እንደተሰቀሉ ጌታ ያስተምረናል። ማቴ 22፥36-40። በሰው ላይ ፍርሐት ይሉኝታ የሚያሳድረው ፍቅር ነው። በሰው ሕሊና ሰላም የሚቀረጸው ከፍቅር የተነሳ ነው። አንዱ ለአንዱ የሚያስብለትና ሊረዳው የሚችል ከፍቅር የተነሳ መሆኑ ግልጽ ነው። ፍቅር ለሰው ልጅ ሰው ለመሆኑ መታወቂያው ፍቅር ነው። በተለይ ለክርስቲያኖች ሁሉ ምልክቻው ፍቅር መሆኑን ማወቅ አለብን። ክርስቶስ ፍቅርን ለተከታዮቹ ልዩ ምልክት አድርጎ ሰጣቸው። የእኔ መሆናችሁን ዓለም የሚያውቀው በፍቅሬ ስትኖሩ ነው ብሎ የፍቅርን ከፍተኛነትና ታላቅነት አስረድቶአቸዋል።
ፍቅር በሰው ልጅ ላይ የሚሰነዘረውን የበደል ፍላጻ የምትከላከል አጥር ናት። ፍቅር ከአለ ጠላት የለም።
ፍቅር ካለ እድሜ ይረዝማል፣ ሁሉን ይወዳል፣ ሁሉን ያፈቅራል፣ ሁሉን ያከብራል። ፍቅር ከሌለህ ግን የአገኘህ ሁሉ ሊያጠፋህ ይፈልጋል። ምቹም ጊዜ ይመርጣል። ወንድሜ ወንድሜ እህቴ እህቴ መባባልን ተማር በዚህም ሕግጋትን ሁሉ ትፈጽማለህና። ፍቅር የስነምግባር ትምህርታችን ማሰሪያ መጀመሪያና መጨረሻ ስለሆነ በፍቅር ጎዳና መመላለስ ይገባናል። በዚህም ትእዛዛትን ሁሉ እንፈጽማለን።
ስድስቱ ቃላተ ወንጌል
በዚህ ርእስ ውስጥ የምናገኛቸው 6 የወንጌል ቃላት ጌታችን መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ የተናገራቸው ለሕዝብ ያስተማራቸውና ቀደም ብሎ

በዘመነ ኦሪት ለሙሴ የተሰጡትን ሕጎች ፍጹማን ያደረገባቸው ናቸው። ስለነዚህ አምላካውያን ሕጎችና ፍጹማንም ስለሆኑ ክርስቲያናዊ ስነምግባር ይባላሉ። ምክንያቱም ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ሊማራቸውና ሊአስተምራቸው ስለሚገባ ነው።

አንቀጽ 1

በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል ማቴ 5፡22

ወንድም ሲባል በስጋ ብቻ የሚዛመድ ሳይሆን በነገድ፣ በቤተሰብ በሐገር በቃልኪዳን በመንፈስ ቅዱስ በሃይማኖት በስራ በመረዳዳት እና በመሳሰለው ሁሉ ወንድም ይባላል። ቁጣ ሲልም በሚገባና በማይገባ አንዱ በአንዱ ላይ ተነስቶ የሚናገረውና የሚፈርደው ነው። ቁጣ ወደ መግደል ከሚያደርሱ ነገሮች አንዱ ነው። ዘፍ 27፡ 44-45። ኃጢአት የሌለበት ተገቢ ቁጣ በማቴ 3፡5 በኤፌ 4፡26 እንመለከታለን። ከቅናትና ከቂም የመነጨ ቁጣ ሰይጣናዊ መሆኑ ግልጽ ነው። ዘፍ 47፡41 ይመልከቱ። ሳኦል በዚህ አይነት ቁጣ ዘወትር ይቆጣ ነበር። 1ኛ ሳሙ 20፡30-34 ያንብቡ። በዚህ ሁኔታ የሚቆጣ ሰው ጠብን ያነሳሳል። ምሳሌ 15፡8። ክርስቲያን ግን ከዚህ መሰል ቁጣ መራቅ ይኖርበታል። ሮሜ 12፡19። ክርስቲያን ሊያስወግዳቸው እና ከነሱም ሊሸሽ ሊርቅ የሚገባው በኤፌ 4፡31 በቆላ 3፡8 ያዕ 1፡19-21 ያሉትን ነው። በለዘብተኛ ምላስ የሌላውን ሰው ቁጣ ማብረድ እንደሚቻል በምሳሌ 15፡1-4 እንማራለን።

አንቀጽ 2

ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ አመነዘረ

ማመንዘር ማለት ሰው ከትዳር ጓደኛው ሌላ ቢወድና ቢለምድ አመነዘረ ይባላል። ጌታ ግን ማንም ሰው በዝሙት ወጥመድ ውስጥ እንዳይገባ አርቆ አጥሯል። ሰው በተግባር የሚፈጽመውን በልቡ ያሰበውን ስለሆነ በልቡም እንዳመነዘረ ይህ ቃል ያስተምረናል። በዚህ ቃል መሰረት የዝሙት የምንዝር ማሰሪያ የሆኑትን ሁሉ ማስወገድ ይገባናል። ማቴ 5፡29። ማቴ 18፡8። ማር 9፡43-58። ምሳሌ 6፡25። የጌታ አባባል ሴትና ወንድ ሳይተያዩ ይኑሩ ማለት ሳይሆን በዝሙት መንፈስ አተኩሮ የሚመለከት አይኑር። አንዱ የሌላውን አይመኝ ማለቱ ነው።

ዝሙት በብዙ አቅጣጫ ይታወቃል። በዘፈን ሮሜ 13፡13 በውዝዋዜ በእንቅስቃሴ ማር 6፡21 በዘመናዊ ሙዚቃ ገላ 5፡19-21 በዓለማዊ ዳንስ /ዳንኪራ/ በነዚህና በመሳሰሉት ነው። ይህን ሁሉ የዝሙት ሐሳብ ልብና ኩላሊትን የሚመረምር አምላክ ያውቃል። ሕዝ 11፡5 ኤር 17፡10 ስለዚህ የልብን ምንዝርነት ማስወገድ ይገባል።

እግዚአብሔር በነብዩ ኤርሚያስ አድሮ የሚያስተምረን እያንዳንዳችን በሰራነው መጠን ዋጋችንን እንደሚከፍለን ነው። ይህን የመሰለ ቃል በመዝ 61፡12 እና በራ 22፡12 እናገኛለን። እግዚአብሔር አምላካችን በአገልጋዮቹ አማካኝነት ያስተማረንን ትምህርት ያስተላለፈልንን መልዕክት ሰምተን በስራ ላይ ማዋል ይገባናል። ዋጋችንን የምንቀበለው በሰራነው መጠን ነውና። 1 ቆሮ 3፡14።

አንቀጽ 3

ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል የተፈታችውንም የሚገባ ያመነዝራል ማቴ 5፡31-32

ዝሙት ቀደም ብለን በአንቀጽ 2 የተመለከትነውን ይመስላል። ይሁን እንጂ ከጋብቻ ውጭ የሚደረግ ማንኛውም አይነት ስጋዊ ግንኙነት ሁሉ ዝሙት ይባላል። ይህም በክርስቲያኖች ዘንድ የተከለከለ ነው። 1ኛ ቆሮ 6፡9-18 በሌላ መልኩ ዝሙት እውነተኛ የሆነውን ያልሆነውን አምልኮ ይገልጣል። ማር 8፡38 እንመልከት። በዝሙት ምክንያት እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየውም ይላል ማቴ 19፡6። ጋብቻ ሕጋዊና ምስጢራዊ በአምላክ የተመሰረተ እንደመሆኑ መጠን ሰው ሁሉ ጋብቻውን አክብሮ መያዝ ይኖርበታል። ዘፍ 2፡21-24። ሙሴም በሆነው ምክንያት ሁሉ ሰው ሚስቱን የፍቺዋን ጽሕፈት ሰጥቶ እንዲፈታ አዞ ነበር። ዘዳ 24፡ 1። ጌታ ግን ሙሴ ይህን ያለበት ምክንያት በማብራራት መልስ ሰጥቶበታል ማቴ 19 አንብብ። የክርስቲያን ጋብቻ ግን እንዲህ አይነት ሳይሆን በስጋውና በደሙ ማህተምነት የታተመ በመሆኑ ምስጢራዊ ጋብቻ ይባላል። 2ኛ ቆሮ 11፡2። ኤፌ 5፡21-33። ጋብቻ ክቡርና መኝታውም የተቀደሰ ነው። ዕብ 13፡4። ስለዚህ ጋብቻን አክብረው።

አንቀጽ 4

እኔ ግን እላችኋለሁ ከቶ አትማሉ ማቴ 5፡34-37

መሐላ ሰው ቃሉን እውነተኛ መሆኑን ለማረጋገጥ የእግዚአብሔርን ስም ወይም ሌላ ነገር ይጠራል። ይኸውም እውነት እንዲሆንለት ነው። ዘፍ 21፡23 ተመልከት። በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን አንዳንድ የእግዚአብሔር ሰዎች እውነትን ከሐሰት ለመለየት እና በእውነት ለመመስከር ሲሉ ስመ እግዚአብሔር ጠርተው ይምሉ ነበር። 1ኛ ነገ 18፡15። መሐላ የነገር ሁሉ ማሰሪያ መደምደሚያ ነው። ዕብ 6፡16። ሰሎሞን ማንም ሰው በጌታ መቅደስ ቢምል እግዚአብሔር በዳኝነት እንዲፈርድ በጸሎቱ እግዚአብሔርን ጠይቋል። 1ኛ ነገ 8፡31-33። ከዚህ በተረፈ

ነገራችን ሁሉ እውነት ከሆነ እውነት ሐሰት ከሆነ ሐሰት መሆኑን እንድንናገር ጌታ አስተምሮናል። ቁ 37 ጌታ አትማሉ ያለበትን ምክንያት በማያስፈልገው ነገርና በሐሰት አትማሉ ማለቱ ነው። ሐዋርያው ያዕቆብም ይህን የመሰለ ቃል ጽፎልናል። ያዕ 5፡12። ማቴ 5፡38-48

አንቀጽ 5

ባለንጀራህን ክፉውን በክፉ አትቃወሙ

ክርስቲያናዊ ስነምግባር የሚያተኩረው በሰዎች ላይ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ክፉ ሲል ሰውን እንጂ ሌላ አያመለክትም። ሰይጣንም ክፉ ተብሏል። ሰይጣንን ግን እንድንቃወመው ታዘናል። ማቴ 5፡37። ያዕ 4፡7። ክፉን በክፉ የምንቃወም ከሆነ ሰይጣንን አልተቃወምነውም ማለት ነው። ክፉውን በመልካም ስናሸንፍ ግን ሰይጣንን መቃወማችን መሆኑን እንወቅ። ሮሜ 12፡21። ይህን ትእዛዝ የምንፈጽመው ብርቱዎች ስንሆን ደካሞች ጥበበኞች ስንሆን ሞኞች በመሆን ነው። 1 ቆሮ 4፡10-13። እንግዲህ ክርስቲያን ክርስቶስን መምሰል ይገባዋል። እሱ ሲቃወሙት አልተቃወመምና፣ ሲሰድቡት አልተሳደበምና። ማቴ 27፡12-14። 1ኛ ጴጥ 2፡23 ተመልከት። ክርስቲያኖች ለክፉዎች ሊጸልዩላቸው ይገባል። የሐዋ 7፡57-60።

አንቀጽ 6

በሰማያት ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙአችሁን መርቁ ማቴ 5፡43-48

በዚህ በስድስቱም ቃላት መደምደሚያ ፍቅረ ቢጽን አፍቅሮ ጸላዕትን እንማራለን። በብሉይ ኪዳን ጠላትህን ጥላ ባለንጀራህን እንደራስህ ውደድ የሚል ነበር ጌ ግን ጠላታችሁን ውደዱ ክፉውን በክፉ አትቃወሙ ሲል ያስተምረናል። በዚህም አባባሉ ጠላትህን ጥላ የሚለውን ቃል ሽሮታል። የእግዚአብሔር ልጆች በመሆን ጠላቶቻችንን መውደድ ክርስቲያናዊ ስነምግባር ስለሆነ ልንፈጽመው ይገባናል። እርሱ የወደደን ገና ጠላቶቹ ሳለን ነውና። ሮሜ 5፡8። ይህን ቃል ሐዋርያው ለቆላስይስ ሰዎች ደግሞ ጽፎላቸዋል። ቆላ 1፡21-2። እግዚአብሔር ሁሉን ይወዳል የሚፈልጉትንም ይሰጣቸዋል።

ማቴ 5፡44-46። እኛም እንደሰማያዊው አባታችን ሁሉን አስተካክለን እንውደድ። ጠላታችን ቢራብ እናብላው ቢጠማም እናጠጣው ሮሜ 12፡20። ስለዚህ መልካም እናድርግላቸው እንጂ ክፉውን በክፉ እንድንቃወም ክርስቲያንነታችን የሚለካው ይህን አምላካዊ ቃል /ትምህርት/ ስንፈጽም ነውና። እግዚአብሔር ይርዳን።

like . Abeba Tesema

E.nde new keresteyanawy senemegebar ketewhedo ement teketay:engy kehamat : ketenkhol keadema kemesaselut keseyetan tegebare yeseda sehone endate des yelale batekersteyanen lemekefafel ena kersetyanen yanget mehatebune beged endebetesu kerstyanen kemeasdedu yetewhedo telathoh gefen telahan yememerun kemketeu sewehe enkoteb sedeben lesedabe a nesetat mane yegel telaha adema bemaderg bebatekersetyan sem angelse yetewahdo amelak ayankelafam yeferdebnal enasetewel yezemdekun adema batekerdetyan leafers. Ayehelem fb gudega enge tewahedo lezelalem tenur

12/ መንፈሳዊ አገልግሎት

በዲ/ን ሕሊና በለጠ ዘኆኅተብርሃን

(መቅረዝ ዘተዋሕዶ፣ ነሐሴ 12 ቀን 2007 ዓ.ም.)፡- በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!!

አገልግሎት የሚለው ቃል ገልገለ ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ እንደሆነ ይጠቁማል። ገልገለ (አገለገለ) ማለት ተገዛ፣ ታዘዘ፣ ዐገዘ፣ ረዳ፣ ጠቀመ፣ ማንኛውንም ሥራ ሠርቶ ጌታውን ደስ አሰኘ ማለት ነው። ስለዚህ አገልግሎት ማለት መታዘዝ፣ መገዛት፣ መርዳት፣ መጥቀም...ማለት ይሆናል። ማንኛውም ሥጋዊና መንፈሳዊ ሥራ አገልግሎት ነው። ለመንግሥት የሚሠራ የመንግሥት አገልጋይ፣ ለግለሰብ የሚሠራ የግለሰብ አገልጋይ፣ ለእግዚአብሔርም የሚሠራ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ አገልጋዮችን በተለያየ ስያሜ ጠርቷል። ምንም አይነት መብት በራሱ

ላይ የሌለውንና በጌታው ሐሳብ ፍፁም አዳሪ የሆነውን ተገዢ ባሪያ በማለት ገልፆታል። ንዋይ ኅሩይ ቅዱስ ጳውሎስ ‘ከሰው ሁሉ አርነት የወጣሁ ስሆን የሚበልጡትን እንድጠቅም እንደባሪያ ራሴን ለሁሉ አስገዛለሁ’ በማለት የተናረው ይህን ያጠናክራል። (1 ቆሮ. 9÷19) አብሮት የሚያገለግለውን ቲኪቆስንም ‘በጌታም አብሮኝ ባሪያ የሆነ’ በማለት ጠርቶታል። (ቆላ 4፥7) ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም አርነት ወጥታችሁ እንደ እግዚአብሔር ቅዱሳን ባሪያዎች ሁኑ በማለት አገልግሎታችን በፍፁም መገዛት እንዲሆን ይመክረናል። (1 ጴጥ. 2፡፥16) በራሱ ላይ ሙሉ ነፃነት ያለውን አገልጋይ መጽሐፍ ቅዱስ ሠራተኛ ይለዋል። (ሉቃ 10፥2፣ ቆላ 4፥11፣ 2 ጴጥ 1፥8) ይህ ከባሪያ ይልቅ በራሱ ላይ የመወሰን ሥልጣን ያለው ነው። ከፈለገ አለማገልገል ይችላል። በባሪያና በሠራተኛ መካከል ነፃነቱ መካከለኛ የሆነው ደግሞ ብላቴና፣ ሎሌ ተብሎ የተጠራው ነው።

መንፈሳዊ አገልግሎት የምንለው የእግዚአብሔር የሆነውንና መንፈሳዊ ዓላማን መሠረት በማድረግ የሚገለገለውን ነው። መንፈሳዊ አገልግሎትን ከሌሎች አገልግሎቶች/ሥራዎች የሚለዩት በርካታ ጠባያት አሉ። ትልቁና መሠረታዊው ልዩነት ዓላማው ነው። በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ የመንፈሳውያን ሰዎችና የሰማያውያን መላእክት ረቂቅ ኅብረትና አንድነት የሚገለፅበት በማይታይ ፀጋ ወደ ክርስቶስ በእውነትና በፍቅር የሚያሳድግ (ኤፌ 4፥15) የሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሥራ ነውና ልዩ ነው። አገልግሎትን ስንተረጉም ማንኛውንም ሥራ ሠርቶ ጌታውን ደስ ማሰኘት ነው ካልን መንፈሳዊ አገልግሎትም ጌታው አንድ እግዚአብሔር ነውና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ማንኛውንም ሥራ መሥራት ነው። (ሮሜ.12፥1) እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት የሚቻለው ደግሞ በዕምነት ብቻ በመሆኑ (ዕብ. 11፥6) መንፈሳዊ አገልግሎት የመታመን ሥራ ነው። ሃይማኖት ማለት ማመንና መታመን ማለት እንደመሆኑ አምላክን አምነን የምንታመነው በመንፈሳዊ አገልግሎት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

መንፈሳዊ አገልጋይ ማነው?

ፍጥረታት ሁሉ አገልጋዮች ናቸው። ቅድስት ሥላሴ አንዱንም ፍጥረት ካለዓላማ እንዲሁ በዘፈቀደ አልፈጠሩምና ይልቁንስ አበው እንዳስተማሩት ሰውና መላእክትን እንዲያመሰግኑ ሌሎቹን ፍጥረታት ደግሞ ለአንክሮ፣ ለተዘክሮ፣ ለምስክርነት ፈጥረዋል። ስለዚህ ላያገለግል የተፈጠረ ፍጥረት የለም። ካልእ ፍጥረታት የሰው ልጅ አገልግሎቱን በዘነጋ ጊዜ ስለ አምላክ እየመሰከሩ ሰውን ወደተፈጠረበት ዓላማ

(አገልግሎት) ለመመለስ በመጣር አገልግለዋል። የበለዓም አህያ (ዘፍ 22) እና የቢታንያ ድንጋዮች (ሉቃ 19) ለዚህ ምስክሮች ናቸው።
ስለ ቅዱሳን መላእክት መንፈሳዊ አገልጋይነት በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ቦታ ተጽፏል። ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ ምዕራፍ 1 ቁጥር 14 ላይ 'ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?' በማለት ከርቀታቸው (ረቂቅነታቸው) የተነሳ መናፍስት ብሎ የሚያገለግሉ ያላቸው መላእክትን ነው። ልበ አምላክ ዳዊትም 'መላእክቱን መንፈስ የሚያደርግ አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል' በማለት (መዝ 103፥4) ይህንኑ አጠናክሯል። ነቢዩ ኢሳይያስና ነባቤ መለኮት ዮሐንስም የምስጋና አገልግሎታቸውን በራእይ ተመልክተው ጽፈውታል። (ኢሳ. 6፥1-6፣ ራዕ. 4፥5-8)
"እንዲያገለግሉኝ ሕዝቤን ልቀቅ" ዘፀ. 7፥16
እግዚአብሔር አምላክ እስራኤላውያንን ከዘመናት የግብፅ ስደት ወደ ምድረ ርስት የመመለሻው ወቅት በደረሰ ጊዜ በሙሴ በኩል ፈርኦንን 'እንዲያገለግሉኝ ሕዝቤን ልቀቅ' (ዘፀ 7፥16) ብሎታል። የእስራኤላውያን ከስደት መመለስ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ነው። በሌላ አነጋገር ከስደት የመፈታታቸው ዓላማ አገልግሎት ነው። ከስደት ተመልሶ እግዚአብሔርን የማያገለግል በስደት ቢኖር ይሻለዋል። 'እንዲያገለግሉኝ' ብሏልና። በተመሳሳይ የሰው ልጅ የመፈጠሩ ዓላማ ሃይማኖት እንደመሆኑና ሃይማኖት ደግሞ የማመንና የመታመን ጉዳይ በመሆኑ፣ እንደዚሁም መታመን በመንፈሳዊ አገልግሎት ስለሆነ እግዚአብሔርን የማያገለግል ሰው የመፈጠሩን ዓላማ ስቷልና ባይፈጠር ይሻለዋል። እዚህ ጋ መንፈሳዊ አገልግሎት ስንል በጠበበው ትርጉሙ የተለመዱትን የክህነት፣ የሰ/ት/ቤት ወይም የመንፈሳዊ ማኅበራትን አገልግሎት ብቻ ማለታችን አይደለም፤ መሠረታዊ የክርስትና ተግባራትንና የምስጋና ሕይወትን አጠቃለልን እንጂ። በዚህ አረዳድ ሰው ሁሉ መንፈሳዊ አገልጋይ ነው። ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስም ሰውን የእግዚአብሔር የተቀደሰ መቅደስ ብሎ የጠራው። (1 ቆሮ. 3፥16)
ታላቁ የቤተክርስቲያን ሊቅ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በሉቃ 6፥38 ላይ ጌታችን 'ስጡ ይሰጣችሁማል' ያለውን ቃል ሲተረጉመው መንፈሳዊ አገልግሎትን የተመለከተ ቃል ስለመሆኑ መስክሯል። ጌታ ስጡ ማለቱ አገልግሉ ማለቱ ነው። የምድሩን ትታችሁ፣ ጊዜያችሁን ሰውታችሁ፣ ጉልበታችሁን ገብራችሁ፣ ዕውቀታችሁን አፍሳችሁ፣ ገንዘባችሁን በጅታችሁ ብታገለግሉ እኔ ደግሞ በጸጋ ላይ ጸጋ፣ በበረከት ላይ በረከት፣

በሕይወት ላይ ቅድስናን እሰጣችኋለሁ ሲል ነው ይላል ሊቁ።

የመንፈሳዊ አገልግሎት መለያዎች

ምንም እንኳን አንድ ሰው ቅዳሴ፣ ምስጋና፣ ምስክርነት እና የመሳሰሉትን ከኹላዊት ቤተክርስቲያን የተገኙ ሁሉንም የሚያሳትፉ ኹላዊ አገልግሎቶች ላይ መሳተፍ ግዴታው ቢሆንም በሰንበት ት/ቤቶች፣ ቤተክርስቲያን ማኅበራት ወይም በተለያዩ መንፈሳዊ ኃላፊነቶች ለማገልገል የሚያስብ ከሆነ የመንፈሳዊ አገልግሎት የተለዩ ጠባያትን አጥርቶ ማወቅ አለበት። ይህ ካልሆነ አገልግሎቱ እንደማንኛውም ዓለማዊ ሥራ ከመሆኑም ባሻገር በረከት የተለየው ድካም ይሆናል። ስለዚህ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦች በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ላሉ አገልጋዮችም ሆነ ለማገልገል ለሚሹ አስፈላጊ ናቸው።

1. በእምነት (በመንፈስ) ማገልገል

መንፈሳዊ አገልግሎት በምድራዊ አመክንዮ (logic) ያልተሳሰረ መሠረቱም ጉልላቱም ረቂቅ እምነት የሆነ የአምልኮ ዘርፍ ነው። በእግዚአብሔር ሳያምኑ መንፈሳዊ አገልጋይ መሆን አይቻልም። ዕምነት የመጀመሪያው አንድ አገልጋይ ሊያሟላ የሚገባው ሰማያዊ የመንፈሳዊ አገልግሎት ስንቅ ነው። ሳያምኑ ማገልገል ድካም ነው። የመንፈስ ዝለትንም ያመጣል። አንድ ጥሩ እምነት ያለው አገልጋይ ከአላስፈላጊ ጭንቀት ነፃ ስለሆነና መንፈስ ቅዱስን የአገልግሎቱ መሪ ስለሚያደርግ የሚያገለግለው በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደለም። ይህም ማለት አገልግሎቱ የረቀቀ ነው። ምናልባትም ከአእምሮ በላይ ሆኖ በምን ችሎታ ይህን አደረገው? በየትኛው ጊዜው ሠራው ብለን የምንደነቅበት ነው።

ብዙ አገልጋዮች ትልቁ ችግራቸው አገልግሎታቸው በአእምሯዊ ቀመር (calculation) ብቻ የተሰላ መሆኑ ነው። እግዚአብሔርን በፀሎት የሚጠይቁ እንኳን ጥቂት ናቸው። ስለዚህ እንደማንኛውም ሰው ግዙፍ ግዙፉን እንጂ ረቂቁን ርካታና ፀጋ አያገኙም። ቀመራዊ ስለሆኑና የእምነት መነፅር ስለሌላቸው የፀበል ይዘት እንደማንኛውም ውሃ የሃይድሮጅን እና የኦክስጅን ውሕድ እንጂ ያለበት መንፈስ እግዚአብሔር አይረዳቸውም። ምክንያቱም ምድራዊ ቤተሙከራን እንጂ መንፈሳዊነትን አያውቁም። መናፍቃኑ ስንሳለም አይተው ድንጋይን ይስማሉ (ይቅር ይበላቸውና) እንደሚሉን መንፈሳዊነት ጎድሏቸው በመንፈስ የማያገለግሉት እነዚህ አገልጋዮችም ‘እግዚአብሔር በገደለው ይሙላ’ የሚልን ንግግር የማያውቁ ከመሆናቸው የተነሳ ሁሉ ነገር በእነርሱ ዝግጅትና ድካም ብቻ የሚሳካ ይመስላቸዋል።

መዝሙር ላይ ተመስጦ የሚባል ነገር አያውቃቸውም። የማን ድምፅ ወጣ? የማን ወረደ? እንዴት ልራመድ እንዴት ላጨብጭብና ሰውን ላስደስተው? ከበሮ አመታቴ ያምር ይሆን ሰው ደስ ብሎት ይሆን? በሚሉና በመሳሰሉት ሐሳቦች ከመጠን በላይ ስለሚዋጡ በመዝሙር ተመስጠው አያውቁም። ግን ደግሞ የቅዱስ ያሬድን የመዝሙር ተመስጦ ታሪክ በደንብ ያውቁታል። ቅዱስ ያሬድ በዐፄ ገብረመስቀል ፊት ሲዘምር ከመመሰጡ የተነሳ ምድራዊን ነገር ሁሉ፣ የራሱንም ሥጋ ጭምር ረስቶ በሕሊናው ሰማየ ሰማያትን አቋርጦ ከመላእክት ጋር ያመሰግን ነበር። እሱ ይቅርና ንጉሡም ተመስጠው በጦር እስኪወጉት ድረስ በመንፈስ ነበሩ። ቅዱስ ያሬድ ንጉሡ በተመስጦ ሲንቀሳቀሱ የያዙትን ጦር እንደመቋሚያ እያንቀሳቀሱ እግሩን ድንገት ቢወጉትም መወጋቱ እንኳን እርሱን ከተመስጦው የመመለስ ኃይል አልነበረውም። በኋላ ዝማሬያቸውን ጨርሰው ዝቅ ቢሉ ምድር ላይ ደም አዩና ነገሩን በዛ ተረዱ። በእርግጥ ጀማሪ አገልጋይ ሁሉ እንዲህ መሆን አለበት አይባልም። እየዘመርን ጉንዳን ስትበላን የምንተረማመስ ሰዎች ጦርን ያህል የቻሉትን ቅዱሳንን እንሁን ማለትም ተገቢ አይደለም። ነገር ግን እነሱን በመምሰል የተመሰጦን ሕይወት፣ የእምነትን ብርታት የመንፈሳዊነትን መዐዛ ለሰውነታችን ማለማመድ የግድ ነው። ጉባኤ ሲዘረጋ፣ ተውኔት ሲሠራ፣ ሲዘመር እና ማንኛውንም መንፈሳዊ አገልግሎት ሲገለገል ቢያንስ ጸሎት ያስፈልጋል።

ከመንፈሳዊነት የራቀ የጉባኤ ድምቀትን አምጥቶ ሰውን ለማስደሰት መጣር ይሁዳን መሆን ነው። መጀመሪያ እግዚአብሔርን ማስደሰት ይቀድማል። እርሱን ደግሞ ካለ እምነትና መንፈሳዊነት ማስደሰት አይቻልም። (ዕብ. 11፥6) እግዚአብሔርን ስናስደስት የእርሱ የሆኑት ሁሉ ይደሰቱብናል። ለዚህ ነው አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ 'መንፈሳዊነት ከተለየው አገልግሎት አገልግሎት የሌለው መንፈሳዊነት ይሻላል' ብለው የተናገሩት።

ቅዱስ ዮሐንስ ሐጺር በተመስጦ ከሚታወቁትና በመንፈሳዊነታቸው ከሚመሰገኑት አገልጋዮች አንዱ ነበሩ። በአንድ ወቅት በአታቸው ውስጥ ሆነው ሥራቸውን እየሠሩ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ በሩ ይንኳኳል። ሄደው ሲከፍቱ አንድ መነኩሴ "አባ ቅርጫት እንዲሰጡኝ ነው የመጣሁት" ይላቸዋል። አባ ዮሐንስም በተመስጦ ውስጥ ስለነበሩ ቅርጫቱን ሊሰጡት ወደ ውስጥ ገቡና ዘንግተውት ያቋረጡትን ምስጋና ቀጠሉ። በር ላይ የቆመው መነኩሴ ቢቆዩበት መልሶ አንኳኳ። አባም በሩን ከፈቱና ምን ነበር አሉት። መነኩሴውም አባ ቅርጫት ብዬዎት ነበርኮ አላቸው። ነገር ግን

አባ ዮሐንስ ሐጺር ወደ ውስጥ ሲገቡ እንደገና ወደ ተመስጦአቸው ተመለሱ። መነኩሴው ሲቆዩበት እንደገና አንኳኳ። አባ ዮሐንስ በሩን ከፈቱና “ምን ነበር?” አሉት። መነኩሴው ጉዳዩን መልሶ ቢያስታውሳቸው አባ ዮሐንስ እጁን አፈፍ አድርገው ወደ በዓታቸው አስገቡትና “ና የፈለግከውን መርጠህ ውሰድ። እኔ ለእንደዚህ አይነቱ ጊዜ የለኝም” አሉት።

አንድ መንፈሳዊ አገልጋይን በመንፈስ እንዳያገለግል ዘወትር የሚያንኳኩበት ጉዳዮች አሉት። ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች፣ ቤተሰባዊ፣ ኅብረተሰባዊ እና ወቅታዊ ጉዳዮች የሥጋ ፍላጎት፣ ወዘተ...ዘወትር በጭንቀት እንጂ በመንፈስ እንዳያገለግል ያንኳኩበታል። በዚህን ጊዜ እንደ አባ ዮሐንስ ሐጺር ፈፅሞ የመርሳት የብቃት ደረጃ ላይ ባይደርስ እንኳን በመንፈሳዊነትና በፀሎት ማሸነፍ መቻል ይጠበቅበታል።

መንፈሳዊ አገልግሎት በመንፈስ መሆን አለበት ስንል ሌላው መርሳት የሌለብን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ‘ሁሉ በአግባቡና በሥርዓት’ መሆን እንዳለበት ነው። (1 ቆሮ 14፡40) እንደ ቤተክርስቲያን ሕግና እንደ እግዚብሔር ቃል ማገልገላችንን መመርመር ያስፈልጋል።

## 2. ሰማያዊ ዋጋን አስቦ ማገልገል

አንድ መንፈሳዊ አገልጋይ ማንኛውንም ምድራዊ ሽልማት አስቦ ማገልገል ከጀመረ ምድራዊውን ዋጋ ሲያጣ አገልግሎቱ ይቆማል። እግዚአብሔርን ሳይሆን እገሌን ብሎ የሚመጣ እገሌ ሲጠፋ ወይም ሲጣላው አገልግሎቱን ያበቃል። እግዚአብሔርን ብሎ የመጣ ግን ቢጣላና ቢሰደብ እንኳን ቢደበደብና ቢገደል እንኳን ‘ስለ ክርስቶስ ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ በናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ’ የሚለውን ቅዱስ መፅናኛ ያስባል። (1 ጴጥ. 4፡14) ሰማያዊ ዋጋን አስቦ የመጣ ሰው ጊዜና ነገሮች ሲመቻቹለት ሳይሆን አመቻችቶ ያገለግላል። ኑሮው ሲሞላለት፣ ሀብት ሲሰፋለት፣ ዘመድ ሲበዛለት ጊዜን ለሰጠ ጌታ ጊዜ አጣሁ ብሎ አይቀርም። የነበረው ከሆነም ቤቱ ሲቀዘቅዝ፣ ድህነት ሲያንቀው፣ ወዳጅ ዘመን ሲያጣ ተማሮ አይጠፋም። የምድራዊ ሁኔታዎች መቀያየር ከአገልግሎት አይለየውም። ይልቁንስ “ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየኛል? መከራ ወይስ ጭንቀት፣ ወይስ ስደት ወይስ ራብ፣ ፣ ወይስ ራቁትነት፣ ወይስ ፍርሃት፣ ወይስ ሰይፍ ነውን? በማለት ፀንቶ ይዘምራል። (ሮሜ 8፡35) ሰማያዊ ዋጋን የሚያስብ አገልጋይ አይበረገግም። የኑሮ ውድነት፣ የመንግሥት መለወጥ፣ የፖሊሲ መቀየር እና ሌሎች ምድራዊ ነገሮች አያስደነግጡትም። ሁሌም ፅኑዕ ነው። የፅናቱ መጠን ይደንቃል። የብርታቱም ልክ

ይገርማል። መመካቱም በእግዚአብሔር ነው።
የይታይልኝ አመል የለበትም። ሰው አየው አላየው ግድ የለውም። እግዚአብሔር እንደሚያየው ያውቃል። በብዙ ድካም የተዘጋጀበት መርሐ ግብር ተሰረዘ ሲባል አያኮርፍም። ገና አገልግል ሲባል 'አቤት ያ ሁሉ ሕዝብ ሲያየኝ' ብሎ ሳይሆን ሰማያዊውን ክፍያ አስቦ ያገለግላል። የሕዝብ አለመብዛት የሚያስጨንቀው ለጥቂት ሰው የተዘጋጀሁትን አቀርባለሁ ብሎ ሳይሆን የቀረውን ሰው ከቤተክርስቲያን መራቅ በማሰብ ነው።
ሰማያዊ ዋጋን ማሰብ አንድን አገልጋይ ከዓለማዊ ሠራተኞች የሚለየው ታላቅ ሀብት ነው። ምድራዊ ሕሊና ያላቸው እግዚአብሔርን ለገንዘብ ማግኛነት ይጠቀሙበታል ሰማያዊ ሕሊና ያላቸው መንፈሳዊያን አገልጋዮች ግን በገንዘብ እግዚአብሔርን ያገለግሉበታል።

3. በትሕትና ማገልገል

ትሕትና ለክርስቲያኖች ከተሰጡ ሀብቶች ሁሉ ውቧ ነች። 'ትሕትናና እግዚአብሔርን መፍራት ባለጠግነት ክብር ሕይወትም ነው።' (ምሳ. 22፡4)። 'እግዚአብሔር ትሑታንን ይወዳል። (ያዕ. 4፡6)። ለስም አጠራሩ ክብር ይሁንና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሱ እንድንማር ካዘዘን ነገሮች አንዱ ትሕትናው ነው። 'ከእኔ ተማሩ እኔ የዋሕ በልቤም ትሑት ነኝ።' (ማቴ. 11፡29)።
ካለ ትሕትና መንፈሳዊ አገልግሎትን መከወን ማለት ፍሬን የበጠሰ (የሌለው) መኪናን መንዳት ማለት ነው። መኪናው ሄዶ ሄዶ እንደሚጋጨው አገልጋዩም ከሆነ አካል ጋር መጋጨቱ አይቀርም። ካለ ትሕትና በትዕቢት አገልግሎ የፀደቀ ቅዱስ በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የለም። እንደውም ትልቁን ክብርና ልዕልና ያገኙት በትሕትና የተጓዙ ቅዱሳን ናቸው። እመቤታችን ድንግል ማርያም ምንም እንኳን በመልአክ እየተመገበች በቅድስና ብታድግም፣ ሴቶች ጌታን የምትወልድ ብለው በሹፈትም ቢሆን ቢጠቁሟትም፤ ቅዱስ ገብርኤል 'ትፀንሲ፣ ትወልዲ' ቢላትም እሷ ግን ያቺ የጌታ እናት በኔ ዘመን ኑራ ምነው ባሪያ በሆንኳት ትል ነበር። መልአኩ ለሦስተኛ ጊዜ በቤተመቅደስ እስኪነግራት እና የጌታ እናትነቷን እስከታውቅ ድረስ ሐሳቧ ይኸው ነበር። ትሑታንን የሚያከብር እግዚብሔርም መልዕልተ ፍጡራን መትሕተ ፈጣሪ አደረጋት። ሙሴንና ኤርሚያስን የመሳሰሉት ቅዱሳንንም ብናነሳ 56 56 56 አይገባኝም፤ አልችልም እያሉ እንደተጋደሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል። 'ወደ ፈርኦን የምሄድ የእስራኤልንም ልጆች ከግብፅ የማወጣ እኔ

ማነኝ' (ዘጸ. 3፡11)። 'ወዮ ጌታ እግዚብሔር እነሆ ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም' (ኤር. 1፡6)። እኔ እያለሁ በማለት ፈንታ እኔ ማነኝ፣ እኔ አውቃለሁ በማለት ፈንታ አላውቅም ብለው ከበሩ።
ጌታ በወንጌል ትሕትናን ለሐዋርያት ሲያስተምር የሚከተለውን ብሏል። 'ከእናንተ ታላቅ የሆነ በመካከላችሁ እንደታናሽ የሚገዛም እንደሚያገለግል ይሁን። በማዕድ የተቀመጠ ወይንስ የሚያገለግል ማናቸው ታላቅ ነው? የተቀመጠው አይደለምን? እኔ ግን በመካከላችሁ እንደሚያገለግል ነኝ'። ሉቃ. 22፡26። መንፈሳዊ አገልግሎት በመሸነፍ ማሸነፍ፣ በመሰደብና በመዋረድ ክብር፣ በመሞት ድል የሚገኝበት የትሕትና ባሕር ነው። ከትሕትና የራቀ አገልጋይም ከባሕር ውስጥ የወጣ አሳ ነው።
ፍሬ የያዘ ዛፍ (ቅርንጫፍ) ዝቅ ይላል ይላሉ አበው። አባ ኤስድሮስ የተባሉ አባት 'ሁል ጊዜ የምትጾም ከሆነ በትዕቢት ራስህን ወደ ላይ አታውጣ፣ ከዚህ የተነሣ ራስህን ከፍ አድርገህ የምትመለከት ከሆነ ግን ሥጋ ብትበላ ይሻላል። ለአንድ ሰው ራሱን በትዕቢት ከመንፋትና ራሱን ከማክበር ሥጋ ቢበላ ይሻለዋልና።" ብለው የትሕትናን ጥቅም አብራርተዋል። አንድ ሌላ አባትም 'ካልበደለና ጻድቅ ነኝ ከሚል ሰው ይልቅ የበደለና ኃጡአተኛነቱን የሚያምን ሰው ይሻለኛል' ብሎ ስለ ትሕትና ገልጿል።
አባ መቃርዮስን በአንድ ወቅት ሰይጣን ተገናኘውና "ካንተ የተነሳ የሚደርስብኝ መከራ ታላቅ ነው፣ ጉዳት ላደርስብህ ስፈልግ አልችልም። ነገር ግን አንተ የምታደርገውን ማንኛውም ነገር እኔም አደርገዋለሁ ያውም ካንተ አብልጬ አደርገዋለሁ። አንተ አብዝተህ ትጾማለህ፣ እኔ ግን ምግብ የሚባል ነገር ፈጽሞ አልበላም፣ አንተ ሌሊት እንቅልፍ በማጣት በትጋት ታድራለህ፣ እኔ ግን ጨርሶም አልተኛም። አንተ እኔን የምትበልጠኝና እኔም እርሱን የምመሰክርልህ በአንድ ነገር ብቻ ነው።" አለው። መቃርዮስም "እርሱ ምንድን ነው?" ሲለው ጋኔኑ "በትሕትና ነው" አለው። ቅዱሱም ይህን የረቀቀና የመጨረሻ ፈተና ለማስወገድ መሬት ላይ ወደቀ፤ ሰይጣኑም ወደ አየር ተኖ ጠፋ።" (ይህ ፈተና ትሑት ነኝ ብሎ እንዲመካ የቀረበ ረቀቂ ፈተና ነበርና)
አንድ መንፈሳዊ አገልጋይ ለአገልግሎቱ ስኬት ትሕትና ያለውን ጠቀሜታ በመረዳት ማገልገል ይጠበቅበታል።

### 4. በፍቅር /በመሥዋዕትነት ማገልገል

ፍቅር ግብሩ መስጠት ነው። የሚሰጡበትን ምክንያት ሳይፈልጉ እንዲሁ መስጠት።

አብ ዓለምን እንዲሁ ከለምክንያት ወዶ አንድያ ልጁን እንደሰጠ። (ዮሐ 3፡16)። መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲህ አይነቱን ሕይወት ይሻል። የመስጠት ሕይወትን። አገልጋዮች የአገልግሎት ፍቅር ሲገባቸው ጊዜያቸውን ባለመሰሰት ይሰጣሉ። ጉልበታቸውን ፣ ገንዘባቸውን፣ እውቀታቸውን በጣም የበረቱትም ሕይወታቸውን ጭምር አሳልፈው ይሰጣሉ።

መንፈሳዊ አገልግሎት የሚታይ፣ የሚጨበጥን ነገር ሰጥተው የማይታይ፣ የማይጨበጥ ፀጋን የሚቀበሉበት የፍቅር/የመስጠት ሕይወት ነው። ስጡ ይሰጣችሁማል (ሉቃ. 6፡ 38) የተባለው ለዚሁ ነው። በዳግም ምፅአቱ ጌታ ጻድቃንን በቀኝ ኃጥአንን በግራ አሰልፎ የሚጠይቀው የፍቅር/የመስጠት ጥያቄን ነው። ተርቤ አብልታችሁኛል? ተጠምቼ አጠጥታችሁኛል?፣....(ማቴ. 25) የፍቅር/የመስጠት ጥያቄዎች ናቸው። ፍቅር የሌለው አገልጋይ የእግዚአብሔር መሆን አይችልም። ኃጢአቱ እንኳን የማይሸፈንለት ምስኪን ነው። በፍቅር የሚያገለግል ግን የኃጢአቱ ብዛት በፍቅር ይሸፈንለታል። (1 ጴጥ 4፡8፣ ምሳ. 10፡12) ካለ ፍቅር እግዚብሔርን ማወቅና ወደእርሱ መቅረብ አይቻልም። ወንጌል የፍቅር ሕግ ናት። ክርስትና የፍቅር ሃይማኖት ናት። እግዚአብሔርም ፍቅር ነው። ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ ምንም የሰመረ አገልግሎት ቢኖርም ካለፍቅር ከንቱ እንደሆነ ያስተማረው። የሰውን ሁሉ ቋንቋ ባውቅ፣ የመላአክትንም ሁሉ ቋንቋ ባውቅ፣ ነገር ግን ፍቅር ከሌለኝ እንደሚጮህ ነሐስ ወይም እንደሚመታ ከበሮ መሆኔ ነው። ትንቢት ብናገር፣ የተሰወረውን ሁሉ፣ ጥበብን ሁሉ ባውቅ፣ ተራራ እስከ ማፍለስ የሚያደርስ ፍጹም እምትም ቢኖረኝ ፍቅር ከሌለኝ ከንቱ ነኝ። ገንዘቤን ሁሉ ለምጽዋት ብሰጥ፣ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል ብሰጥ ነገር ግን ፍቅር ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም።’ 1 ቆሮ. 13፡1-3

ፍቅር የሌለው አገልጋይ መስጠትን አያውቅም። መስጠትን የማያውቅ ደግሞ ጊዜውን፣ ጉልበቱን፣ ዕውቀቱን፣ ገንዘቡን በመለገስ ማገልገል አይችልም። ስለዚህ ፍቅር የሌለው መንፈሳዊ አገልጋይ መሆን አይችልም።

5. በትጋት፣ በጸሎትና በቅንዐት ማገልገል

አንድ መንፈሳዊ አገልጋይ ትጉህ፣ ጸሎተኛና ቅንዓተ ቤተክርስቲያን ያለው መሆን ይገባዋል። ለሰው የከበረ ሀብት ትጋት ነው (ምሳ 12፡27) እንዳለ ጠቢቡ ትጋትን የመሰለ ሀብት ከአገልጋይ ሊለየው አይገባም። ትጋትን ገንዘብ ያደረገ አገልጋይ ለደካማ ጎኖቹ ዘወትር መፍትሔ ያበጃል። አባ ቢሾይ የተባሉ አባት በትጉህ ጸሎተኝነታቸው ይታወቃሉ። በትጋኃ ሌሊት የፀኑ ከመሆናቸው የተነሳ እንቅልፍ

እንዳይጥላቸው ፀጉራቸውን ከዛፍ ቅርንጫፍ ላይ አስረው ይፀልያሉ። እንቅልፋቸውን በርትቶ ዝቅ ሲሉ ፀጉራቸውን ስለሚነጫቸው በርትተው ይፀልዩ ነበር። አባ አርሳንዮስም ለፀሐይ ማታ ጀርባቸውን ሰጥተው ለፀሎት ይቆሙና ጠዋት በምስራቅ በፊት ለፊታቸው ስትወጣ ሥጋቸውን ያሳርፋሉ። በእነዚህ አባቶች ብቃት ደረጃ መገኘት ቢከብድም የእነርሱን ብርታት አርአያ በማድረግ ግን መትጋት ያስፈልጋል።
ሌላው ወሳኝ ነጥብ አንድ አገልጋይ ቅንዓተ ቤተክርስቲያን ሊኖረው የሚገባ መሆኑን ማወቁ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ብዙ መከራና ግፍ ቢደርስበትም 'የቀረውን ነገር ሳልቆጥር ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሐሳብ ነው።' እንዳለው (2ኛ ቆሮ. 11፥28) በዚህ መናፍቃን በበዙበት ዘመን አገልጋዮች ለቤተክርስቲያን የሚቀኑ ሰይፎች መሆን ይገባቸዋል።
ባጠቃላይ መንፈሳዊ አገልግሎትን በመኪና ከመሰልነው እምነትን/መንፈሳዊነትን (መንፈስ ቅዱስ) በመሪ፣ ትሕትናን በፍሬን፣ ሰማያዊ ዋጋን ማሰብ በመስታወት ፍቅርን በቤንዚን/ነዳጅ፣ ትጋትን በጎማው መመሰል እንችላለን። መኪና ካለመሪው አቅጣጫ እንደማይኖረውና ወደ መድረሻው እንደማይሄድ ሁሉ ካለእምነት/መንፈሳዊነት መንፈሳዊ አገልግሎትም እንዲሁ ነው። ካለፍሬን መኪና አደጋ ላይ ይወድቃል ይጋጫል። አገልግሎትም ካለ ትሕትና እንዲሁ ነው። ካለ መስታወት የፊቱን ማየት እንደማይቻል ሰማያዊ ዋጋን ማሰብም የፊቱን በተስፋ እንድናይ ይረዳናል። ካለ ቤንዚን/ነዳጅ መኪና የማይንቀሳቀስ ቆርቆሮ ነው። ካለ ፍቅርም አገልግሎት ከንቱ ድካም ነው። መኪና በጎማው ይሄዳል፣ መንፈሳዊ አገልግሎትም በአገልጋዩ ትጋት ይገፋል።
አገልጋዮችና ለማገልገል የሚፈልጉ መገንዘብ ያለባቸው የመጨረሻው ነጥብ መንፈሳዊ አገልግሎት ከፈተና ርቆ እንደማያውቅ ነው። ከረቂቁ እስከ ግዙፉ ድረስ ሁሉም ፈተና በአገልግሎት ላይ ሊያጋጥም ይችላል። የቤተክርስቲያን ምሥረታዋ በመስቀል ላይ እንደመሆኑ ከፈተና ርቆ በምድር ደልቶት የፀደቀ ቅዱስ የለም። የመንፈሳዊ አገልጋይ ሕይወትም በፈተና የታጀበ ሊሆን ይችላል። አገልጋዩ እየበረታ በሄደ ቁጥር በፈተናው ይበረታል። በዚህን ጊዜ በጸሎት፣ በጾምና በስግደት መጋደል ያስፈልጋል። ከጭስ ለመሸሽ እሳት ውስጥ አይገባምና ተሸንፎ ማገልገልን ማቆም እሳት ውስጥ መውደቅ ነው። ፀጥ ያለ ባሕር ምርጥ ዋናተኛ አያፈራም እንዲሉ የአገልግሎት ባሕር ፀጥ ያለ አለመሆኑን ተገንዝቦ ምርጥ ዋናተኛ ለመሆን መዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ከመንፈሳዊ አገልግሎት በረከት አይለየን።

አገልግሎታችንን ቅዱስ አምላካችን ይባርክልን። አሜን።

Miko ZE Ethiopia

13/ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

ሊቀ ልሣናት ቀሲስ ከፍያለው ጥላሁን

ሥነ ምግባር፡- ማለት ደግነት፣ በጎነት፣ መልካም ጠባይ ማለት ሲሆን ክርስቲያን የሚለው ቃል ሲጨመርበት ደግሞ የተሟላና የተለየ ያደርገዋል። መልካም ጠባይ ማንም ሰው ሊኖረው ይችላል። ነገር ግን የተሟላ ዘላቂና የሁል ጊዜ ሆኖም ለሰማያዊ መንግሥት የሚያበቃው በክርስትና እምነት ሲኖሩ ነው።

ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር፡- በምድር እያለን ሰማያዊ ኑሮ ኖረን ለሰማያዊ መንግሥት የምንበቃበት ሕይወት ነው። ሰውን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን ማስደሰት ነውና። በመሆኑም ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በሚከተሉት ሕግጋት ሊለካ ይችላል።

1. ሕገ እግዚአብሔር

መጀመሪያውና ዋነኛው የክርስቲያን ሥነ ምግባር መለኪያው ቃለ እግዚአብሔር ነው። አንድ ሰው ምናልባትም ሕይወቱ በሰው ፊት ሲታይ የማያስደስት በአፍአ ያለው ጠባዩ እንከን የማይወጣለት ሊሆን ይችላል። በሕገ እግዚአብሔር ተመዝኖ ካላለፈ ዋጋ የለውም በሰው ፊት መልካም ሆኖ የሚታይ ምግባር እግዚአብሔርን ሊያስደስት ያስፈልጋል። “የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርጉ እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች እንጂ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ አትሁኑ።” ፌፌ.6፥6

ፈሪሳውያን ከእነርሱ ውጪ የሆነውን ሁሉ የናቁ ያለእኛ ሕገ እግዚአብሔርን አክባሪ ከእኛም በላይ ጻድቅ የለም ባዮች ነበሩ። ነገር ግን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግብዞችና ሥራቸው ሁሉ ከንቱ እንደሆነ ነገራቸው። እንዲያውም “ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም” ማቴ.5፥20 በማለት ደቀ መዛሙርቱን አስጠነቀቀ። እንዲያውም ከእነርሱ እርሾ /ትምህርት/ እንዲጠበቁ አስጠነቀቃቸው። “ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠንቀቁና ተጠበቁ” ማቴ.16፥6 አለ። ከዚህም ሌላ ብዙ ሠርተናል ሥነ ምግባራችን አስደሳች ነው እያሉ ለመወደስ በኩራት ይቀርቡ የነበሩትን ሁሉ አፍረው እንዲመለሱ አድርጓል። ማቴ.19፤16-22

የንጉሥ ሳዖል ሥራ በራሱ በንጉሡ አሳብ ሲመዘን ምክንያታዊና ትክክልም ነበር።

ነገር ግን እግዚአብሔርን ሊያስደስት አልቻለም። ቃሉን ስላላከበረ ለእርሱም ስላልታዘዘ ንቀኸኛልና ንቄሃለሁ ተባለ። ከንግሥናውም ወረደ። 1 ሳሙ.15፥10-22 “ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም።” ዕብ.11፥6
ክርስቲያን በጉዞው ሁሉ በጭፍን በራሱ እውቀት ብቻ አይመራም። በቃለ እግዚአብሔር ሕይወቱን እየመዘነ ሊራመድ ያስፈልጋል። “በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ ራሳችሁን ፈትኑ።” 2 ቆሮ.13፥5 የክርስትና እምነት እያጸኑና እየጠነከሩ እየበሰሉ የሚጓዙበት ሕይወት ነው። በመሆኑም አንድ ክርስቲያን ከትላንት ዛሬ ከአምና ዘንድሮ አድጐ ጠንክሮ መገኘት አለበት። “ንቁ በሃይማኖት ቁሙ ጐልምሱ ጠንክሩ” 1 ቆሮ.16 በሃይማኖት መጠንከር ሲባል በጊዜውም /በተመቸ ጊዜ/ አለ ጊዜውም /ባልተመቸ ጊዜ/ መጠንከር ይገባል። “በጊዜውም አለ ጊዜውም ጽና።” 2 ጢሞ.4፥2 እንዲል።
ከሰው ሕግ ይልቅ የእግዚአብሔር ሕግ ቅርብ ነው። ከሰው ሕግ መደበቅ መሸሽ ይቻላል። ከእግዚአብሔር ግን ማምለጥ አይችልም። የእያንዳንዱ ሰው ሥራ በእርሱ ዘንድ የተገለጠች ናት። የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍን ማንም አያየኝም ኀጢአት እንሥራ ብላ ለሁለት ዓመታት ባባበለችው ጊዜ ኩፉ.27፥25 እግዚአብሔር ከእርሱ እንደማይለይ እያንዳንዱም ሥራው በፊቱ የተገለጠ እንደሆነ ያመነው ኀጢአትን እንዴት እሠራለሁ በማለት መለሰለት። ዘፍ.39፥9፣ መዝ.138፥2-12
ስለዚህ ክርስቲያናዊ አኗኗራችን መልካም ምግባራችን ትክክለኛ የሚሆነው በእግዚአብሔር ሲመዘን ብቻ ነው። ብልጣሶርን “በሚዛን ተመዝነህ ቀለህ ተገኘህ” ዳን.5፥27 የተባለው ለዚህ ነው። የሰው ልጁ ሕግ ተለዋዋጭና ጊዜያዊ ነው። ሕገ እግዚአብሔር ግን በዘመናት ብዛት የማይሻርና ቋሚ በመሆኑ ምግባራችን ከዚህ አንጻር ሊለካ ያስፈልጋል። “እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ። ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሠላም ነው።” ሮሜ.8፥5-6

## 2. ሕገ ልቡና

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሲፈጥረው ከሌሎች ፍጥረታት በተለየ ሁኔታ የሚመራመር ክፉና በጎውን ለይቶ የሚያውቅ አእምሮ ሰጥቶታል። “ግሩምና ድንቅ ሆኘ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ።” መዝ.139፥10 እንዲል። በተጨማሪም “ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው።”መዝ.118፥105 ብሏል። ሕግ ለሙሴ ከመስጠቱ በፊት ደጋግ አባቶች በዚህ ሕግ እየተመሩ እንደሚገባ ኖረዋል።

የሰው ልጅ ማንም ባያስተምረውና ባይነግረው የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን ያውቃል። "እያንዳንዱ ሰው ባልንጀራውን እያንዳንዱም ወንድሙን እግዚአብሔርን እወቅ ብሎ አያስተምርም ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ያውቁኛልና ይላል እግዚአብሔር።" ኤር.31፥34 ምሳሌ አቤል "ከበጎቹ በኩራትና ከላቡ አቀረበ። እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ ወደ ቃየል እና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም።" ዘፍ.4፥4-5 ሄኖክ "አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም እግዚአብሔር ወስዶታልና።" ዘፍ.5፥24 ኖኅ "ኖኅ ግን በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አገኘ በትውልዱ ጻድቅ ፍጹምም ሰው ነበረ ኖኅ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ።" ዘፍ.6፥9 እነዚህና ሌሎችም በሕገ ልቡና ተመርተው መልካም ተግባር የፈጸሙና እግዚአብሔርም ሥራቸውን የወደደላቸው ናቸው። ዕብ.11፥4-7

የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር በራቀ ቁጥር ግብሩ ወደ እንስሳነት ይለወጥና የሚወቅሰው ኅሊና እንኳን ያጣል። "የሰው ልጅ ክቡር ሆኖ ሳለ አያውቅም እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ።" መዝ.48፥12 ናቡከደነፆር በበደል ላይ በደል በመጨመሩ ለእግዚአብሔር ሕግ አልገዛም በማለቱ ግብሩ ሁሉ የእንስሳ ሆነ። ዳን.4፥32 ስለዚህ ክርስቲያን በመጽሐፍ ከተጻፈነው የእግዚአብሔር ሕግ በተጨማሪ በልቡናው ለተቀረጸው ሕግ ይገዛል። ራሱንም እየመረመረ ይጓዛል አጥፍቶም እንደሆነ ማንም ሳይፈርድበት በራሱ ላይ ይፈርዳል፤ ንስሐ ይገባል የጠፋው ልጅና በጌታ ቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ ለዚህ ምስክር ይሆኑናል። ሉቃ.15፥11-19፣ ሉቃ.23፥41

3. የሰው ሕግ

ይህን በሁለት ከፍሎ መመልከት ይቻላል። የመጀመሪያው የአንድ ሀገር መንግሥት ወይም የሚያስተዳድር አካል ሕዝቡን ለማስተዳደር የሚያወጣው ሕግ ከሆነ ሁለተኛው ደግሞ ኅብረተሰቡ በባሕሉ ትክክል ነው ብሎ የተቀበለውና በወረቀት ያልተጻፈው ሕግ ነው። "በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ" 2 ተሰ.2፥15 እንዲል።

ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ሕግ እንደሚገዛ ሁሉ የሰውንም ሕግ ከእግዚአብሔር ጋር እስከ አላጣላው ድረስ ሊያከብር ይገባል። አንድ ሰው ምንም ብጾም ብጸልይ፣ ለእግዚአብሔር እገዛለሁ ቢል የሚያስተዳድረውን አካልና የኅብረተሰቡን መልካም ባሕል ካፈረሰ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባሩን ጎደሎ ያደርገዋል። በሥራ ቦታ የታዘዘውን ካልፈጸመ፣ የሥራ ሰዓት ካላከበረ፣ በቤተ ክርስቲያን ያለውን ምግባሩን በሌላ ሥፍራ

ካልገለጸው ዋጋ አይኖረውም። ለእግዚአብሔር እንደሚገዛ ሁሉ በሰውም ፊት ያለነቀፋ ሊኖር ያስፈልጋል። “በመጥፎና በጠማማ ትውልድ መካከል ያለነቀፋ የዋሆችም ነውርም የሌለባቸው የእግዚአብሔር ልጆች እንድትሆኑ ሳታንጐራጉሩ ክፉም ሳታስቡ ሁሉን አድርጉ በእነርሱም መካከል የሕይወት ቃል እያቀረባችሁ በዓለም እንደ ብርሃን ትታያላችሁ” ፊል.2፥15

ሐዋርያው ከዚህም በተጨማሪ “ማንም እንዳይነቅፈን እንጠነቀቃለን በእግዚአብሔር ፊት ብቻ ያይደለ ነገር ግን በሰው ፊት ደግሞ መልካም የሆነውን እናስባለን” ብሏል። 2 ቆሮ.8፥20 ይህ ሲባል ኀጢአትም ሲሆን የሰው ሕግ ወይም ባሕል ነውና ሁሉን መፈጸም አለበት ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ያስፈልጋል።

ለምሳሌ ከአንድ በላይ ማግባት፣ ጫት መቃም፣ ዋርሳ መያዝ፣ ባሕል በሆነበት አካባቢ የሚኖር ክርስቲያን ከሰው ጋር ለመኖር በሚል ሰበብ ይህንና ይህን የመሰለ የአረማውያኑን ኑሮ ይኑር ማለት አይደለም። እንዲያውም ክርስቲያን በእንዲህ ዓይነት ሰዎች መካከል ሲኖር የቅድስናን ሕይወት በተግባር በመኖር ማንነቱን ሊገልጥ ያስፈልጋል። “መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።” ማቴ.5፥16

ከዚህ አንጻር ብዙ ወጣቶች ሕገ እግዚአብሔርን ከኑሮአቸው ጋር አጣጥመው መኀዝ ሲከብዳቸው ይታያሉ። በእምነት የጸኑትን ሠለስቱ ደቂቅን፣ ዮሴፍን ሶስናን አይመለከቱም። እንኳን ክርስቲያን የሚለውን ስም የተሸከሙ ሲጠራም የሰሙት የማይመስሉ አሉ። ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በሰውና በእግዚአብሔር ፊት የምንኖረው ኑሮ እንደመሆኑ መጠን የግል መንፈሳዊ ሕይወትና ማኅበራዊ ኑሮ በማለት በሁለት ከፍለን መመልከት እንችላለን።

ሀ. የግል መንፈሳዊ ሕይወት፡-

የግል መንፈሳዊ ሕይወት ማለት እኛ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት የሚኖረን ሕይወት ነው። ይህም ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረን ግንኙነት ይመሠረታል። አንድ ሰው ፍቅሩ እግዚአብሔር ከሆነ ምግባሩ መንፈሳዊ ሕይወቱ ይህንኑ የሚገልጥ ይሆናል። አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረው ሕይወት የጠበቀ ለማድረግ ከሚያስፈልጉት ነገሮች ውስጥ ቃለ እግዚአብሔር፣ ንስሐ፣ ቅዱስ ቁርባን፣ ጸሎት ወሳኝ ነገሮች ናቸው።

ቃለ እግዚአብሔር ለአንድ ክርስቲያን የሕይወት መስመሩን የሚያቃናለት ነው። “ቃልህ ተገኝቷል እኔም በልቸዋለሁ አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ በስምህ

ተጠርቼአለሁና ቃልህ ሐሴትና የልብ ደስታ ሆነኝ።" ኤር.15፥16

ንስሓ ማለት መጸጸት ማለት ነው። የክርስትና ሕይወት የንስሓ ሕይወት ነው። በንስሓ የበደለ ከበደሉ ይነዳል። ኀጢአተኛውም ጻድቅ ይሆናል። ስለዚህ ለግል መንፈሳዊ ሕይወት ሥራችሁን አቅኑ።" ኤር.18፥11 ከንስሐ በኋላ ቅዱስ ቊርባን መቀበል ያስፈልጋል። "የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ ሕይወት የላችሁም።" ዮሐ.6፥53

እንግዲህ ቃሉን ሰምተን ንስሓ ገብተን ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ስንቀበል የግል መንፈሳዊ ሕይወታችን የተስተካከለ ይሆናል። የግል መንፈሳዊ ሕይወት ጽናት ደግሞ ለማኅበራዊ ኑሮአችን ወሳኝ ነውና። "ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ ይህን አሳብ ይህንም አዘውትር። ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ። በእነዚህ ጽና ይህን ብታደርግ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህ።" 1 ጢሞ.4፥15

ለ. ማኅበራዊ ኑሮአችን

ክርስቲያን በማኅበራዊ ኑሮው ከሌሎች ጋር በሠላምና በፍቅር ሊኖር እንዲሁም አልጫውን ዓለም በምግባሩ ሊያጣፍጥ ይገባል። በመሆኑም ክርስቲያን በማኅበራዊ ኑሮ ተሳትፎ ውስጥ ሊይዝ የሚገባቸው ነገሮች አሉ። እነዚህም፡-

ዓላማ፡- ክርስቲያን እንደ ውኃ ላይ ኩበት እየተንሳፈፈ ወንዙ ወደ ሚወርድበት አቅጣጫ አይጓዝም። እንደሚወዛወዝ ዛፍም ወደ ነፈሰበት አያጋድልም። የራሱ የሆነ ውሳጣዊ ዓላማና አቋም አለው። "በምትሄድበት ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል።" ኢያሱ.1፥7 ከዚህ የተነሣ የሚሠራውን በጽናትና በትጋት ይሠራል። የጀመረውን ከፍጻሜ ያደርሳል። በመከራ አይናወጥም። መስሎ ለማደር እንደ ጊዜው አይለወጥም። በዓላማ ስለሚጓዝ ዓላማውን ያሳካል።

ክርስቲያን ምን ዓይነት ዓላማ ሊኖሩት ያስፈልጋል?

መንግሥተ ሰማያትን መውረስ፡- አንድ ክርስቲያን ወደ እግዚአብሔር ቤት የሚመጣው ለጊዜያዊ ችግሩ ብቻ መፍትሔ ለማግኘት አስቦ ሳይሆን ሰማያዊ ክብርና ዋጋ ለማግኘት ነው። "ድንኳን የሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘለዓለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንፃ እንዳለን እናውቃለን። 2 ቆሮ.5፥1

የሚታወቅና ግልጽ ዓላማ፡- ክርስቲያን ያለ ዓላማ በጭፍን አይጓዝም። ሳይታሰብ በድንገት በአጋጣሚ የሚል ነገር በርሱ ዘንድ እምብዛም ቦታ አይኖረውም። የሚታወቅ ግልጽ ዓላማ ኖሮት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንዲሳካለት ይጸልያል። "ሳታቋርጡ

ጸልዩ።" 1 ተሰ.5፥18 ከዚህ አንጻር አንዱን ዓላማው አድርጎ ይጓዛል ጋብቻ ወይም ምንኩስና መካከል ሆኖ አያወላውልም።
ራስን መግለጽ፡- ክርስቲያን በሄደበት ሁሉ ማንነቱን መግለጥ አለበት። በተራራ ላይ ያለች ከተማ መሰወር አትችልም። ይህም ሲባል እኔ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስቲያን ነኝ እያለ በማወጅ ወይም በማስታወቂያ ሳይሆን አኗኗሩ ማንነቱን ይገልጠዋል። ይህም ኑሮው በቤተሰብ፣ በት/ቤት፣ በሥራ ቦታ፣ በአካባቢው ኅብረተሰብ ዘንድ ወዘተ...... መገለጥ አለበት።
ታማኝነት፡- እውነተኛ ክርስቲያን ምሎ የማይከዳ፣ አደራ የማያጠፋ፣ የማያወላውል ለምስክርነት የሚበቃ ነው። ታማኝ ሰው መልካም የሚለውን ይናገራል። የሚናገረውን ይሠራል በሐላፊነት ቢቀመጥ ያለ አድልዎ ወገናዊነት ያስተዳድራል። "በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሀለሁ።" ማቴ.25፥21 ይባልለታል። ታማኝነት ለራስ ታማኝ መሆን ለእግዚአብሔር ሰዎች በመታመን ይገለጣል። ይህም በትዳር፣ በሥራ፣ በተሰጠው ሐላፊነት መታመን አለበት። ምሳሌ ዮሴፍ ዘፍ.39፥9
ፍቅር፡- ክርስቲያናዊ ፍቅር የያዘ ሰው በሰውና በእግዚአብሔር ፍቅር ያለነቀፋ ይኖራል። ፍቅር የክርስቲያንነታችን መገለጫ ነው። አምላክን ከዙፋኑ ያወረደው ራሱንም እስከ ሞት አሳልፎ ለሰው ልጅ እንዲሰጥ ያደረገው ፍቅር ነው። ስለዚህ አንደ ሰው ፍቅር ከሌለው ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር የለውም ማለት ይቻላል። የምናፈቅረው ማንን ነው?
እግዚአብሔርን፡- እግዚአብሔርን ማፍቀር ሲባል እግዚአብሔርንና የእርሱ የሆነውን ሁሉ ማፍቀር ማለት ነው። ከዚህ አንጻር ፍቅረ እግዚአብሔርን በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን።
ትእዛዙን ማክበር፡- እግዚአብሔርን መውደድ ትእዛዛቱን በመፈጸም ይገለጣል። "ትእዛዙ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው።" ዮሐ.14፥21
የእግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ መውደድ ይህን በሦስት ከፍለን መመልከት እንችላለን
2.1. ቅዱሳንን መውደድና ማክበር፡- ቅዱሳን እግዚአብሔር የመረጣቸው ያከበራቸውና የወደዳቸው ናቸው። "የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኗልና አስቀድሞ የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው የጠራቸው እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው ያጸደቃቸው እነዚህን ደግሞ አከበራቸው።" ሮሜ.8፥29 ፍቅረ እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑ ቅዱሳንን በማክበር እንገልጻለን። እንዲህ ዓይነቱ ፍቅር

የትሕትናና የኦርቶዶክሳዊነት ውጤት ነው።

2.2. ሀገርን መውደድ፡- ሀገር የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። አንድ ክርስቲያን እግዚአብሔር በሰጠው ሀገር ሆኖ እርሱን ሊያመሰግን ሀገሩን ሊወድ ግዴታ አለበት። ሀገር ከሌለ ሠላም ካልሆነ እግዚአብሔርን በደስታ ማመስገን አይቻልምና። "ኢየሩሳሌም ሆይ ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ ባላስብሽ ምላሴ በጉሮሮዬ ይጣበቅ ከደስታዬ ሁሉ በላይ ኢየሩሳሌምን ባልወድ።" መዝ.136፥5

2.3. ቤተሰብን መውደድ፡- ክርስቲያን እምነትን፣ ምግባርን፣ ሥርዓትን በመጀመሪያ የሚማረው ከቤተሰቡ ነው። ቤተሰብ የመጀመሪያዎቹ ትምህርት ቤቶች ናቸው። ነቢዩ ሙሴ የእግዚአብሔርን፣ የወገንን፣ የሀገርን ፍቅር የተማረው ከእናቱ ነውና። ወልደው፣ አሳድገው፣ አስተምረው ለትልቅ ደረጃ ያበቁትን ቤተሰቡን ክርስቲያን ሊወድ ይገባዋል። "ስለ ቤተሰቦቹ የማያስብ ማንም ቢኖር ሃይማኖትን የካደ ከማያምን ሰው ይልቅ የከፋ ነው።" 1 ጢሞ.5፥8

3. የሰው ልጆችን ሁሉ ማፍቀር፡- /ፍቅረ ቢጽ/ የሰውን ልጅ ሁሉ ማፍቀሩ ፍቅረ ቢጽ ይባላል። ይህም በሥላሴ አርአያ የተፈጠረውን ሰው ሁሉ መውደድና ማፍቀር ነው። ይህም ኀጥእ ጻድቅ፣ አማኒ መናፍቅ፣ ዘመድ ባዕድ ሳይሉና ሳይለዩ ሁሉን አስተካክሎ መውደድ ነው። ይህም ትእዛዝ ጠላትን እስከመውደድ በመድረስ ነው። "በሰማያት ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙችሁን መርቁ፣ ለሚጠሏችሁ መልካም አድርጉ ስለሚያሳድዷችሁ ጸልዩ።" ማቴ.5፥44

በአጠቃላይ ክርስቲያን ከአለባበሱ ጀምሮ ውጫዊ አቋሙም ሆነ አጠቃላይ ሕይወቱ በማናቸውም ጊዜና ቦታ ሁሉ ክርስቲያንነቱን ሊገልጡ ይገባቸዋል። ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ኖረው ለሰውም ብርሃን ሆኖ እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔር የሆኑትን አስደሰተ የሚባለው ያን ጊዜ ነው። እንግዲህ ክርስቲያን በምድር ሲኖር በግል ሕይወቱም ሆነ በማኅበራዊ ኑሮው ምን መምሰል እንዳለበት ራሱን ከላይ በተገለጸው በሦስቱ ሕግጋት አንጻር እየመረመረ መጓዝ አለበት። በግል ሕይወቱ ዘወትር ንስሐ እየገባ ቅዱስ ቁርባን በመቀበል እየጾመ፣ እየጸለየ፣ እየመጸወተ ሰማያዊ መንግሥትን ተስፋ በማድረግ ይጓዛል። በማኅበራዊ ኑሮውም ደግሞ ሰዎችን በሐዘናቸው ጊዜ ማጽናናት፣ በደስታቸው ተካፋይ መሆን፣ ከቸገራቸው ለችግራቸው ደራሽ በመሆን እውነተኛ ፍቅሩን ሊገልጽ ያስፈልጋል። "የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁል ጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞራለን።" 2 ቆሮ.4፥10

Miko ZE Ethiopia

## 14/ ሕይወት በባዕድ ምድር (፪ጴጥ. ፪፥፰)

የርዕሳችን መነሻ የሆነው በ፪ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ ፪ ላይ የምናገኘው ታሪክ ነው። "ጻድቅ ሎጥም እያየና እየሰማ፣ አብሮአቸውም እየኖረ በክፉ ሥራቸው ዕለት ዕለት ጻድቅት ነፍሱን ያስጨንቃት ነበር።" ፪ጴጥ. ፪፥፰

ሎጥ ኃጢአትን የዕለት ከዕለት ተግባራቸው ካደረጉ ሰዎች ጋር ለመኖር የተገደደው በዘፍ ፲፫ ላይ እንደምናነበው ከአጎቱ ከአብርሃም ጋር ይኖርበት የነበረው ቦታ ስለጠበባቸው በእረኞቻቸው መካከልም እየተፈጠረ የነበረው ጥላቻ ወደ እነርሱ እንዳይጋባ ራቅ ወዳለ ቦታ መሄድ ስለነበረበት ነበር። ለመለያየት ሲወስኑም ለሎጥ እንዲመርጥ ዕድል በተሰጠው ጊዜ የመረጣት ውሃ የሞላባትን ለምለሟን ሰዶምን ነበር። ሎጥ ግን በጎረቤቶቹ መካከል እየኖረ ዕለት ዕለት የሚሠሩትን ሥራ እያየና እየሰማ

ይጨነቅ ነበር። ጎረቤቶቹ ግን ማንኛውንም ኃጢአት ከመስራት ወደ ኋላ የማይሉ ነበሩ። ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልከው የመጡ መላእክትን እንኳን ሳይቀር በግብር ለማወቅ ከሎጥ ጋር ግብግብ ሲገጥሙ በዘፍ ፲፱:፩-፲፩ ላይ እናነባለን።

በተለያየ ምክንያት ከሀገራችን ወጥተን በስደት ሕይወትን ለመግፋት ግድ የሆነብን ሰዎች

ዛሬ ከአባታችን ከሎጥ የምንማረው ብዙ ነገር አለ። ፈተና የክብር ማግኛ መንገድ ነዉ። ስለሆነም ደጋግ አባቶቻችን ፈተና ሲርቅላቸዉ አይወዱም ነበር፤ ከቅዱስ እግዚአብሔር ጋር ለመሆናቸዉ አንዱ ማረጋገጫቸው በፈተና መጎሸማቸዉ ስለሆነ። ጻድቅ ሎጥ አስጸያፊ የሆነ ግብረ ሰዶም በሚፈጸምባት ከተማ እየኖረ ከእግዚአብሔር አልተለየም ነበር፤ ነፍሱን በብዙ ያስጨንቃት ነበር እንጂ። አበ ብዙሃን የተባለ አብርሃም ስለነዚያ ሰዎች ድኅነት ልመና ቢያቀርብም በከተማዋ 10 ደጋግ ሰዎች ባለመገኘታቸዉ ቅዱስ እግዚአብሔር ከተማዋን ሊያጠፋት በወሰነ ጊዜ ከነዚያ ሰዎች ኃጢአት ተሳታፊ ያልነበረ ጻድቅ ሎጥ እና ቤተ ሰዎቹን ለማውጣት መላእክት ተልከዋል።

ጻድቅ ሎጥ በመጀመሪያ የአካባቢዉን ልምላሜ እና ለከብቶቹ ምቹ መሆኑን እንጂ የነዋሪዎቹን ክፋት አልመረመረም። በመሆኑም የነዚያን ሰዎች ገደብ የለሽ የኃጢአት ሕይወት በማየትና በመስማት እየተጨነቀ መኖር ግድ ሆነበት። ለእግዚአብሔር ሰዉ የሰዶም ሰዎች ሕይወት የተጠላ ነዉና። በየአዝማናቱ በክፉ መንገድ የሚጓዘው ሰዉ በቁጥር አያሌ ነው። ቅዱሳን ሰዎች የቅድስና እና የብጽእና ክብር የተቀዳጁት ከነዚህ ሰዎች ጋር እየኖሩ በክፉ ሥራቸው ሳይተባበሩ ራሳቸውን ጠብቀዉ በመኖራቸዉና ፈተናዉን በማሸነፋቸው ነዉ። ሁሉ በደለኛ ነዉ እኔ እንዴት ብቻየን መኖር ይቻለኛል? የሚል አዕምሮ የለባቸዉም። እንዲህስ ቢሆን ጽድቃቸዉ ግዘፍ ነስቶ ባልተናገረ ነበር።

ኖኅ በጽድቁ ዓለምን ኮነነ የተባለዉ ሰብአ ትካት (የጥንት ሰዎች) ሲበድሉ በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸንቶ በመገኘቱ ነዉ። ለሎጥስ የግብረ ሰዶምን አስከፊነት ማን ነገረዉ፣ በዚያን ጊዜ የጽሑፍ ሕግ አልነበረምና። ዛሬ ግብረ ሰዶም በዓለም ተንሰራፍቶ እንዲያዉም በመንግሥታት ሳይቀር ሕግ እየወጣለት ነዉ፤ ወንድ ከወንድ፣ ሴትም ከሴት መጋባት ተጀምሯል። እጅግ የሚገርመዉ በእንስሳቱም እኮ ይሕ ይፈጸማል በማለት የሚናገሩ መኖራቸዉ ነዉ። ዓለም በቴክኖሎጂ፣ በዕዉቀት፣ በስልጣኔ እና በመሳሰሉት መጥቆ ሄዷል እየተባለ እንደገና ሰዉ ራሱን አዋርዶ ከእንስሳት ለመማር መዳዳቱ የጊዜዉን አስከፊነት ፍንትዉ አድርጎ የሚያሳይ ነዉ። ቀነጃጅቱ ራቁታቸዉን ሲሄዱ፣ በየመንገዱ እንደዉሻ ሲላላሱ፣ ዝሙቱንም ያለ ሃፍረት ሲፈጽሙ እነሆ እናያቸዋለን። በአንዳንድ አካባቢዎች ሰዎች ራቁታቸዉን ሆነዉ የሚታዩበት ቦታ የተከለለላቸዉ መሆኑ ይነገራል። ወንድ ከወንድ ጋር ጋብቻ እንዳይከለከል በፍርድ ቤት ቀርበዉ ሲከራከሩ ከተፈጥሮ ሕግ ወጣን ብለዉ ቅንጣት ታክል እንኳን አይደነግጡም። ታዲያ ከሎጥ ዘመን፣ ከሰብአ ትካት የተሻሉት በምን ይሆን? ሰዉ እንስሳትን መምሰል ብቻ አይደለም ከእንስሳትም አንሷል። እንስሳት እና አራዊት እንኳ የየራሳቸዉን ግብር ይዘዉ ይኖራሉ፤ ሰይጣንም እንኳ ስለሚበላዉና ስለሚጠጣዉ ተጨንቆ አያዉቅም። ለዚህም ነዉ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ አንተ ማስተዋል ከሌላቸዉ ዱዳ አራዊት እንስሳት ከሰይጣንም የምታንስ ስለሆነ ምን ብዬ ልጥራህ? እያለ ለመናገር የደረሰዉ።

15/ ምግባር የሃይማኖት ነፍስ ናት።

ምግባር የሃይማኖት ነፍስ ናት።

የእግዚአብሔርን አምላክነት ማመን የግድ ስለሆነ አጋንንትም ያምናሉ ስሙም ሲጠራ ይደነግጣሉ። ነገር ግን ይህ እምነት ቅዱሳን ሊያሰኛቸው አይችልም፤ ክርኩስነትም አያወጣቸውም። ሃይማኖት በምግባር ፍፁም ካልሆነ ሰውን ሊጠቅመውና ሊረዳው አይችልም።

እንደ ታላቁ አባት እንደ አብርሃም ምግባር ከሃይማኖት አስተባብረን እንያዝ። አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ ከዘመድ ከአገር ተለይተህ ውጣ ሲባልም ማመኑን በምግባር (አገሩን ጥሎ በመውጣት) ገለፀ፤ ልጅህን ሰዋልኝ ቢለው እሺ ብሎ ይሰዋ ዘንድ ይስሐቅን አዘጋጀው። ሃይማኖትን በምግባር ገለፃት፤ በምግባር የገለፃት ሃይማኖት ደግሞ አጸደቀችው፥ መጽሐፍ አብርሃም አመነ ጸደቀሞ እንዳለ። ዳግመኛም "ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ" (ያዕቆብ 2:24)

ምግባር የተለያት ሃይማኖት ነፍስ የተለየው ሥጋን ትመስላለች ህይወት አይኖራትምና።

melke tsedik Vs Abreham geber segeber

St. Michael Golden Domed monastery (Ukraine)

Like . MayEyesus Talak

ወንድሜ እኔ ያልኩት አልተጻፈም ነው፤ስለዚህ አንተ አይ ተጽፏል ማለት ትችል ነበር።

ሌላው፤ክርስቲያን የሚጸድቀው በምግባር ሳይሆን በእምነት ነው።ስነምግባር ሃይማኖታዊ ጉዳይ ነው፤ለምሳሌ ፈሪሳውያኖች በስነምግባርና በወግ የላቁ ነበሩ፥ ስላላመኑ ግን አልጸደቁም።

በእርግጥ ሃይማኖት ጥሩ ነገር ነው ፥የዘላለም ህይወት የሚገኘው ግን በክርስቶስ በማመን ብቻ ነው ።ስለዚህ ጌታ ስለ ሃይማኖት አንድም ቦታ አላስተማረም፤ነገርግን እኛ ልማዳችንን መከተል ስለምንፈልግና

በአጥርና ግድግዳ ካለታጠርን በእምነት መኖር ስለማንችል ሃይማኖት የሁላችንም አጀንዳ ነው

ክርስትና ግን ሃይማኖት ሳይሆን እምነት ነው

-ሃይማኖት ሰው ሰራሽ ሲሆን፤እምነት ክእግዚአብሄር በላከው በልጁ ወደ ሰው የመጣ ነው

-ስለዚህ ጌታ የጠየቀውም፤ዳግም በመጣ ጊዜ በምድር ላይ እምነት ያገኝ እንደሆን እንጂ የሰው ልጅ ፍላጎት እየጨመረ ሲሄድ ሃይማኖት እየበዛ እንደሚሄድ ያውቅ

ነበር፤ምክንያቱም ሃይማኖት በሰዎች ፍላጎትና ስምምነት የመጣ ነው።
በመሆኑም ከስነምግባር በፊት እምነትን ልናስተምር ይገባናል፥ውስጡ ጥሩ ከሆነ ውጭው ደግሞ ጥሩ ይሆናል!
Like · Daniel Alemayhu
ስራ ብቻ ያድናል ለማለት አይደለም ለመዳን መሰረቱ እምነት ነዉና ግና ይሄ እምነት በተግባር ሊገለፅ ይገባዋል!!
ተፅፏል ወይ ላልከዉ አዎን ተፅፏል
(ያዕቆብ 2፥17) "... ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው።"
ፃድቁ አባታችን አብርሃምን ማየት እንችላለን
በሐዋርያት ዘንድ የተመሰገነ ቅዱስ ያዕቆብ አብርሃም ይስሐቅን በመሰዊያዉ ፊት ለመስዋእትነት ሲያቀርበዉ በስራ የፀደቀ ይለናል:: በሌላ መልኩ ቅዱስ ጳውሎስ በእምነት የፀደቀ ይለዋለወ:: ነገር ግን ይህን ልንረዳዉ የሚገባዉ አብርሃም ይስሐቅን ከማቅረቡ በፊት አምኗል ይስሐቅም የእምነት ሽልማት ሆኖ ተሰጥቶታል:: በተመሳሳይ ሁኔታ ደግሞ ይስሐቅን በመሰዊያዉ ፊት ሲያቀርበዉ የሚፈለግበትን ስራ ብቻ የሰራ አልነበረም በእምነት ጭምር አደረገዉ እንጂ::
እምነት ከሌለዉ ስራ በራሱ ብቻ ከንቱ ነዉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ መልካም ስራ የተለየዉ እምነት ደግሞ የሞተ ነዉ ምክንይቱም "እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።" ያዕቆብ 2፥19
ማመን በራሱ ብቻ አያድንምና!!

Zerabruk Gebrehiwet
16/ "መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።"
"10 በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ።
11 የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር

ሁሉ ልበሱ።
12 መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር
ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን
ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።
13 ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ
የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ።
14-15 እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፥ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥
በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤
16 በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ
የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤
17 የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል
ነው።
18 በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን
ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤" ኤፌሶን 6: 10-18 —

Miko ZE Ethiopia

17/ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ እወቁ።ያዕ 1፡2

---

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የተዋጀችውና የተመሠረተችው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ ተቀብሎ፣ ሥጋውን ቆርሶ፣ ደሙን አፍስሶ ነው። ሐዋ.2 ዐ፥28። ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን ሲገልጽም “በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።” ብሏል። ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን በደሙ ሲዋጅ ጥንተ ጠላት ዲያቢሎስን ድል ነስቶ፣ ምርኮውን መልሶ፣ ሞትን ደመስሶ በመሆኑ ዲያቢሎስ የድል ነሺውን ቤተ ክርስቲያንና ወደ ነጻነት የተመለሱትን ክርስቲያኖች ዘወትር ይፈትናቸዋል።

ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊው እግዚአብሔር ኃላፊያቱንና መጻእያቱን በገለጸለት ራዕይ ስለ ዲያቢሎስ ፈተና ሲጠቁም “ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስና ሰይጣን

የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ ....ለምድርና ለባሕር ወዮላቸው፤ ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቍጣ ወደ እናንተ ወርዶአልና። ዘንዶውም ወደ ምድር እንደ ተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት።" ዮሐ. ራዕ. 12፥9-17።

ታሪክና መጻሕፍት እንደሚያስረዱት ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ከፈተና ተለይታ አታውቅም። ጌታን የሰቀሉ አይሁድ ደቀመዛሙርቱን በእርሱ ስም እንዳያስተምሩ ለማድረግ በማስፈራራት ብዙ ጥረዋል፤ አስረዋቸዋል፣ ገርፈዋቸዋል፣ አሳደዋቸዋል፣ ገድለዋቸዋል። ሐዋ.ሥ 4፥17-21 ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን በአለት ላይ የተመሠረተችና በመንፈስ ቅዱስ የምትመራ ስለሆነ ሥራዋ አልተቋረጠም፤ ተከታዮቿም አልጠፉም ዕለት ዕለት ይበዛሉ እንጂ። ማቴ. 16፥18

ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ሐዋርያት፣ በዘመነ ሰማእታትና በዘመነ ሊቃውንት እንደጊዜው የተለያየ መከራና ፈተና አሳልፋለች። የቤተ ክርስቲያን ጠላት የሆነው ዲያብሎስ ጥንት በአይሁድ፣ በሮማዊያን ነገሥታት፣ በአህዛብ እያደረ፤ ክርስቲያኖች በሃይማኖታቸው በመጽናታቸውና ቤተ ክርስቲያንን በማገልገላቸው ሰውነታቸው በሰም ተነክሮ በእሳት እንዲቃጠሉ፣ በቁርበት ተጠቅልለው ለአንበሳ እንዲሰጡ፣ በድንጋይ ተወግረው እንዲሞቱ፣ በስለት እንዲቀረደዱ፣ በሰይፍ እንዲቀሉ ያስደርግ ነበር። ክርስቲያኖችም በእምነታቸው እየጸኑ ከሞት የተረፉት፤ በዋሻ በግበበ ምድር እየሆኑ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ሲፈጽሙ ኖረዋል። ጌታ "የሲዖል ደጆች አያናውጧትም" ያላት ቤተ ክርስቲያን እስከ ዓለም ዳርቻ እየሰፋች የመሰረታትን ጌታ እያመሰገነች ትኖራለች። ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷን ለማሳካትና የዲያቢሎስን ሽንገላ ለመቋቋም በተለያዩ የአገልግሎት መስኮች ልጆቿን ታሰማራለች።

ስለዚህ ሐዋርያው ያዕቆብ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ እወቁ። ያዕ.1፡2 እንዳለ ስለ እምነታችንና ስለቤተ ክርስተያናችን የምናደርገውን አገልግሎት ፈታኙ ዲያብሎስ ሊያደናቅፍ ሠራዊቶቹን ቢያሰማራም እግዚአብሔር አምላካችንን ትዕግስትንና ጽናትን እንዲሰጠን ፈተናውንም እንዲያሳልፍልን በጽናት እንለምነው።- እርሱ በሰው ዘንድ የማይቻለውን እንድንችል ማድረግ ያውቅበታልና። ለዚህም የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር ይርዳን።

Miko ZE Ethiopia

18/ ጽድቃችን በእምነት ወይንስ በበጎ ምግባርና ሥራ ፤

አንዳንድ ወገኖቻችን በእምነት ብቻ እንጸድቃለን ሲሉን ሌሎቹ ደግሞ በሥራና በትሩፋት በማለት ዘካ (አሥራት) በመክፈል ሊጸድቁ ሲታገሉ ይስተዋላሉ። በመሆኑንም ቤተ ክርስቲያናችን የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል መሰረት በማድረግ ከእግዚአብሔር ጸጋ በተጨማሪ ስለ ጽድቅ (መዳን) የምታስተምረው እንደሚከተለው ቀርቧል ።

ሃይማኖትና ምግባር ፤

ሃይማኖትና (እምነትን ለማለት) ምግባር ሁለቱ በአንድነት በክርስትና ሕይወት ውስጥ ሲገኙ ድኅነትን እንደሚያሰጡ ቤተ ክርስቲያናችን ታምናለች ፥ ታስተምራለች። ነገር ግን ከሁለቱ እምነት ይቀድማል ፤ መልካም ሥራም ይከተላል ።

እምነት (ለመዳናችን / ለጽድቃችን) መሠረት ናት ፤ ሌሎቹ ግን ሕንጻና ግንብ ናቸው ። መሠረት ሕንፃውን ሁሉ እንደሚሸከም እምነትም ምግባራትን ሁሉ ትይዛለች ማለትም በጎ ምግባር ታሠራለች ። ሕንፃ ያለ መሠረት ሊቆምና ሊታይ እንደማይችል ክርስቲያንም ያለ ምግባር ክርስቲያን መሆን አይችልም ። (ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ) ሃይማኖት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያረጋግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው ። ለአባቶችም የተመሰከረላቸው በዚህ ነውና (ዕብ 11:1-2)። ሃይማኖት የማይታየውን እንደሚታይ አድርጎ ሊያረጋግጥና ሊያስረዳ የሚችለው በምግባር ሲገለጥና ሲጸና ነው ።

ቅዱስ ጳውሎስ "እምነት ተስፋ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም የሚበልጠው ግን ፍቅር ነው።" (1 ቆሮ 13:13) በማለት ለምግባር ከፍተኛ ደረጃ ሰጥቶአል ።

ሐዋርያው ያዕቆብም እምነትና ምግባር በክርስቲያናዊ ሕይወት ውስጥ መነጣጠል እንደሌለባቸው ሲገልጥ ፥ ሥራ የሌለው ሃይማኖት አይጠቅምም ፥ አያድንም ፤ እምነት ፍጹምና ሕያው ሊሆን የሚችለው በሥራ ነው ። ሃይማኖትና ምግባር የሌሉት ሰው ከንቱ ነው ፤ ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ ሃይማኖት የሞተ ነው ብሏል።(ያዕ 2:14:17)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ይቆረጣል ወደ እሳትም

ይጣላል (ማቴ 7:19) ካለ በኋላ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጅ ፤ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት አይገባም ብሎ ፥ መዳን ወይም መንግሥተ ሰማያት መግባት (መጽደቅ) የሚቻለው ፤ ምግባር በሃይማኖት መሠረትነት ላይ ሲጸና ፥ ሃይማኖትም በምግባር ሲገለጥና ሲፈጸም መሆኑን ተናግሮአል ። በዚያ (በፍርድ) ቀን ብዙዎች። ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜም። ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ። (ማቴ 7:20-23 ፤ ሉቃ 3:8)
በፍርድ ቀን ማንም ሰው የሚጠየቀው አምኖ ስለሠራው ሥራ ነው እንጅ ፥ ምግባር ስለሌለው ሃይማኖቱ አይደለም (ማቴ 25:41-45) ። በቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የተነገረውም ፥ ሁሉም እንደየሥራው ዋጋውን ይቀበላል የሚል ነው። (ማቴ 16:27 ፤ ዮሐ 5:28-29 ፤ 2 ቆሮ 5:10 ፤ ራእ 14:13 ፥ 20:12 ፥ 22:12)
ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ምንጭ:- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ፥ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት (1988)

Sekokaw Ermias

19/ መንፈሳዊ ሕይወትህ/ሽ ለውጥ እንዲኖርህ/ሽ:-

1 ኛ የፀሎትን ህይወት ተለማመድ ተጠቀምበትም፣

2 ኛ ከመንፈሳዊ አባቶችና ሊቃውንት መ/ራን ምክርና ትምህርት አትራቅ

3 ኛ ከቅዱሳት መፃህፍት ጋር ያለህን ግንኙነት አዘውትር፣

4 ኛ የምትውልባቸውን ቦታዎች ፥የምታነባቸውን መፃህፍት፥የምትመርጣቸውን ባልጀሮችህን ምረጥ፤ለመንፈሳዊ ህይወትህና ለሌሎች ወንድሞችህና እህቶችህ የሚያሰናክሉ እንዳይሆኑ ተጠንቀቅ፣

5 ኛ የእግዚአብሄር ቤተመቅደስ መሆንህን ዘወትር አትዘንጋ፣

6 ኛ ሃፍረትንና ፍርሃትን አስወግድ፥በራስህ ማስተዋልም አትደገፍ፣

7 ኛ አላዋቂነትህን ተቀበል 'እኔ ብቻ' አትበል ውዳሴ ከንቱንም አትፈልግ፣
8 ኛ ለሰራሃው ሃጢአት ሳትዘገይ ንስሃ ግባ፣
9 ኛ ልበ ደንዳናነትንና አመፀኛነትን ከአንተ አርቃቸው፣
10 ኛ እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ ለመኖርና የቃሉ ሙላት በውስጥህ ኖሮ ከክርስቶስ ጋር መኖርን ተለማመድ በቃሉም ፀንተህ ተገኝ፣
11 ኛ የቅዱሳንን ተጋድሎና ፍቅር በመመልከት እነርሱን ለመምሰል ትጋ፣
12 ኛ ከዚህ በፊት የነበርክበትን የሃጢአት ህይወት ኮንነው
13 ኛ ሰዎችን/ባልንጀራህን አፍቅር ከጥላቻም ራቅ፣
14 ኛ ነገርን ሁሉ ለበጎነው ብለህ ተቀበል። ጌታ ሆይ ይህን እንድናደርግ እርዳን:: አሜን።.

## Andadirgen

20/ ከዓመታት በፊት "የበቁ ባሕታዊ ናቸው" በማለት ሆ ብላችሁ የተከተላችኋቸው ባሕታዊ መጨረሻቸው ምን እንደሆነ አይታችኋል። ዛሬም "ጸጋው የበዛለት ሰባኪ"፣ "ታዋቂ ዘማሪ"፣ "ፈዋሽ አጥማቂ".... እያላችሁ የምትከተሏቸው ሰዎች የነገው መጨረሻቸው ከዚህ የተለየ እንዳልሆነ በእርግጠኝነት መናገር እንችላለን። ደግሞም አይተናል፣ እያየንም ነው።

ምንጊዜም ቢሆን ሰው በሕይወት እስካለ ድረስ ያው ሰው ነው-ያውም ለኃጢአት የተስማማ! እኔ ከዚህ ከዚህ ጋር በተገናኘ ብዙ ማውራት የለብኝም፣ ፍላጎቱም የለኝም። አንድ ነገር ግን መናገር እፈልጋለሁ። እስቲ የቅዱሳኑንና የሰማዕታቱን ገድል ተመልከቱት። ከዚያም የእነርሱን ሕይወት ከእኛ ሕይወት ጋር አነፃፅሩት። እኔ በጾም በጸሎት የምትጋ ከሆንኩ፣ በምክረ ካህን የምመራ ከሆነ፣ ምሥጢራትን የምካፈል ከሆነና የተስተካከለ መንፈሳዊ ካለኝ ሰይጣን እኔ ዘንድ ምን ይሠራል??? እንዳውም የአመንዝራነት መገለጫ የሆነውን ተአምርን በመፈለግና ሰይጣንን ለማስወጣት በሚል ሰበብ ሌላ የርኩስ መንፈስ መቀበል እንዳይመጣ እፈራለሁ።

ወደ ልባችን እንመለስ-መንፈሳዊ ሕይወት በቴፎዞ (በድጋፍ) አይጸናም። እውነተኛውን ክርስትና ጠንቅቀን እንወቀው። ነገሮችን በቃለ እግዚአብሔር ሚዛንነት እንመዝናቸው። በጾም፣ በጸሎት፣ በምጽዋት እንትጋ፣ ምሥጢራትን እንሳተፍ፣ ተጋድሏአቸውን የፈጸሙትን አባቶቻችንን አብነት እናድርግ፣ ገድላቸውን

እንመልከት። "የጸናውን አስቡ" ነው ያለው ሐዋርያው። ዕብ 12፥3። መፍትሄ ይሄ ብቻ ነው። ነገር ግን ሰዎችን መከተሉና ከመንፈሳዊ ተጋድሎ በመራቅ ደረቴ ይቅላ፣ ሆዴ ይሙላ እያሉ ዝም ብሎ ያለ ዕውቀት በስሜት መነዳቱ (የኔታ እንደሚሉት) እንኳን ለሃይማኖተኛ ሰው ለስፖርተኛም አይጠቅምም።
ከቀድሞ ጀማል ሀሰን አሊ

## 21/ የስነልቦና ትምህርቶች ,አነቃቂ ታሪኮች

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ስኬት ትክክለኛ አመለካከት እንዲኖረን ያበረታታናል። ስኬት ጥቂት ዕድለኛ ሰዎች ብቻ የሚያገኙት ነገር እንደሆነ አያስተምርም። በሌላ በኩል ደግሞ በተረት መጻሕፍት ላይ የሚንጸባረቀውን ‘ልብህ የሚልህን ከተከተልክ የምትፈልገውን ሁሉ ታገኛለህ’ የሚለውን ሐሳብ አይደግፍም። ልጆች ከሕፃንነታቸው ጀምሮ የሚነገራቸው ይህ ሐሳብ ብዙ ጊዜ እውን ስለማይሆን ውሎ አድሮ ለብስጭት ሊዳረጉ ይችላሉ።
እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ማንኛውም ሰው እውነተኛ ስኬት ሊያገኝ ይችላል፤ ይሁንና ጥረት ማድረግ አለበት። ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያዎች እንመልከት፦
መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?
“ገንዘብን የሚወድ፣ ገንዘብ አይበቃውም፤ ብልጽግናም የሚወድ፣ በትርፉ አይረካም።”— መክብብ 5:10
ይህ ምን ማለት ነው? ሀብትና ንብረትን በማካበት ላይ ያተኮረ ሕይወት እርካታ ለማግኘት ዋስትና አይሆንም። እንዲያውም ውጤቱ የተገላቢጦሽ ሊሆን ይችላል። ዶክተር ጂን ትዌንጂ የተባለች አንዲት ጸሐፊ ጀነሬሽን ሚ
በተባለ መጽሐፏ ላይ እንዲህ ብላለች፦ “በሕይወታቸው ውስጥ ለገንዘብ ዋነኛ ቦታ የሚሰጡ ሰዎች ከሌሎች ጋር ጥሩ ዝምድና መመሥረትን ከፍ አድርገው ከሚመለከቱ ሰዎች ጋር ሲነጻጸሩ የበለጠ ጭንቀትና ውጥረት ይሰማቸዋል። . . . በርካታ ጥናቶች ገንዘብ ደስታ ሊያስገኝ እንደማይችል አረጋግጠዋል፤ መሠረታዊ ነገሮችን ለማግኘት የሚበቃ ገቢ እስካላችሁ ድረስ የገቢያችሁ መጠን በሚኖራችሁ እርካታ ላይ ያን ያህል ለውጥ አይኖረውም።”
ምን ማድረግ ትችላለህ? ሀብትና ንብረት ከማካበት የተሻለ እርካታ የሚያስገኝ ግብ

አውጣ። ኢየሱስ “አንድ ሰው ሀብታም ቢሆንም እንኳ ሕይወቱ በንብረቱ ላይ የተመካ ስላልሆነ ተጠንቀቁ፤ ከመጎምጀትም ሁሉ ተጠበቁ” ብሏል።—ሉቃስ 12:15
መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?
“ትዕቢት ጥፋትን፣ የእብሪት መንፈስም ውድቀትን ትቀድማለች።”— ምሳሌ 16:18
ይህ ምን ማለት ነው? ከፍ ያለ ቦታ ለማግኘት መቋመጥ እውነተኛ ስኬት ለማግኘት አይረዳህም። እንዲያውም
ጉድ ቱ ግሬት የተባለው መጽሐፍ ለረጅም ጊዜ ስኬታማ ስለሆኑ የድርጅት ኃላፊዎች ሲናገር “ትሑት፣ ልታይ ልታይ የማይሉ እንዲሁም የተለየ ትኩረት እንዲሰጣቸው የማይፈልጉ ናቸው” ብሏል። አክሎም “በአንጻሩ ደግሞ ጥሩ የድርጅት ኃላፊ ሆነው ካልተገኙት ሰዎች መካከል ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት ራሳቸውን ከልክ በላይ ከፍ አድርገው ስለሚመለከቱ ለድርጅታቸው ውድቀት ወይም እድገት አለማግኘት ምክንያት ሆነዋል” ብሏል። ከዚህ ምን ትምህርት እናገኛለን? ራስን ከፍ አድርጎ መመልከት ከስኬት ይልቅ ውድቀት ያስከትላል።
ምን ማድረግ ትችላለህ? ለራስህ ክብርና ማዕረግ ከመፈለግ ይልቅ ትሕትናን አዳብር። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው “አንድ ሰው ራሱን ከፍ አድርጎ የሚመለከትበት ምንም ነገር ሳይኖረው ራሱን ከፍ አድርጎ የሚመለከት ከሆነ ራሱን እያታለለ ነው።” ይህ ደግሞ ስኬት ሊባል አይችልም።— ገላትያ 6:3
መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?
“ሰው . . . ተግቶ በመሥራት እርካታ ከማግኘት የሚሻለው ነገር የለም።”—
መክብብ 2:24 NW
ይህ ምን ማለት ነው? ጥሩ የሥራ ባሕል ካዳበርክ ሥራህን ይበልጥ ትወደዋለህ። ዶክተር ማደሊን ለቫይን
ቲች ዩር ችልድረን ዌል በተባለ መጽሐፋቸው ላይ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፦ “በአንድ ነገር ስኬት እንዳገኘን የሚሰማን ያንን ነገር ጥሩ አድርገን ማከናወን ስንችል ነው፤ አንድን ነገር ጥሩ አድርጎ የመሥራት ችሎታ የሚገኘው ደግሞ በጥረትና ተስፋ ባለመቁረጥ ነው።” ይህ ደግሞ አልፎ አልፎ ባይሳካልህም እንኳ ሁኔታውን ተቋቁመህ ማለፍን ይጠይቃል።
ምን ማድረግ ትችላለህ? በሥራህ የተዋጣልህ እንድትሆን በርትተህ ሥራ፤ እንዲሁም

እንቅፋት ሲያጋጥምህ ተስፋ አትቁረጥ። ልጆች ካሉህ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በራሳቸው እንዲወጡ (ዕድሜያቸውንና አቅማቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት) አጋጣሚ ስጣቸው። የሚያጋጥማቸውን ችግር በሙሉ ጣልቃ ገብተህ ለመፍታት አትቸኩል። ልጆች በሕይወታቸው እውነተኛ እርካታ የሚኖራቸው እንዲሁም አዋቂ ሲሆኑ የሚጠቅማቸውን ሥልጠና የሚያገኙት ችግሮችን ተቋቁሞ የማለፍ ችሎታ ካዳበሩ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

“በሕይወት ያለ ውሻ ከሞተ አንበሳ ይሻላል።”— መክብብ 9:4

ይህ ምን ማለት ነው? ራስህን ለማስተዳደር የምትሠራው ሥራ የሕይወትህ አንድ ክፍል እንጂ መላው

ሕይወትህ መሆን የለበትም። እውነቱን ለመናገር፣ ጤንነትህን ወይም የቤተሰብህን አክብሮት አጥተህ በሥራህ ትልቅ ደረጃ ላይ ብትደርስ ስኬታማ እንደሆንክ ሊሰማህ ይችላል? ለሥራቸው፣ ለጤንነታቸውና ለቤተሰብ ሕይወታቸው ተገቢውን ቦታ የሚሰጡ ሰዎች እውነተኛ ስኬት ያገኛሉ።

ምን ማድረግ ትችላለህ? ራስህን ተንከባከብ። በቂ እረፍት አድርግ። ጤንነትን፣ ቤተሰብንና ወዳጆችን ሠውቶ ሙሉ በሙሉ በሥራ በመጠመድ የሚገኘው ጥቅም ከንቱ ነው፤ ምክንያቱም ይህ እውነተኛ ያልሆነ ስኬት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

“በመንፈሳዊ ድሆች መሆናቸውን የሚያውቁ ደስተኞች ናቸው።”—

ማቴዎስ 5:3

ይህ ምን ማለት ነው? መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናትና በውስጡ የሚገኙትን መመሪያዎች ሥራ ላይ ማዋል ለእውነተኛ ስኬት አስፈላጊ ነው። እንዲያውም በሚሊዮን የሚቆጠሩ የይሖዋ ምሥክሮች ለመንፈሳዊ ነገሮች ቅድሚያ መስጠታቸው ስለ ቁሳዊ ነገሮች ብዙ እንዳይጨነቁ እንደረዳቸው ተገንዝበዋል።— ማቴዎስ 6:31-33

ኦርቶዶክስ መልስ አላት/Orthodox Have An Answer

መንፈሳዊ ተጋድሎ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን::

22/ ▶1.መንፈሳዊ ተጋድሎ ማለት ምን ማለት ነው?

መንፈሳዊ ተጋድሎ ማለት - አንድ ሰው የሚያምንበትን እምነት፣ የሚመራበትን ሕግ፣ የሚያልመውን ተስፋ እና የሚወደውን ነገር ተከትሎ ከግቡ ለመድረስ ማድረግ ያለበትን በማድረግ÷ ማድረግ የሌለበትን በመተው በነፃ ፈቃዱ ወስኖ፥ በሙሉ ልቡናው፥ በሙሉ ኃይሉ የሚያደርገው የውስጥና የውጭ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ፥ ጥረትና ትግል ነው።

ሀ. ከፈቃደ ሥጋ ጋር የሚደረግ ውጊያ ነው።

ሰው በዚህ ዓለም በተሰጠው ዘመኑ ራሱን ለፈጣሪው ለማስገዛት ከራሱ ጋር ብርቱ ተጋድሎ ማድረግ ግድ ይለዋል። ቅዱስ ጳውሎስ <<ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛል፤ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ። ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም>> ብሎ የገለጸው ይህንን በሰው ሕይወት ውስጥ ያለውን የማያቋርጥ ጦርነት ነው። (ገላ 5፥12) ታላቁ አባት ኢዮብም <<በምድር ላይ የሰው ሕይወት ብርቱ ሰልፍ አይደለምን ?>> በማለት ሰው ጽኑ ጦርነት የሚካሄድበት የጦር ሜዳ መሆኑን ገልጿአል። ይህም ጦርነት በተወሰነ ጊዜ ተነሥቶ የሚጠፋ ሳይሆን በሰው ዘመን ሁሉ የሚኖርና የዕድሜ ልክ ትግል ነው። ይህን የሥጋና የነፍስ ጦርነት በነፍስ አሸናፊነት ማጠናቀቅና ፈቃደ ሥጋን ድል አድርጎ ለፈቃደ ነፍስ ማስገዛት ይገባል።

ይህ ሲባል ግን ሥጋ ርኩስ ነው፤ ሥጋ መጥፋትና መወገድ አለበት ማለት አይደለም። ሥጋ በራሱ ርኩስ አይደለምና፤ ምክንያቱም ሥጋ የተፈጠረው በራሱ በእግዚአብሔር ነው። አምላካችን ደግሞ ርኩስ ነገር አይፈጥርም። ሰውን (ሰው የነፍስና የሥጋ ተዋሕዶ ውጤት ነው) ከፈጠረ በኋላ <<ያደረገውን ሁሉ አየ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ።>> ተብሏል። (ዘፍ 1፥31) ሥጋ ርኩስ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ወልድ (ቃል) <<ሥጋ ሆነ>> ባልተባለ ነበር። (ዮሐ 1፥14) አዳምና ሔዋን ከኃጢአት በንጽሕና ይኖሩ ነበር። <<አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ፣ አይተፋፈሩም ነበር>> እንዲል (ዘፍ 2፥25) ህፃናት፣ ልጆች ሰውነት አላቸው ነገር ግን የኃጢአት ምኞት የላቸውም።

ስለዚህ ፈቃደ ሥጋን መዋጋት ማለት ሥጋን ማጥፋት ወይም ደግሞ ተፈጥሮአዊና ንጹህ የሆነ የሥጋን ፈቃድ ማስወገድ ማለት ሳይሆን፣ ኃጢአትን በማየት፣ በመስማት፣ በመለማመድ ያደገውን÷ ወደ ኃጢአት ያዘነበለውን ፈቃዳችንን መጐሰም/መግራት ማለት ነው። ይህ ፈቃድ (ኃጢአት) ሥጋን በመጠቀም ይሠራል÷ ሥጋን ከነፍስ ቁጥጥር ውጭ እንዲሆን ያደርገዋል።

የሰው ሥጋዊ ባሕርዩ ምግብ ሲያጣ ይራባል፣ ይደክማል፣ ሥራ መሥራት ይሳነዋል። ሲሰጡት ደግሞ ኃጢአትን ተለማምዷልና ሌላ ፈቃድ በማምጣት ጠላት ሆኖ ይፈትነዋል። <<ያዕቆብ በላ፣ ጠገበ፣ ወፈረ፣ ደነደነ፣ ሰባ፣ የፈጠረውንም እግዚአብሔርን ተወ፣ የመድኃኒቱንም አምላክ ናቀ። (ዘዳ 32፥15)
ሰውነት የሚፈልገውን ሁሉ እንደ ልቡ ካገኘና ያለ ገደብ የሚቀለብ ከሆነ ወደ ኃጢአት ለመገስገስ የተዘጋጀ መርከብ ነው። ሰውነት በተመቸውና ፈቃዱን ለመፈጸም ኃይል ባገኘ ጊዜ ነፍስ እየደከመች ትሄዳለች። በሌላ በኩል ደግሞ ሰውነት ፈጽሞ ከደከመና ከዛለ ሥራ መሥራት ያስቸግራል። ስለዚህ ሐዋርያው <<ሰውነቴን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ>> እንዳለ። በአግባቡ ሊያዝና ሊገራ ይገባዋል። (1ኛ ቆሮ 9፥27) በአጠቃላይ ቅዱስ ጳውሎስ <<ወንድሞች ሆይ ዕዳ አለብን እንደ ሥጋ ፈቃድ ግን እንኖር ዘንድ ለሥጋ አይደለም። እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና፤ በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ>> እንዳለ ከፈቃደ ሥጋ ጋር በመጋደል ፈቃደ ሥጋችንን ለፈቃደ ነፍስ ማስገዛት ይገባናል።
ለ. ከርኩሳን መናፍስት ጋር የሚደረግ ጦርነት ነው።
ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ <<መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር እንጂ>> እንዳለ መንፈሳዊ ተጋድሎ ማለት ሰው ከሰው ጋር በመጣላት የሚያደርገው ትግል ሳይሆን ጥንተ ጠላታችን ከተባለው በእባብ ወይም በዘንዶ ከተመሰለው ዲያብሎስና ከእርሱ ጋር ካሉት ሠራዊቱና መልእክተኞቹ ጋር የሚደረግ ጦርነት ነው። (ኤፌ 6፥12)
ከአዳምና ከሔዋን ከልጆቻቸውም ከቃየን ጀምሮ ሰይጣን የሰው ልጆችን ዘወትር ይዋጋል፤ ከዘላለም የሞት ፍርድ ሥር ሊጥል ይሠራል። በዚህም ውጊያው ከነቢያት ፤ከሐዋርያት ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ካደረባቸው ሰዎች እንኳ ሳይቀር ብዙዎችን ጥሏል።
ዛሬም በገዛ ባሕርያችን የሚገኘውን ፈቃደ ሥጋ በመጠቀም፣ የራሱን በመጨመርና የተለያዩ ፈተናዎችን በማቀናበር ይዋጋናል። ቅዱስ ጴጥሮስ <<ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና>> በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት።>> እንዳለ ጠላት ዲያብሎስ ክርስቲያኖችን በኃጢአትና ሞት ሊውጥ ዘወትር ይተጋል። ማንም ሰው ደግሞ ከዚህ ፈተናና ውጊያ ሊያመልጥ አይችልም፤ ስለዚህ ሐዋርያት <<በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት>>፣ <<የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ

እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።>> እንዳሉን የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ለብሰን ልንዋጋው ይገባል። (1ኛ ጴጥ 5፥8-9፣ኤፌ 6፥11)

ሐ. የሚመጣውን ዓለም ደስታ ተስፋ እያደረጉ ብቻ በዚህ ዓለም ሕይወት ከደስታ ውጪ መሆን ማለት አይደለም።

ደስታ በራሷ የቤተ ክርስቲያን መገለጫ የሆነች፤ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የተሰጠች፤ ንጹሕ ፈርጥ ነች። (ገላ 5፥22)

እውነት ነው፤ በዚህ ዓለም ስንኖር መከራ አለብን። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀሉን ተሸክመን እንድንከተለው አዞናል። እያንዳንዱ ክርስቲያን በዚህ ምድር ላይ እስካለ ድረስ ከጨለማው ዓለም ገዢ ከዲያብሎስና ከሠራዊቱ የሚመጣ ልዩ ልዩ ፈተናና ከሥጋችንም ባሕርይ ከሚገኘው ክፉ ምኞትና ርኩሰት ሥራ እንዲሁም ከሌሎቹ የኃጢአትና የፈተና ዓይነቶች ጋር በማያቋርጥ እልህ አስጨራሽ በሆነ ትግል ውስጥ መኖሩ የግድ ነው። መከራና ስቃይ፣ ትግልና ጦርነት የሌለበት በዘለዓለማዊ ደስታ ብቻ የሚኖርበት ሕይወት በሚመጣው ዓለም የሚገኝ ነው።

በዚህ ምድር በጉዞ ላይ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ጉዞዋን ጨርሳ ድል ከነሱት አባላቷ ጋር አንድ እስክትሆን ድረስ መከራው፣ እንቅፋቱ፣ መሰደዱ፣ መራቡ፣ መጠማቱ የግድ ነው። <<ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል።>> እንዲል (ሐዋ 14፥22)

ይህ ሲባል ግን በዚህ ዓለም የሚኖሩ ክርስቲያኖች ከደስታ የተራቆቱ ዘወትር በኀዘንና በስቃይ ብቻ የሚኖሩ ናቸው ማለት አይደለም። ክርስቲያኖች የሚለዩትና ዘወትር ለመለየት ጥረት የሚያደርጉት የውሸት ከሆነው ኃጢአት (ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንአት፣ ቁጣ፣ አድመኝነት፣ መለየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ ይህንም የሚመስል) ከሚገኘው ደስታ እንጂ ከእውነተኛውና ከሰማያዊው ደስታ አይደለም።

መንፈሳዊ ተጋድሎ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነትና ረድኤት መንፈስ ቅዱስ መሪና አስተማሪ፣ የሚያነቃቃና የሚያጽናና፣ የሚያርምና የሚገሥጽ፣ የሚረዳና የሚያጸና፣ በመሆን ስለ ክርስቶስ በክርስቶስ ጸጋ የሚከናወን በመሆኑ መከራንና ስቃይን በሚያስረሳ እውነተኛ ደስታና ሰላም የተሞላ ሕይወት ነው።

ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ ሲላስ ስለ ክርስቶስ በማስተማራቸው ምክንያት ገዢዎች ልብሳቸውን ገፈው በበትር እንዲመቱ አዘዙ በበትር ከመቷቸውም በኋላ በወኅኒ ቤት ጣሏቸው እነርሱ ግን ከጀርባቸው ደም እየፈሰሰ በመንፈቀ ሌሊት እንኳን

እግዚአብሔርን በመዝሙር ያመሰግኑ ነበር። እውነተኛውና ሰማያዊው ደስታ በልቡናቸው ሞልቶ ነበርና። (ሐዋ 16፥22-25)

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሐዋርያት እንዲህ ይለናል << ሐዋርያትንም ወደ እነርሱ ጠርተው ገረፏቸው በኢየሱስም ስም እንዳይናገሩ አዝዘው ፈቷቸው። እነርሱም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለተቆጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ።>>(ሐዋ 5፥40-41)

ቅዱስ ዮሐንስ ካሲያን የተባለው አባት በተጋድሎ በግብጽ በረሃ ውስጥ ይኖሩ ስለነበሩት መነኰሳት ሲናገር << እነዚህ ምድራዊ መላእክት ናቸው፤ የግብጽን በረሀዎች በደስታ ወደ ተሞላ መዝሙርና እግዚአብሔርን የማመስገኛ ገነትነት ለውጠዋልና>> ብሏል።

በአጠቃላይ መንፈሳዊ ተጋድሎ ማለት ከተድላ ሥጋ፣ በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ በመሸሽ ሰማያዊና እውነተኝ በሆነ ሰላምና ደስታ ውስጥ መኖር ይህንንም ለማግኘት መጋደል ማለት ነው።

2.መንፈሳዊ ተጋድሎ ዓላማው ምንድነው?

ሀ. የድል አክሊል (የዘለዓለም ሕይወት) ለመቀበል

እግዚአብሔር አምላካችን ሰዎች ነፃ ፈቃዳቸውን ተጠቅመው ከአምላካቸው ጋር መኖር ከመረጡ ሊሰጣቸው ያዘጋጀው ከመነገርና ከመታሰብ በላይ የሆነ የዘለዓለም ሕይወት አለ። የሰው ልጅ ሕሊናዊ ነፃ ፈቃዱ ደግሞ ከአዳምና ከሔዋን ውድቀት በኋላ በየጊዜው እየደከመና ወደ ኃጢአት እያዘነበለ መጥቷል። ከዚህ በተጨማሪ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ዘንድ ክብሮ ባየ ጊዜ ከአባቶቻችን ጀምሮ ዘወትር የሚቀና ክፉ ጠላትም (ዲያብሎስ) አለን፤ ባገኘው አጋጣሚ ስንፍናችንንና ድካማችንን እየተከተለ እነዚህንም በመጠቀም ዘወትር ከአምላካችን ሊለየን እንደሚተጋም ከላይ ተመልክተናል።

ሽልማት፣ አክሊል የሚሰጠው ደግሞ ማሸነፍ ለሚችል ጎበዝ ሰው ነው። ሰነፍና ቸልተኛ ሰው ግን ሊሸለም አይገባውም አንድ ሰው ጎበዝ ወይም ሰነፍ መሆኑ የሚታወቀው ደግሞ በፊቱ ያጋጠመውን ውድድር ወይም ፈተናና መከራ ማሸነፍና ማለፍ ሲችል ብቻ ነው።

ስለዚህ የመንፈሳዊ ተጋድሎ ዓላማ በገዛ ባሕርያችን ያለን መጥፎ የኃጢአት ዝንባሌና ጠላታችን ዲያብሎስ የሚያመጣብንን ፈተናና ሸንገላ ከእግዚአብሔር ርዳታና ቸርነት ጋር ሕሊናን በማንቃት፣ ራስን በመግዛትና ጠንክሮ በመጋደል

አምላካችን ያዘጋጀልንን የድል አክሊል የዘላለም ሕይወትን መቀበል ነው። << የተጠራህለትን የዘለዓለም ሕይወት ትቀበል ዘንድ መልካሙን የሃይማኖት ገድል ተጋደል>> እንዲል (1ኛ ጢሞ 6፥12) ሐዋርያቅ ቅዱስ ጳውሎስ ብዙ መከራዎችን አልፎ ገድሉን በድል አድራጊነት ሲፈጽም << መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፤ ሩጫዬን ጨርሻለሁ፤ ሃይማኖቴንም ጠብቄያለሁ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፤ ይህም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፤ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱ ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።>> ብሏል ( 2ኛ ጢሞ 4፥7-8)

ለ. ለመንፈሳዊ እድገት

ክርስቲያናዊ ሕይወታችን ለፍሬ የሚበቃው የድል አክሊልን መቀዳጀት የምንችለው የማያቋርጥ (የማይቆም) መንፈሳዊ ዕድገት ሲኖረን ነው። በጥምቀት ያገኘነው አዲሱ ሕይወታችን ዘወትር ማደግ ይኖርበታል። ክርስቲያናዊ ሕይወታችን በዛፍ ተክል ይመሰላል። ከችግኝ ማፍላት ጀምሮ ፍሬ እስከሚያፈራለት ጊዜ ድረስ ያለው ድካም ቀላል አይደለም። የዛፉ ችግኝ እንዲያበቅል፣ እንዲለመልም፣ እንዲያብብና እንዲያፈራ አትክልተኛው ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፤ በየጊዜው ውሃ ማጠጣት፣ ማረምና መኰትኰት፣ ፀረ ዕፅዋትና ፀረ ሕይወት የሆኑ በሽታዎችን መከላከል ያስፈልጋል። እንደዚሁ ክርስቲያናዊ ሕይወታችን አድጎ ለፍሬ እስኪበቃ ድረስ ዕለተ ዕለት ጠንክረን በትዕግሥት መሥራት በመንፈሳዊ ተጋድሎ መጽናት ይገባል። የመንፈሳዊ ተጋድሎም ዓላማው መንፈሳዊ ሕይወታችንን የሚያቀጭጩ ከጸጋ እግዚአብሔርም የሚያራቁቱ ኃጢአትና የዲያብሎስ ፈተናን በመቃወም መንፈሳዊ ምግቦችንም በመመገብ አዲሱ ሕይወታችንን ማሳደግ ነው።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

23/ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ልጆች የተሀድሶን አላማ እንቃወማለን !!!!የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ልጆች የተሀድሶን አላ

"በወንጌልም የተሰበከላችሁ ቃል ይህ ነው።" 1ጴጥ.1:25

ኢየሱስ ክርስቶስ

.....................................

=እግዚአብሔር ነው:: ዮሐ.1:1

=አምላክ ነው:: 1 ዮሐ.5:20 ሮሜ.9:5 ቆላ.1:15
=ፈራጅ ነው:: ዮሐ.5:22 ሮሜ.14:10
=ፈጣሪ ነው:: ዮሐ.1:3 ቆላ.1:15 ኤፌ.2:10
=የዓለም መድኃኒት ነው:: ዮሐ.4:42 ሉቃ.2:11
=የዓለም ብርሃን ነው:: ዮሐ.1:9 ዮሐ. 8:12
=እውነተኛ ሰላም ነው:: ዮሐ.14:27 ኤፌ.2:17 ዮሐ.20:19
ድንግል ማርያም
…………………………………
=ክብር ይገባታል:: ሉቃ.1:49 ሉቃ.1:43 ራእ.12:1
=ዘላለማዊት ድንግል ናት:: ኢሳ.7:14 ሕዝ.44:1
=የጌታ እናት ናት:: ሉቃ.1:43 ዮሐ.19:26
=ታማልዳለች:: ዮሐ.2:12 መዝ.44:9
=ከሴቶች ትበልጣለች:: ሉቃ.1:39 ሉቃ.1:28
=በፀጋ የተሞላች ናት:: ሉቃ.1:28
=ትውልድ ሁሉ ብጽዕት ይላታል:: ሉቃ.1:48
=መንፈስ ቅዱስ ያደረባት ናት:: ሉቃ.1:35
=የሰላምታዋ ቃል ፅንስ ያስዘልላል:: ሉቃ.1:44
ቅዱሳን መላዕክት
…………………………………
=ክብር ይገባቸዋል:: ራእ.18:1 ማቴ.28:2
=ሥልጣን አላቸው:: ራእ.18:1
=ስግደት ይገባቸዋል:: ኢያ.5:13 1 ዜና.21:16
=ያማልዳሉ:: ዘካ.1:13 ዳን.12:1
=ከሰው ወደ እግዚአብሔር ጸሎትን ያሳርጋሉ:: መሳ.6:21 ራእ.8:3
=ያጽናናሉ:: ዳን.10:21
=ያድናሉ:: መዝ.33:7
=ተአምራት ያደርጋሉ:: መሳ.13:19
ቅዱሳን ጻድቃን
…………………………………
=ክብር ይገባቸዋል:: መዝ.14:4

=ስግደት ይገባቸዋል:: 1 ነገ.2:15
=ምሥጋና ይገባቸዋል:: መዝ.32:1
=ያማልዳሉ:: ዘጸ.32:10
=ከሞቱም በሗላ ያማልዳሉ:: ሄኖ.9:22
=በረከት ከእነርሱ ይገኛል:: ምሳ.10:6
=መታሰብያቸው ለዘላለም ይኖራል:: መዝ.111:6
=ቃል ኪዳን ተሰጥቷቸዋል:: መዝ.88:3
ታቦት
.....................................
=ክብር አለው:: ኢያ.3:1~5
=ኃይል አለው:: 1 ዜና.13:19
=የእግዚአብሔር መገለጫ ነው:: ዘጸ.25:22
=ጣዖትን የሚሰባብር ነው:: 1 ሳሙ.5:1~5
=ሰማያዊ ነው:: ራእ.11:19
=በሐዲስ ኪዳንም አለ:: ማቴ.5:17 ራእ.11:19
=እግዚአብሔር የሠራው ነው:: ዘጸ.32:15~17
=ቅዱስ ነው:: 2 ዜና.35:3
=እርሱ ያለበት ሥፍራም የተቀደሰ ነው:: 2 ዜና.8:11

Wengel Lehzbachin
24/ ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ እነሆ
1: ስለ ሥላሴ
የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት:-
ዘፍ 1:26 ዘፍ 3:22
ዘፍ 11:18 ዘፍ 18:1-2
ኢሳ 48:26 ማቴ 3:16-17
ማቴ 28:19 ሉቃ 1:35
ዮሐ 7:28-29 ዮሐ 14:25-26
ሐዋ 3:14 1ኛ ቆሮ 12:4-7

2ኛ ቆሮ 13:14 ኤፌ 4:4-7
2: ስለ እመቤታችን ቅድስናዋ ፣ ክብሯ ፣ ድንግልናዋና አማላጅነቷ:-
መዝ 9:11 መዝ 13:10
መዝ 44:9 መዝ 86:5
መዝ 131:13 መዝ 44:2
መኃ 4:12 ኢሳ 7:14
ኢሳ 49:23 ኢሳ 60:14
ማቴ 1:23 ሉቃ 1:28
ሉቃ 1:42 ዮሐ 2:1-11
ዮሐ 19:16 ሮሜ 11:26-27
2ኛ ቆሮ 11:2 ራዕ 12:16
3: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈራጅ እንጂ አማላጅ አይደለም፥-
ዘፍ 3:22 1ኛ ሳሙ 16:1
ኢሳ 9:6 ዳን 7:14
ሆሴ 13:4 ዘካ 9:9-10
ሚክ 5:2 ሉቃ 1:32-33
ዮሐ 10:30 ሉቃ 2:12
ዮሐ 14:7 ሮሜ 9:5
ቆላ 2:9-10 ቲቶ 2:11-13
ዕብ 1:3-4 ዕብ 1:10-11
1ኛ ጴጥ 3:23 1ኛ ዮሐ 2:23
ራእ 3:22 ራእ 22:12-13
4: ስለ ታቦትና ጽላት
ዘፀ 24:12 ዘፀ 25:10
ዘፀ 25:21 ዘፀ 26:34
ዘፀ 31:18 ዘፀ 32:15
ዘፀ 34:1 ዘፀ 34:28
ዘፀ 37:1 ዘፀ 40:20
መኃ 7:89 ኢያ 3:3
ኢያ 7:6 2ኛ ቆሮ 6:16

5: ስለ ጾም የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ:-
ዘፀ 34:28 ዘፀ 9:9
ሳሙ 20:26 1 ሳሙ 7:6
1 ሳሙ 31:13 2 ኛ ሳሙ 1:12
2 ኛ ሳሙ 12:16 ዕዝ 8:21
ዕዝ 68:10 ዕዝ 108:24
ኢሳ 48:3 ኤር 36:9
ዳን 9:3 ዳን 20:2-3
ኢ. ዩኤ 2:14 ኢ.ዩኤ 2:12
?ዮና 3:5 ማቴ 4:2
ማ ቴ 6:16:18 ማቴ 9:14-15
ማ ቴ 17:21 ማር 2:18
ማ ር 9:29 ሉቃ 2:37
ሉ ቃ 18: 12 የሐ.ስራ 13:3 □ ሐዋ 14:23 2 ኛ ቆሮ 11:17
6: ስለ መስቀል በመጽሐፍ ቅዱስ:-
ማ ቴ 10:38 ማቴ 16:20
ማ ር 8:34 ሐዋ 5:30
□ 1 ኛ ቆሮ 1:18 ገላ 3:13
□ገ ላ 6:13 ፊል 2:8
ፊል 3:18
7: ጥምቀትን በተመለከተ:-
ሕዝ 36:25 ማቴ 3:5-6
ማቴ 26:19-20 ማር 1:4-5
ማር 16:16 ሉቃ 3:21
ዮሐ 3:5 ዮሐ 3:22
ኤፌ 4:5 ገላ 3:26-27
ሐዋ 19:4 ሐዋ 18:8
ሐዋ 13:24 ሐዋ 10:47 □ የሐዋ 9:18 1 ኛ ቆሮ 1:16
□ 1 ኛ ቆሮ 10 :2 1 ኛ ቆሮ 12:13
8:ስእለትን በተመለከተ:-

ዘ ኍ 28:20 ዘኍ 21:2
 ዘ ፀ 23:21 መሳ 11:30
መዝ 49:14 መዝ 75:11
 1ኛ ሳሙ 1:11 መክ 5:4-5
ዮና 2:10 ናሆ 1:15
ሐዋ 18:18

9: ጻድቃን ሰማዕታት ያማልዳሉ:-

 ዘ ፍ 18:17-18 ዘፍ 18:23:24
 ዘፍ 20:7 ዘፍ 33:3
ዘፍ 42:6 1ኛ ሳሙ 28 :14
2ኛ ሳሙ 1:2 2ኛ ነገ 1:13
2ኛ ነገ 2:15 2ኛ ነገ 4:9
2ኛ ነገ 4:32-35 መዝ 88:34
ማቴ 18:18 ዮሐ 20:23
 ሐዋ 10:25 ሐዋ 16 :29
 1ቆሮ 6:1-2 ፊሊ. 4:6
 1ኛጢሞ 5:17 ያዕ 5:14
 ራእ 14:13

10: መላእክት ዘወትር በእግዚአብሔር ፊት ይቆማሉ:-

መዝ 148:2 ኢሳ 6:3
ማቴ 4:12 ማቴ 18:10
ማቴ 25:31 ማር 8:38
ራእ 1:11 ሉቃ 1:19

11: መላእክት ጸሎታችንን ወደ እግዚአብሔር ያደርሳሉ:-

ጦቢ. 12:15 ሉቃ 15:10
 የ ሐዋ 10:4 ኢዮ 25:3
ኤር 33:22 ዳን 7:10
ሄኖ 10:1 ራእ 5:11

12:ለመላእክት የአክብሮት ስግደት ይገባል:-

ዘ ፍ 19:1 ዘኍ 22:31

ኢያ 5:14 ዳን 8:16-17
13:መላእክት አብሣሪያን ናቸው:-
ዘፍ 16:11 ሉቃ 1:13
ሉቃ 1:19 ሉቃ 1:30-31
ሉቃ 2:10-11
14:መላእክት በአደጋ ጊዜ ፈጥነው ይደረሳሉ:-
ዘፍ 22:11-12 መዝ 90:11-12
ዳን 6:22 ዳን 10:13
ማቴ 2:13 ሐዋ 5:19-20
ሐዋ 12:7
15: ፀበል መርጨት ያስፈልጋል:-
ዘኁ 19:20

በእግዚአብሔር የተወደደ ምስጋና.

25/ ሰባት ቁጥር ምስጢራት

በመጽሐፍ ቅዱስና በስርዓተ ቤተ-ክርስቲያን አስተምህሮ ሰባት ቁጥር ብዙ ምሳሌ እንዳለው ይታወቃል። በዕብራዊያን ዘንድም ሰባት ፍጹም ቁጥር ነው። ምሳሌ 24፥16 እግዚአብሔር ከሰኞ እስከ እሑድ ያሉትን ቀናት በሰባት ቁጥሮች ወስኗል:: ሕዝበ እስራኤል ከግብጽ ባርነት ወጥተው በሲና በርሀ ሲጓዙ ይመሩት የነበሩት በ 7 ደመና እንደነበረ ይታወቃል። ዘጻ 13፥21 ከዚህ ቀጥለንም ለቤተ-ክርስቲያን አስተምህሮ የ 7 ቁጥር ምስጢራትን ምሉዕነትን የሚያስረዱ ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን በዝርዝር እንመለከታለን፥፤

ሀ/ ሰባቱ አባቶች

1. ሰማያዊ አባታችን እግዚአብሔር
2. የነፍስ አባት
3. ወላጅ አባት
4. የክርስትና አባት
5. የጡት አባት

6. የቆብ አባት
7. የቀለም አባት

ለ ሰባቱ ዲያቆናት

1. ቅዱስ እስጢፋኖስ
2. ቅዱስ ፊልጶስ
3. ቅዱስ ጵሮክሮስ
4. ቅዱስ ጢሞና
5. ቅዱስ ኒቃሮና
6. ቅዱስ ጳርሜና
7. ቅዱስ ኒቆላዎስ

ሐ ሰባት የጌታ ቃላት /እኔ ነኝ

1. የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ
2. የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ
3. እኔ የበጎች በር ነኝ
4. መልካም እረኛ እኔ ነኝ
5. ትንሣዔና ሕይወት እኔ ነኝ
6. እኔ መንገድና ሕይወት ነኝ
7. እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ

መ ሰባቱ ሰማያት

1. ጽርሐ አርያም
2. መንበረ መንግሥት
3. ሰማይ ውዱድ
4. ኢየሩሳሌም ሰማያዊት
5. ኢዮር
6. ራማ
7. ኤረር

ሠ ሰባቱ ሊቃነ መላእክት

1. ቅዱስ ሚካኤል
2. ቅዱስ ገብርኤል
3. ቅዱስ ሩፋኤል

4. ቅዱስ ራጉኤል
5. ቅዱስ ዑራኤል
6. ቅዱስ ፋኑኤል
7. ቅዱስ ሳቁኤል

ረ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት

1. የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን
2. የሰርምኔስ ቤተ ክርስቲያን
3. የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን
4. የትያጥሮስ ቤተ ክርስቲያን
5. የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን
6. የፊልድልፍልያ ቤተ ክርስቲያን
7. የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን

ሰ ሰባቱ ተዐምራት

ጌታ እኛን ለማዳን በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ የተፈጸሙ ተዐምራት

1. ፀሐይ ጨልሟል
2. ጨረቃ ደም ሆነ
3. ከዋክብት ረገፉ
4. ዐለቶች ተሠነጠቁ
5. መቃብራት ተከፈቱ
6. ሙታን ተነሡ
7. የቤተ መቅደስም መጋረጃ

ሸ ሰባቱ የመስቀሉ ቃላት

1. አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ
2. አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው
3. ዛሬ ከእኔ ጋራ በገነት ትሆናለህ
4. እነሆ ልጅሽ እናትህ እነሆት
5. ተጠማሁ
6. ተፈጸመ
7. አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እስጥሃለሁ

ቀ ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን

1. ምሥጢረ ጥምቀት
2. ምሥጢረ ሜሮን
3. ምሥጢረ ቁርባን
4. ምሥጢረ ክህነት
5. ምሥጢረ ተክሊል
6. ምሥጢረ ንስሐ
7. ምሥጢረ ቀንዲል

በ ሰባቱ ዐበይት አጽዋማት

1. ዐቢይ ጾም
2. የሐዋርያት ጾም
3. የፍልሰታ ጾም
4. ጾመ ነቢያት
5. ጾመ ገሀድ
6. ጾመ ነነዌ
7. ጾመ ድኅነት

ተ ሰባቱ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠሉ ነገሮች

1. ትዕቢተኛ ዓይን ምሳ 16፥6-19
2. ሃሰተኛ ምላስ
3. ንፁህን ደም የምታፈስ እጅ
4. ክፉ ሃሳብን የምታፈልቅ ልብ
5. ለክፋት የምትፈጥን እጅ
6. የሐሰት ምስክርነት
7. በወንድሞች መካከል ጠብን የምታፈራ ምላስ

ቸ ሰባቱ ፀሎት ጊዜያት

1. ነግህ የጠዋት ጸሎት
2. ሠለስት (የ 3 ሰዓት ጸሎት)
3. ቀትር (የ 6 ሰዓት ጸሎት)
4. ተሰአቱ (የ 9 ሰዓት ጸሎት)
5. ሰርክ (የ 11 ሰዓት ጸሎት)
6. ነዋም (የምኝታ ጸሎት)

7. መንፈቀ ሌሊት (የሌሊት ጸሎት)

Share , Like, Comment, በማድረግ ለዓለም ይዳረስ ዘንድ ሃይማኖታዊ ድርሻዎን ይወጡ... ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ለዘላለም ፀንታ ትኑር!!

Habtamu Ayele

26/ ☞ኃጥያትን ስትሠራ፦ መዝሙረ ዳዊት ፶፩(51) ኣንብብ፤
☞ኣደጋ ሲያጋጥምህ፦ መዝሙረ ዳዊት ፺፩(91) ኣንብብ፤
☞ሰዎች ቢያሳዝኑህ፦ መዝሙረ ዳዊት ፳፯(27) ኣንብብ፤
☞እግዚኣብሔር ከኣንተ የራቀ ሲመስልህ፦ መዝሙረ ዳዊት ፻፴፩(131) ኣንብብ፤
☞እምነትህ ማነቃቂያ ሲያስፈልጋት፦ ዕብራውያን ፲፩(11) ኣንብብ፤
☞ብቻህን ስትሆንና ስትፈራ፦ መዝሙረ ዳዊት ፳፫(23) ኣንብብ፤
☞ስትጨነቅ፦ ማቴዎስ ወንጌል ፰፥፱–፴፬(8:9–34) ኣንብብ፤
☞ስትቀየምና ነቃፊ ስትሆን፦ 1 ኛ ቆሮንቶስ ፫(3) ኣንብብ፤
☞ስለክርስትና ግራ ሲገባህ፦ 2 ኛ ቆሮንቶስ ፭፥፲፭–፲፰(5:15–18) ኣንብብ፤
☞ያልተፈለክ መስሎ ሲሠማህ፦ ሮሜ ፰፥፴፩–፴፱(8:31–39) ኣንብብ፤
☞ሠላምን ስትሻ፦ ማቴዎስ ወንጌል ፩፥፳፭–፴(1:25–30) ኣንብብ፤
☞ዓለም ከእግዚኣብሔር የበለጠ ሲመስልህ፦ መዝሙረ ዳዊት ፺(90) ኣንብብ፤
☞ክርስቶስን እንደ መታመኛህ ስትሻው፦ ሮሜ፰፥፩–፴(8:1–30) ኣንብብ፤
☞ለጉዞ ከቤትህ ወጥተህ ስትሄድ፦ መዝሙረ ዳዊት ፻፳፩(121) ኣንብብ፤
☞ለምትሠራው ስራ ብርታት ሲያስፈልግህ፦ ኢያሱ ፩(1) ኣንብብ፤
☞የኑሮ ውድነት ባለፀጋነት ሀሳብህን ሲያጠብቡት፦ የማርቆስ ወንጌል ፲፥፲፯–፴፩(10:17–31) ኣንብብ፤
☞የጭንቀት ሐሳብ ሲያስቸግርህ፦ መዝሙረ ዳዊት ፳፯(27) ኣንብብ፤
☞የባንክ ሂሳብህ ባዶ ሲሆን፦ መዝሙረ ዳዊት ፴፯(37) ኣንብብ፤
☞በሰው ልጅ ላይ አመኔታ ስታጣ፦ 1 ኛ ቆሮንቶስ ፲፫(13) ኣንብብ፤
☞ሰዎች የወዳጅነት ስሜት ያላሳዩህ ሲመስልህ፦ የሐንስ ወንጌል ፲፭(15) ኣንብብ፤
☞ተስፋ ስታጣ፦ መዝሙረ ዳዊት ፻፳፮(126) ኣንብብ፤
☞አለም ከኣንተ ጋር ሲነፃፀር ትንሽ መስሎ ሲሠማህ፦ መዝሙረ ዳዊት ፲፱(19)

ኣንብብ፣
☞ፍሬ ማፍራት ስትፈልግ፦ የየሐንስ ወንጌል ፲፭(15) ኣንብብ፣
☞የጳውሎስ የደስታ ሚስጥር፦ ቆላሲስ ፫፡፲፪–፲፯(3:12–17) ኣንብብ፣
☞ከሌሎች ሰዎች ጋር በሠላም ለመኖር፦ ሮሜ ፲፪(12) ኣንብብ፣
☞ሙስና ለመስራት ስታስብ፦ ትንቢተ ዕንባቆም ፪፡፮(2:6) ኣንብብ፣
☞ንስሃ መግባት ስትፈራ፦ ሲራክ ፩፡፭(1:5) ኣንብብ፣
☞ስለ ኣስራት ቦክራት ግር ካለህ፦ ሲራክ ፲፬፡፲፩(14:11) ኣንብብ።
፡
ወስብሐት ለእግዚኣብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል
ወለመስቀሉ ክቡር

Zerihun Yeshy.

27/ ፡፡፡ ሕግጋተ እግዚአብሔር ፡፡፡ 1. ሕገ ልቦና (የሕሊና ሕግ):-

2. አሠርቱ ቃላት: /አሠርቱ ትዕዛዛት/ /አሠርቱ ሕግጋት/ /ሕገ መጽሐፍ (ሕገ ኦሪት)/:-

3. ስድስቱ ሕግጋት /ስድስቱ ትዕዛዘተ / /ስድስቱ ቃላተ/ ወንጌል:-

4. አሥሩ አንቀጸ ብፁዓን:-

5. በለተ ምጽአት ከጌታችን የምንጠየቃቸውና የምንመልሳቸው 6 ጥያቄዎች:-

ከላይ በተራ ቁጥር የተዘረዘሩ ሕግጋት ማብራሪያ ተሰቶባቸዋል አንብበው ይጠቀሙ: +

+እግዚአብሔር አማላክ ፈጣሪ እንደመሆኑ ፈቃዱ የማይለወጥ ቀዋሚ ስለሆነ ጊዜያዊና ቅጽበታዊ ፍጥረት አልፈጠረም: ፈጥሮም ያለዓላማ: ያለሕግ ያለሥርዓት አልተወም።

በዓለሙ ሙሉ የሆነ እግዚአብሔር ሕግጋቱም ሁሉን የሚመለከትና ለዓለሙ ሁሉ ቀዋሚ የሆኑ ሕግጋት ናቸው። እነዚህም:- ሕገ ልቦና (የሕሊና ሕግ) : አሠርቱ ቃላት: ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ናቸው።

+++++++

፡፡፡1፡፡፡ ሕገ ልቦና (የሕሊና ሕግ):-

በሰው ልቦና አንድ ጊዜ ከተጻፈ ሳያረጅ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የሚኖር ሕግ ነው። ሕገ ልቦና በሰው ሁሉ ልብ የሚገኝ እያንዳንዱን ሰው ማንም ሳያስተምረው: ክፋውንና ደጉን ለይቶ ሳይነግሩት እንዲያውቅ የሚያደርገው ነው። እውነተኛ ሰው ምንም ባይማር በዚህ በሕገ ልቦና ወይም በሕገ ተፈጥሮ መሰረት እውነትን ከሐሰት: ጽድቅን ከኃጢአት: ደጉን ከክፉ ለይቶ ያውቃል። ከዚህም የተነሣ እውነቱን ይናገራል: ይሰራል ከክፉም ይርቃል።

+። ስለ ሕገ ተፈጥሮ (ሕገ ልቦና) ቅዱሳት መጽሐፍት በተለያየ መንገድ ይመሰክራሉ። ስለዚህም ሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ አለ:-

፲ እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላምና።

፲ ያለ ሕግ ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ ያለ ሕግ ደግሞ ይጠፋሉና፲ ሕግም ሳላቸው ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል፲

፲ በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና።

፲ ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ፥ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፲

፲ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፥ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ። (ወደ ሮሜ ሰዎች ምዕ. 2÷11-15)

+ይኸ ሕገ ልቦና የተባለው ያን ጊዜ በተፈጥሮ እንደተሰጠ ያለ የጸናም ሕግ ይሁን እንጂ የሰው ልጅ በሕገ ልቦና ብቻ ሊጠበቅ ባለመቻሉ በግድ የጹሑፍ ሕግ አስፈለገ። ስለዚህም እግዚአብሔር አምላክ በእጁ ጽፎ ሌላ ሕግን በሙሴ አማካይነት ለጊዜው ለእሥራኤል ወገን ፍጻሜው ግን ለሰው ልጅ ሁሉ ሰጥቷል። ቀጥሎም የጌታ ደቀ መዛሙርት ሐዲሱን የኪዳን ሕግ (ስድስቱን ቃላት ወንጌል) በጹሑፍ አበርክተዋል።

++++++++++

።።።2።።። አሠርቱ ቃላት: አሠርቱ ትዕዛዛት: አሠርቱ ሕግጋት: ሕገ መጽሐፍ(ሕገ ኦሪት):-

የሚባሉት እግዚአብሔር አምላክ ግንኙነቱን ከእስራኤል ህዝብ ጋር በማድረግ መገናኛ ይሆኑ ዘንድ የሠራቸውና የደነገጋቸው ሲሆኑ: በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፉ አሠርቱ ቃላት እየተባሉ የሚጠሩ ናቸው። እነዚህም እግዚአብሔር በሁለት ሠሌዳ ጽፎ ለእስራኤል ያስተላለፈው ሕግ ነው።

ሁለቱ የሕግ ጽላት የአስርቱ ቃላት ማደሪያ ሠሌዳ ሁነው የተሰጡ ናቸው። እንደ ሊቃውንቱ አስተያየት በአንደኛው ጽላት ሦስት ቃላት እግዚአብሔር ወይም እግዚአብሔር አምላክን የሚመለከቱ ለእርሱ ልናደርግና ልንፈፅመው የሚገባንን የሚገልጡ ናቸው። በሁለተኛው ጽላት ደግሞ ሰባት አንቀጾች ተጽፈውበታል: ይኸውም ሰውን የሚመለከቱ ማለት ሰው አንዱ ለሌላው ሊያደርገውና ሊፈጽመው የሚገባውን የሚያሳዩ አሠርቱ ቃላት በመጀመሪያ ለሰው መመሪያ እንዲሆኑ በጽሁፍ የተላለፉ ህግጋት ናቸው። ምክንያቱም የሰው ልጅ በመጀመሪያ በሕገ ልቦና እንዲሁም በሕገ ህሊና በሕግ ሊጸና ለእግዚአብሔርም ሊታዘዝ ተፈጥሮ ነበር: ይህ ግን ባለመቻሉ በጧትና በማታ እያነበበ: እያየም ሰው የሆነ ሁሉ እንዲጠብቀውና እንዲፈጽመው እግዚአብሔር አምላክ ስለፈቃደ ሕጉን በጽሁፍ ሰጠው እነዚህ በጽሁፍ የተላለፉ የብሉይ ኪዳን ሕግጋት ለክርስቲያኑ ህዝብ አሁንም አስፈላጊዎች ናቸው።

+ ከአሠርቱ ቃላት ዘጠኙ ተጠብቀው አንደኛው እንኳን ከፈረሠ አሠርቱ ሕግጋት ሁሉ እንደፈረሱ ይገመታል እንጂ የዘጠኙ መጠበቅ ምንም ዋጋ የለውም። ለምሳሌ አሥር በር ያለው ቤት ቢኖር ዘጠኙ በሮች ቢዘጉና አንዱ ክፍቱን ቢያድር: ሌባ ክፍት በሆነው በአንደኛው በር ገብቶ ንብረቱን ሁሉ ከወሰደው የዘጠኙ በሮች መዘጋት ምንም ጥቅም አላስገኘም ማለት ነው የአንደኛው መከፈት ለንብረቱ መጥፋት ምክንያት ሆኗልና። አሠርቱ ቃላትም በትክክል ካልተጠበቁ ዋጋ የማያሰጡ መሆናቸውን ሐዋርያው ያዕቆብ እንዲህ ሲል ያስረዳል:-

" ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል፤ አታመንዝር ያለው ደግሞ። አትግደል ብሎአልና፤"

(የያዕቆብ መልእክት 2:10)

::::::::::::

10 ቱ ትዕዛዛት እነማን ናቸው

::::::::::::

>አንቀጽ 1:-

" ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።"

(ኦሪት ዘጸአት 20:3)

:::::

>አንቀጽ 2:-

" የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ

የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና። "
(ኦሪት ዘጸአት 20:7)
።።።
>አንቀጽ 3:-
" የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ።"
(ኦሪት ዘጸአት 20:8)
።።።
>አንቀጽ 4:-
" አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም።"
(ኦሪት ዘጸአት 20:12)
።።።
>አንቀጽ 5:-
፤ አትግደል።
(ኦሪት ዘጸአት ምዕ. 20:13)
።።።
>አንቀጽ 6:-
፤ አታመንዝር።
(ኦሪት ዘጸአት ምዕ. 20:14)
።።።
>አንቀጽ 7:-
፤ አትስረቅ።
(ኦሪት ዘጸአት ምዕ. 20:15)
።።።
>አንቀጽ 8:-
፤ በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር።
(ኦሪት ዘጸአት ምዕ. 20:16)
።።።
>አንቀጽ 9
፤ የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባልንጀራህን ሚስት ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም

አህያውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ።
(ኦሪት ዘጸአት ምዕ. 20:17)
።።።።
>አንቀጽ 10
" ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ፤ "
(ኦሪት ዘሌዋውያን 19:18)
++++++
።።3።። ስድስቱ ሕግጋት (ትዕዛዘተ) ወንጌል:-
እንደ ብሉይ ኪዳን እምነት ስርዓት ህግን እንደፈፀመ የሚቆጠረው ፍፁምም አይሁዳዊ ነው የሚባለው አሠርቱ ቃላተ ኦሪትን የጠበቀው ነበር። በሐዲስ ኪዳንም አሠርቱ ቃላት ኦሪት ምንም ሳይነኩ እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪ ሌሎችም አዲሶች ሕጎች አስፈለጉ። አሠርቱ ቃላተ ኦሪት መጠበቃቸውንና እንዳሉም መጽናታቸውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
፤ እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።
፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ። (የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:17-18) ሲል ግልጽ አድርጎ ተናግሯል።
+ከዚህ በተጨማሪ ግን እነዚህኑ አሠርቱ ቃላትን በስድስቱ አንቀጽ አጠቃሎና አሳጥሮ ቃላተ ወንጌል ወይም ትዕዛዛተ ወንጌል ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ ግን እላችኋለሁ እያለ አጥብቆ: አጽንቶና ወስኖ ተናግሮ ይገኛል።
አሁንም የሐዲስ ኪዳንን ህግጋት ስናቀርብ እነዚህ የብሉይ ኪዳን ህግጋት ለሐዲስ ኪዳን መሸጋገሪያ ሆነው አጥረውና ተጠቃልለው በስድስት ቃላት ይቅረቡ እንጂ አሁንም መሠረቶቹ አሠርቱ ቃላት ናቸው።
ሆኖም አጥረው: ተጠቃለው ከበድም ብለው ለሐዲስ ኪዳን መታወቂያ መለያም ሕግ ሆነው የቀረቡ ሲሆን እነዚህን ሕግጋት ለይቶ: ጠንቅቆ ማወቅና መጠቀም በጣም አስፈላጊ በመሆኑ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል:-
።።።።
>አንቀጽ 1:-
አትግደል ላለው

" ለቀደሙት። አትግደል እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል።"
+++++++
" እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:21÷22)
።።።
>አንቀጽ 2:-
አታመንዝር ላለው
" አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል።"
+++++++
" እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:27÷28)
።።።
>አንቀጽ 3:-
መፍታት እንደማይገባ
፤ ሚስቱን የሚፈታት ሁሉ የፍችዋን ጽሕፈት ይስጣት ተባለ።
++++++
፤ እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል።
(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:31÷32)
።።።
>አንቀጽ 4:-
ፈጽመህ አትማል ላለው
፤ ደግሞ ለቀደሙት። በውሸት አትማል ነገር ግን መሐላዎችህን ለጌታ ስጥ እንደተባለ ሰምታችኋል።
+++++++
፤ እኔ ግን እላችኋለሁ። ከቶ አትማሉ፤ በሰማይ አይሆንም የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፤

፤ በምድርም አይሆንም የእግሩ መረገጫ ናትና፤ በኢየሩሳሌምም አይሆንም የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና፤
፤ በራስህም አትማል፥ አንዲቱን ጠጉር ነጭ ወይም ጥቁር ልታደርግ አትችልምና።
፤ ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፤ ከነዚህም የወጣ ከክፉው ነው።
(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:33-37)
።።።
>አንቀጽ 5:-
"ክፉውን በክፉ አትቃወሙ"
፤ ዓይን ስለ ዓይን ጥርስም ስለ ጥርስ እንደ ተባለ ሰምታችኋል።
+++++++
፤ እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ክፉውን አትቃወሙ፤ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፤
(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:38-39)
።።።
>አንቀጽ 6:-
"ጠላትህን ስለመውደድ"
፤ ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል።
+++++++
፤ እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና።
፤ የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን?
፤ ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ? አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን?
፤ እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ።
(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:43-48)
+++++++
።።4።። አሥሩ አንቀጸ ብፁዓን:-

ስድስቱ ቃላተ ወንጌል የአስርቱ ቃላት ኦሪት መጠበቂያና ማጠሪያ እንደሆኑ አንድም አሠርቱ ቃላት በስድስት ቃላተ ወንጌል እንደጸኑ ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ደግሞ አሥሩ አንቀጸ ብፁዓን ይታጠራሉ፡ ይጸናሉ፡ ፍጹምነታቸው እንዲታወቅ ይሆናል።

እነዚህ አሥሩ አንቀጸ ብፁዓን የሕግ ፈጻሚነት ምልክትና የፍፁምነት መታወቂያ ትሩፋት ናቸው እንጂ ሕግጋት አይደሉም። እነዚህ የፍጹምነት፡ የብፅዕናና የቅድስና መታወቂያ አንቀጾች ጌታ የተናገራቸው ሱሆኑ የፍፁምነት ማዕረግ የሚሰጡ ናቸው።

እነዚህ አሥሩ አንቀጸ ብፁዓን ወይም ሕገ ትሩፋት የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው:-

1. " በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:3)

2. " የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፥ መፅናናትን ያገኛሉና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:4)

3. " የዋሆች ብፁዓን ናቸው፥ ምድርን ይወርሳሉና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:5)

4. " ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፥ ይጠግባሉና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:6)

5. " የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፥ ይማራሉና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:7)

6. " ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፥ እግዚአብሔርን ያዩታልና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:8)

7. " የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:9)

8. " ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:10)

9. ፲ ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ።

፲ ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፥ ሐሴትም አድርጉ፲ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና።
(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:11-12)

10. " ይህን ብታውቁ፥ ብታደርጉትም ብፁዓን ናችሁ።"
(የዮሐንስ ወንጌል 13:17)

+ሙሴ ዘጠኙን ሕግጋት በኦሪት ዘፀአት 20:17 ተናግሮ አሥረኛውን በኦሪት ዘሌዋውያን 19:18 እንዳመጣው ጌታም የተናገረውን አስሩን አንቀጸ ብፁዓን 9 ኙን በማቴዎስ ወንጌል ተናግሮ አስረኛውን በዮሐንስ ወንጌል ያመጣዋል። ይህም የመጨረሻው የብፅዕና አንቀጽ ትህትና ነው።
+++++++
።።።5።።። በለተ ምጽአት ከጌታችን የምንጠየቃቸውና የምንመልሳቸው 6 ጥያቄዎች:-
ትንሣኤ ዘጉባኤ:- ትንሳኤ ዘጉባኤ ማለት በዕለተ ምጽአት ጌታ ለፍርድ ሲመጣ በእርሱ ትእዛዝ (በአዋጅ ድምፅ) ተለያይተው በተለያየ ስፍራ ይኖሩ የነበሩ ነፍስና ሥጋ ከሞት በኋላ በነፍስና ስጋ ህይወት መገኘትና ተዋህዶ መነሳት ማለት ነው። ይህ ሰውን ብቻ የሚመለከት ነው።
+++++++
" በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ፤ እኵሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት፥ እኵሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቍልና። "
(ትንቢተ ዳንኤል 12:2)
" በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ።"
(የዮሐንስ ወንጌል 5:28-29)
" እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።"
(የዮሐንስ ራእይ 22:12)
" እነሆ፥ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፥ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። አዎን፥ አሜን።"
(የዮሐንስ ራእይ 1:7)
፲ ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤
፲ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።
፲ ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ።
(1 ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ምዕ. 4:16-18)
። ። ። ። ። ። ። ።

*1 የመጀመሪያው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አውሬ የበላው ነፋስ የበተነው ያለቀውና የደቀቀው ሁሉ ራሱ በፈረሰበት ቦታ ላይ ይሰበሰባል። (ያዕቆብ ዘስሩግ ቁ.91)
*2 ሁለተኛው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አጥንትና ሥጋ ተዋህደው ሳይንቀሳቀስ ትኩስ ሬሳ ይሆናሉ አጥንቶችና ጂማቶች ከስጋና ከደም ጋር ይያያዛሉ። እስኪነሱ ያለመንቀሳቀስ ፍጹም በድን ይሆናል።
*3 ሶስተኛው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ በቅዋሚ አካል በምትናገር አንደበት ከራስ ጠጉራቸው እስከ እግር ጥፍራቸው ከቁጥር ሳይጎድሉ ከሰውነታቸው ሳይከፈል ወንድ በአቅመ አዳም የሠላሳ ዓመት ጎልማሳ: ሴት በአቅመ ሔዋን የአስራ አምስት ዓመት ቆንጆ ሆነው በአርባ ቀን በእናቱ ማኅፀን ደም ሆኖ የወረደ ጽንስ ሳይቀር እያንዳንዱ የሥራውን ዋጋ ሊቀበል ይነሳሉ።
++++++
፲ የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፲
፲ አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፲ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል፥
፲ በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል።
፲ ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል። እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፲ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።
፲ ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፥
፲ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና።
፲ ጻድቃንም መልሰው ይሉታል። ጌታ ሆይ፥ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህስ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ?
፲ እንግዳ ሆነህስ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ?
፲ ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን?
፲ ንጉሡም መልሶ። እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል።
፲ በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል። እናንተ ርጉማን፥ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ።
፲ ተርቤ አላበላችሁኝምና፥ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና፥ እንግዳ ሆኜ

አልተቀበላችሁኝምና፥
፲ ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፥ ታምሜ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና።
፲ እነርሱ ደግሞ ይመልሱና። ጌታ ሆይ፥ ተርበህ ወይስ ተጠምተህ ወይስ እንግዳ ሆነህ ወይስ ታርዘህ ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ መቼ አይተን አላገለገልንህም? ይሉታል።
፲ ያን ጊዜ። እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል።
፲ እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።
(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 25:31-46)
::::: ተፈጸመ :::::
ጌታችን መድኃኒታችና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰራቸው ሕግጋት እንድንፈጽም ይርዳን: አለማመናችንን ይርዳው አሜን።
ወ ስ ብ ሐ ት ለ እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር
ወ ለ ወ ላ ዲ ቱ ድ ን ግ ል
ወ ለ መ ስ ቀ ሉ ክ ቡ ር
አ...ሜ...ን
(ምንጭ:ነገረ ምጽአት ከሚል መጽሐፍ አባ ወልደ ዮሐንስ ወ/ኢየሱስ እንዳዘጋጁት በከፊል የተወሰደና በተጨማሪም ከ 81 አህዱ መጽሐፍት የተወሰደ )

የሰንበት ትምህርት ቤቱ ማስታዎሻና ሰንበት ትምህርት ቤቱ added 2 new photos .
28/ ተህድሶ መናፍቃን ቤተክርስቲያንን ለማጥቃት እና የተሳሳተ አስተምህሮዎቻቸውን ለማስፋፋት የተለያዩ ዘዴዎችን እየተጠቀሙ እንደሆነ ተገለፀ።
ከእነዚህ የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅዶች መካከል
1. የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችን ሰርጎ በመግባት ለመቆጣጠር እና ሰለባ ለማድረግ ሰፊ የሆነ ስራ እየተሰራ ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ አድባራትና ገዳማት መካከል 20 ሰንበት ትምህርት ቤቶችን በመጀመሪያው ዙር (ለሚቀጥሉት 2 ዓመታት) ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር የታሰበ ሲሆን ከእነዚህም መካከል፡-
1. ገነተ ፅጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት (ፒያሳ)
2. ምስካየ ኅዙናን መድኃኒዓለም ገዳም ተምሮ ማስተማር ሰንበት ት/ቤት (6 ኪሎ)

3. የካ ደብረ ሳህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ደብረ ሰላም ሰንበት ት/ቤት (መገናኛ)
4. ግቢ ገብርኤል ገዳም አምደ ሃይማኖት ሰንበት ት/ቤት (4 ኪሎ)
5. ደብረ ፅጌ ቅዱስ ኡራኤል መራሔ ብርሃናት ሰንበት ት/ቤት (ካሳንቺስ)
6. አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም መከታ ደናግል ሰንበት ት/ቤት (መርካቶ)
7. ቦሌ መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን ፈለገ ዮርዳኖስ ሰንበት ት/ቤት በቀዳሚነት የተጠቀሱ ሲሆን በሚሰጡት የተካታታይ ትምህርት ፣ የአባላት ብዛትንና የተለያዩ ክፍተቶችን በመጠቀም ለመቆጣጠር ሰፊ ስራ እየተሰራ ነው። በተጨማሪም ከ 20 ከተዘረዘሩት ሰንበት ት/ቤቶች መካከል የተወሰኑት አሁንም ከባድ በሚባል መልኩ የተሃድሶ መናፍቃን እንቅስቃሴ እንዳለ እና በሚፈልጉት መልኩ እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን መረጃው ከመግለፁም በተጨማሪ ከላይ ለአብነት ከተጠቀሱት ከ 20 ዎቹ ሰንበት ትምህርት ቤቶች መካከል አንኳን በተራ ቁጥር 3 ፣5 እና 6 የተጠቀሱት በዋናነት ተጠቂ ሲሆኑ በተ.ቁ. 4 የተጠቀሰውም የዚሁ ሰለባ ለመሆን ጫፍ ላይ ነው። ለአብነትም በተጠቀሱት ሰ/ት/ቤቶች ያለው ትምህርት፣ ስነ-ፅሁፎች የሚተላለፉ መልዕክቶች ሳይቀሩ ችግር ማሳየታቸው፣ በጥበቡ ዘርፍ መብራት እየጠፋ በኪነ-ጥበብ ምሽት በማሳበብ ስርዓትን ማፋለስ፣ አባላትን ማነሳሳት እና ሰላም ማሳጣት፣ በሀይማኖት ጠንካራ የሚባሉ አባላትን የተለያዩ ምክንያቶችን በመዘርዘርና በአባላት ዘንድ መጥፎ መጥፎ ነገሮች የሀሰት ፕሮፓጋንዳ በማስወራት ማራቅ ፣ የአስተዳደር ቦታውን ለመቆጣጠር መንቀሳቀስና መያዝ ወ.ዘ.ተ በዋናነት ተጠቃሾች ናቸው።

ስለዚህ የሁሉም ሰንበት ትምህርት ቤቶች አስተዳደር፣ አባላቶች እንዲሁም ምዕመናንና ሰበካ ጉባኤ በሙሉ ይህን ከባድ ጉዳይ በመታገል ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችንን በመጠበቅ ተተኪ ዲያቆናትን፣ ካህናትን፣ ለሀገር ፍቅር ያላቸው ዜጎችን ልንፈጥርና ቤተክርስቲያናችንን ልንታደጋት ይገባል እያልን ሰንበት ት/ቤቶችም አባላቶቻችንን በትክክል መለየት፣ ሙሉ መረጃ መያዝ እንዲሁም ከግሩፕኝነት፣ ከአመፃ እንቅስቃሴ እራሳቸውን በመጠበቅ ቤተክርስቲያንን ሊታደጉ እንደሚገባና ሰርጎ ገቦችን በመለየት ማስወጣት እንዳለባቸው ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

2. ማህበራት ..............................................ይቆየን።

ኢትዮጲያ:ኦርቶዶክስ:ቤተ
ክስቲያን(ETHIOPIA ORTHODOX CHURCH)
ደጓ እናቴ ሰንበት ትምህርት ቤት ያስተማረችኝ..............................
29/ በስርዓተ ቤተ-ክርስቲያን አስተምህሮ ስባትቁጥር ብዙ ምሳሌ እንዳለው ይታወቃል። በዕብራዊያን ዘንድም ሰባት ፍጹም ቁጥር ነው።
ምሳሌ 24፥16 እግዚአብሔር ከሰኞ እስከ እሑድ ያሉትን ቀናት በሰባት ቁጥሮች ወስኗል ሕዝበ እስራኤል ከግብጽ ባርነት ወጥተው በሲና በርሀ ሲጓዙ ይመሩት የነበሩት በ 7 ደመና እንደነበረ ይታወቃል። ዘዳ 13፥21
ከዚህ ቀጥለንም ለቤተ-ክርስቲያን አስተምህሮ የ 7 ቁጥር ምስጢራትን ምሉዕነትን የሚያስረዱ ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን በዝርዝር እንመለከታለን፣፤
ሰባቱ አባቶች
1. ሰማያዊ አባታችን እግዚአብሔር
2. የነፍስ አባት
3. ወላጅ አባት
4. የክርስትና አባት
5. የጡት አባት
6. የቆብ አባት
7. የቀለም አባት
ሰባቱ ዲያቆናት
1. ቅዱስ እስጢፋኖስ
2. ቅዱስ ፊልጶስ
3. ቅዱስ ጵሮክሮስ
4. ቅዱስ ጢሞና
5. ቅዱስ ኒቃሮና
6. ቅዱስ ጳርሜና
7. ቅዱስ ኒቆላዎስ
ሰባት የጌታ ቃላት /እኔ ነኝ

1. የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ
2. የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ
3. እኔ የበጎች በር ነኝ
4. መልካም እረኛ እኔ ነኝ
5. ትንሣዔና ሕይወት እኔ ነኝ
6. እኔ መንገድና ሕይወት ነኝ
7. እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ

ሰባቱ ሰማያት

1. ጽርሐ አርያም
2. መንበረ መንግሥት
3. ሰማይ ውዱድ
4. ኢየሩሳሌም ሰማያዊት
5. ኢዮር
6. ራማ
7. ኤረር

ሰባቱ ሊቃነ መላእክት

1. ቅዱስ ሚካኤል
2. ቅዱስ ገብርኤል
3 ቅዱስ ሩፋኤል
4. ቅዱስ ራጉኤል
5. ቅዱስ ዑራኤል
6. ቅዱስ ፋኑኤል
7. ቅዱስ ሳቁኤል

ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት

1. የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን
2. የሰርምኔስ ቤተ ክርስቲያን
3. የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን
4. የትያጥሮስ ቤተ ክርስቲያን
5. የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን
6. የፊልድልፍልያ ቤተ ክርስቲያን

7. የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን

ሰባቱ ተዐምራት

ጌታ እኛን ለማዳን በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ የተፈጸሙ ተዐምራት

1. ፀሐይ ጨልሟል
2. ጨረቃ ደም ሆነ
3. ከዋክብት ረገፉ
4. ዐለቶች ተሠነጠቁ
5. መቃብራት ተከፈቱ
6. ሙታን ተነሡ
7. የቤተ መቅደስም መጋረጃ

ሰባቱ የመስቀሉ ቃላት

1. አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ
2. አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው
3. ዛሬ ከእኔ ጋራ በገነት ትሆናለህ
4. እነሆ ልጅሽ እናትህ እነሆት
5. ተጠማሁ
6. ተፈጸመ
7. አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እስጥሃለሁ

ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን

1. ምሥጢረ ጥምቀት
2. ምሥጢረ ሜሮን
3. ምሥጢረ ቁርባን
4. ምሥጢረ ክህነት
5. ምሥጢረ ተክሊል
6. ምሥጢረ ንስሐ
7. ምሥጢረ ቀንዲል

ሰባቱ ዐበይት አጽዋማት

1. ዐቢይ ጾም
2. የሐዋርያት ጾም
3. የፍልሰታ ጾም

4. ጾመ ነቢያት
5. ጾመ ገሀድ
6. ጾመ ነነዌ
7. ጾመ ድኅነት

ሰባቱ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠሉ ነገሮች

1. ትዕቢተኛ ዓይን ምሳ 16፥6-19
2. ሃሰተኛ ምላስ
3. ንፁህን ደም የምታፈስ እጅ
4. ክፉ ሃሳብን የምታፈልቅ ልብ
5. ለክፋት የምትፈጥን እጅ
6. የሐሰት ምስክርነት
7. በወንድሞች መካከል ጠብን የምታፈራ ምላስ

ሰባቱ የፀሎት ጊዜያት

1. ነግህ የጠዋት ጸሎት
2. ሠለስት (የ 3 ሰዓት ጸሎት)
3. ቀትር (የ 6 ሰዓት ጸሎት)
4. ተሰአቱ (የ 9 ሰዓት ጸሎት)
5. ሰርክ (የ 11 ሰዓት ጸሎት)
6. ነዋም (የምኝታ ጸሎት)
7. መንፈቀ ሌሊት (የሌሊት ጸሎት)

በአረብ:ሀገር:የሚገኙ:ክርስትያኖች:ህብረት(chr
istian Unity In Middle East)

30/ እውነተኛ አገልጋይ ማነው???

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሁለት ጎራ የተከፈለ የአገልጋዮች ህብረት እንዳለ ሀገር ያወቀው ሀቅ ነው ።

1 የአዳም ልጆችና የክርስቶስ ልጆች
2 ብሉይ ኪዳኖችና ሀዲስ ኪዳኖች
3 ፀረ ክርስቶሶችና ፀረ ጣኦቶች

4 ወንጀል ወዳዶችና ወንጌል ወዳዶች
5 ማህበርተኞችና ቲኦሎጅያኖች
ከብዙ በጥቂቱ መለያቸው ይሔ ነው እኔ ግን ለዛሬ ማነው እውነተኛ በሚል ጥቂት ልበላችሁ....
በማህበረ ቅዱሳን የሚመራው ራሱን የቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪ ነኝ የሚለው ቡድን በስሩ 1 የ 4 ኪሎው ግሩፕ አለ እነ ጳውሎስ ተስፋዬ ሞሲሳ ዳዊት ጥበቡ በላይ ወርቁ ..በቅርቡ ከጳውሎስ ጋር ምስጢር እንዳያወጣበት በሚል እርቅ የፈፀመው ዘመድኩን በቀለ ልዑል ሰገድ ...2 የመህይሙ ቡድን ነው ታታ ዘየካ ፣ ደረጀ ወይንዬ ፣ ፊሸን ፀናፅ መዝሙር ቤት ፣እንዳለ ኤሴቅ መዝሙር ቤት ፣ዘማሪ ገዛኸኝ፣ በሀይሉ ተበጀ ፣መቅደስ ማርዬ፣ ሲስተር ሕይወት ( በቅርቡ ዳግመኛ ከይትባረክ ጋር የተጋባችው ) መሰረት ማሞ (( በክፉ አመሏ ባሏ ጥሏት የጠፋው )
መለያቸው
1 መጠጥ ህይወታቸው ነው
2 ጉባኤ ተደራድረው መሄድ
3 የሰው ሚስት ማማገጥ
4 ካሴታቸው ያለመሸጥ እና የገበያ እጦት
5 የሚገኙበት ቦታ ግሮሰሪ ጭፈራ ቤት
እስከ አሁን የምላችሁ ሐሰት አለመሆኑ ማረጋገጥ ለምትፈልጉ በቅርቡ ከአሜሪካ ተሀድሶን ለማጥፋት በሚል የመጣ ብር ላይ መጣላታቸውን እና የሀሳብ ልዩነት ማምጣታቸውን አበክሬ ላስገነዝባችሁ እወዳለሁ የፀባቸው መነሻም እነደረጀ ወይንዬ ይህንን ስልት ያመጣነው እኛ ነን ሲሉ እነ ጳውሎስ ደግሞ መህይም አይመራንም በማለት ጎራ ለይተዋል።
እንግዲህ እነዚህን ነው እንደ ሀይማኖተኛ የምትመሰክሩላቸው..በልተው የሚቀድሱ ዘሙተው ቤተ መቅደስ የሚገቡት እነርሱ ሆነው ሳለ ምንም የማያውቀው ምስኪን ግን ወገቡን ታጥቆ ለበላይ ወርቁ ይሟገታል እኔ በዚህ ፅሁፍ ከዋሽሁ እስኪ ከምትሏቸውና ምታደንቋቸው አንዳቸው አስተያየት ይስጡ ????
የሰውን ገበና ማውጣት በደል ቢሆንም ራሳቸውን ፃድቅ አስመስለው ያልተሰራን ስራ ፈጥረው ለሚያወሩ ግን እኔ ለመፃፍ እገደዳለሁ
ሰክሮ ከኮተቤ ማርያም ስፒከር ተነጥቆ ከአውደ ምህረት የወረደው ማነው?
የሰሚስት ሲያማግጥ እጅ ከፍንጅ የተያዘው ማነው

ሚስቱን በ facebook ያጣው ማነው?
ሽንት ቤት ከራሱ ጋር ሲሴስን የተገኘው ማነው?
ሁለት ጊዜ ተክሊል ያገባው ማነው?
ወልዶ የካደው ማነው ወልዶ የሞተበት ማነው ?
የወለዳትን ልጁን ጴንጤ እንድትሆን ያደረገው ማነው?
የልጇን ባል ፊታ ዘማሪ ያገባችው ዘማሪ ማናት?
እጅ ከፍንጅ ከሌላ ወንድ በመያዟ ተፈታ አሁን አገልጋይ የምታሳድደው ዘማሪትስ ማናት ?

Like . Israel Jemere Bushasho

# ewunet yashenfal ስለሁሉም ነገር እግዝአብሄር ይመስገን። ይህ ሁሉ እየሆነ ያለዉ ተዋህዶ ጣባቧ መንገድ በመሆኗ ነዉ። ግን አንተ ማንነህ? ለላዉ ላይ ምትፈርድ? ለሁሉም ጌታ የዘገየ ብመስላቸዉም ጌታ ስለተሰፋ ቃሉ አይዘገይም። ሁሉም ወደ ንስሀ እንድገባ ይታገሳል እንጂ። ያነም ይፈርዳል # አንተ ከወደት ነህ? ሁሉም አላማቸዉ ያደረጉት በተክርስቲያን ለመበታተን ብሆንም ጌታ ያዉቃል። ለሁሉም እንደየስራቸው ይከፍላል!

Like ·

Eden Taye

አትፍረድ ይፈረድብሀል ይላል እነሱን እግዚሐብሔር መንገዳቸውን ያስተካክልላቸው እንፀልይላቸው

Like · Netsanet Ayalew

አቤት ጉድህ አንተ ማነህ የሰዎችን በደል የምትዘረዝር ንስሃ ዘማዊውን ድንግል ያደርጋል!አንተ የሰው በደል ስትዘረዝር እድሜህ እንዳያልቅ ሰው ስለዘመረ ስለሰበከ ፃድቅ ነው ማለት አይደለም ከዘረዘርካቸው በደሎች ያልፈፀምካቸው አሉ? ከመካከላችሁ ንፁህ የሆነ ድንጋይ አንስቶ ይውገራት! ቃሉ እንዳይፈርድብህ ተጠንቀቅ!!!

Like · Netsanet Ayalew

አቤት ጉድህ አንተ ማነህ የሰዎችን በደል የምትዘረዝር ንስሃ ዘማዊውን ድንግል ያደርጋል!አንተ የሰው በደል ስትዘረዝር እድሜህ እንዳያልቅ ሰው ስለዘመረ ስለሰበከ ፃድቅ ነው ማለት አይደለም ከዘረዘርካቸው በደሎች ያልፈፀምካቸው አሉ? ከመካከላችሁ ንፁህ የሆነ ድንጋይ አንስቶ ይውገራት! ቃሉ እንዳይፈርድብህ

ተጠንቀቅ!!!

Like ·

Kedst Misganaw

እኔ ማነኝ አትልም ስለሰው ከማውራት እዚህ ሁሉ ቦታ ምን ታረግ ነበር አንተ

Like · Timesgene Tadesse

Ene mane negne bele megemeriya ? Shama lesew yaberal lerasu gin yikeltal! Egziabeher kezhi hulu yiseweren!

Like ·

Mamushua Alex

ማንም ቢሆን በወንድሙ ሃጢያት አይፈረድበትም,ራሱ በሰራዉ ስራ እንጅ,አምላካዊ ቃሉ ግን ባታምንም በፃድቅ አንደበት ብቻ ሳይሆን በሃጣንም አንደበት ያድራል(አትጠራጠር)

Like · Report · Just now

Mamushua Alex

ማንም ቢሆን በወንድሙ ሃጢያት አይፈረድበትም,ራሱ በሰራዉ ስራ እንጅ,አምላካዊ ቃሉ ግን ባታምንም በፃድቅ አንደበት ብቻ ሳይሆን በሃጣንም አንደበት ያድራል(አትጠራጠር)

የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞች ኔትወርክ ethiopian orthodox tewahido belivers network

31/ ሰዎች ንስሐ ላለመግባት ከሚያቀርቧቸው ምክንያቶች ውስጥ ጥቂቶቹ እና መፍትሄዎቻቸው

1- እኔ የሠራሁት ኃጢአት ሰው ሁሉ የሚሠራውን ነው እንጂ የተለየ አይደለም። አንዳንድ ሰዎች እነርሱ የሠሩት ብዙ ሰዎች የሚፈጽሙትን ኃጢአት ከሆነ በግል ልንጠየቅበት አይገባም በተናጠልም ንስሐ ልንገባበት አይገባም ብለው ያስባሉ። ለእነርሱ ኃጢአት መሥራት የኅብረተሰቡ ኃጢአትን መፈጸም ምክንያት

እንደሆናቸው ይቆጥራሉ። ይሁን እንጂ ኃጢአት ኃጢአት ነውና የፈጸመው ሰው ይጠየቅበታል። ስለዚህ ከኃጢአት መለየት አንጂ ሰው ኃጢአት ሠርቷል ብለን መልሰን እዚያ ውስጥ አንዘፈቅም።

ለምሳሌ፦ በኖህ ዘመን ሰው ሁሉ በኃጢአት ውስጥ በነበረበት ጊዜ ኖህ በእግዚአብሔር ዘንድ ጻድቅ ነበር ዘፍ. 6፥5 ቅዱስ ጳውሎስም ይህን አለም አትምሰሉ ብሏል። ሮሜ. 12፥2

መላው የግብፅ ሕዝብ ጣኦት ሲያመልክ ጻድቁ ዮሴፍ የሚያመልከው እግዚአብሔርን ነበር።

በባቢሎን የተማረኩት ሠልስቱ ደቂቅና ዳንኤል እንዲሁ እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር እንጂ በጣኦት አምልኮ ከባቢሎናውያን ጋር አልተባበሩም። ዳን. 2፥8

ማንኛውም ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቱ የአለማውያንን ኑሮ ለመለወጥ ባይቻለውም እንኳ አለምንና አለማውያንን ከመምሰል ከእነርሱም ጋር ከመቀላቀል መጠንቀቅና መራቅ ይገባዋል።

2- ውጫዊ ፈተና መደራረብ ምክንያት አድርገው ያቀርባሉ።

ጠንካራና ልቦና ያለው ሰው በኃጢአት ለመውደቅ የፈተናን ብዛት ምክንያት አያደርግም። የውጭ ተጽዕኖን ለኃጢአቱ ምክንያት አድርጎ የሚያቀርብ ሰው ለትዕዛዛተ እግዚአብሔር ከበሬታ ለእግዚአብሔርም ፍቅር የሌለው ነው።

ለምሳሌ፦ ዮሴፍ ኃጢአት ለመሥራት በቂ ምክንያት ነበረው። ያም ምክንያት ባርያ ታዛዥ ባይተዋር ስለሆንኩ ኃጢአትን ሠራሁ ለማለት በቂ ምክንያት ነበረው። እርሱ ግን እንዴት አድርጌ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢያትን አደርጋለሁ አለ።

ሳኦል ያለምንም በደል ዳዊትን ባሳደደው ጊዜ እግዚአብሔር ሳኦልን በዳዊት እጅ አሳልፎ ሰጠው። ዳዊትም ሳኦልን ለመበቀል በቂ ምክንያት ነበረው ያም ምክንያት

- ኃጢአተኛ ስለሆነ
- ክፉ ስለሆነ
- እግዚአብሔርን ንቆ ከሥልጣን ስለ አወረደው
- ለዳዊት ጠላት ስለሆነ ወዘተ... 1 ሳሙ. 16፥14

ዳዊትም እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጄን አላነሳም አለ።

በአጠቃላይ ማንኛውንም ኃጢአት ለመሥራት የእግዚአብሔር ፍቅር በልቡ የታተመ ሰው ምክንያት አይደረድርም።

3- እኔ ደካማ ነኝ የእግዚአብሔር ትዕዛዛትም ከባድና አስቸጋሪ ናቸው ምን ላድርግ?

ይላሉ።

የእግዚአብሔር ዕርዳታ የረሳን እንደሆነ በእርግጥ ደካሞች ነን እግዚአብሔርን የሚያመልክ ሰው ብቻውን አይደለምና። ሰው በባህሪው ደካማ ቢሆንም በእግዚአብሔር እርዳታ የማይቻለው ነገር የለም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ <<ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ>> ፊል. 4፥13 እንዳለ:: ዳዊት እኔ ደካማ ነኝ እግዚአብሔር ግን ይረዳኛል ባይል ኖሮ ጎልያድን ባልተዋጋም ነበር። የእርሱ የባህሪ ደካማነት በእግዚአብሔር ትዕዛዝና በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ከሚሠራው ሥራ ሊያስቀረው አልቻለም ይህም ሲባል፦

1ኛ. ዳዊት በመጀመሪያ ለውጊያ ስላልተመለመለ ሊመለስ ይችል ነበር።

2ኛ. ጎልያድ ግዙፍ ተዋጊና ባለ ብዙ መሣሪያ በመሆኑ ሰው ሁሉ ስሚፈራው ዳዊትም ሊፈራው ይችል ነበር።

3ኛ. ዳዊትን ማንም እንዲዋጋ አልጠየቀውም ነበር።

4ኛ. የጦር መሪዎቹ ሁሉ ሳኦልን ጨምሮ ጎልያድን ፈርተውት ነበር ስለዚህ ዳዊት እኔ ትንሽና ደካማ ነኝ ለማለት በቂ ምክንያት ነበረው። ዳዊት ግን በእምነት ለድል በቃ።

እግዚአብሔር አምላካችን ልንፈጽመው የማንችለውን እንድንፈጽም አያዝዘንምና የእግዚአብሔር ትዕዛዛት ከባድና አስቸጋሪ እንደሆነ ማሰብ የለብንም። ፈጣሪያችን ያዝዘናል የምንፈጽምበትንም ኃይል ይሰጠናል። ከትዕዛዙም ጋር ደግሞ ፀጋው አለ። መንፈስ ቅዱስም በእኛ አድሮ ተግባሩን ለመፈጸም ያበረታናል። ያለበለዚያ ሊውጠን እንደሚያገሳ አንበሳ ሆኖ የሚመጣውን ሰይጣን መቋቋም ባልተቻለም ነበር። 1ጴጥ. 5፥8

በመጨረሻ ነፍስን በመንከባከብና በመጠበቅ የሚከተሉትን ትዕዛዛት ዘወትር ማስታወስ ይገባል።

1ኛ. በመንፈስ ብንመላለስ የሥጋን ምኞት አንፈጽምም። ገላ. 5፥16

2ኛ. መንፈስ የሞላብን መንፈስ ቅዱስ ያደረብን እንሁን። ኤፌ. 5፥18

3ኛ. በመንፈስ የምንቃጠል እንሁን ሮሜ. 12፥11

በዚህም እግዚአብሔርን በመንፈስ እናመልከዋለን ፊል. 3፥3 በመንፈስ እንጸልያለን በመንፈስም እንዘምራለን 1ቆሮ. 14፥15 የመንፈስ ፍሬዎችም እናፈራለን ገላ. 5፥22

ስለዚህ ከንስሐ በኋላ ከእግዚአብሔር ፍቅር እንዳንለይ ከእቅፉም እንዳንወጣ

የናቅናት ዓለምና የተውነው ኃጢአታችን እንዳይናፍቀን ወደ ነበርንበትም እንዳንመለስ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር የገባንለትን ቃል ኪዳን እንዳናፈርስ በእጅጉ ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል። ኃጢአትንም እንድንጠላው ተግተን መጸለይ ንሰሐ አባታችንንም በየቀኑ እያገኘን በመንፈሳዊ ሕይወት የምናድግ መሆን ይገባናል።

ሕይወታችን በእግዚአብሔር ተቃኝቶ የስሙ ቀዳሽ የክብሩ ወራሽ እንዲያደርገን የእግዚአብሔር አብ ጸጋ የእግዚአብሔር ወልድ ቸርነት የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድነት የእመቤታችን አማላጅነት የቅዱሳን ተራዳዒነት አይለየን አሜን

## 32/ መንፈሳዊ ዉጊያዎች

### የአሳብ ዉጊያ

ዉስጣዊ ዉጊያዎች ከሚባሉት መካከል የአሳብ ዉጊያ አንዱ ነው።

አሳቦች በእውን ይሁን በእንቅልፍ ሊመጡ ይችላሉ።

አሳቦች አሳብ ወለዶችና ቀን የተደረጉ ነገሮች ዉጤት ወይም ምኞትና በአሳብ ምክኒያት ሕሊና ዉስጥ የሰፈሩ ጉዳዮች ወይም በሰዉየዉ የተደመጡ ወሬዎችና ወጎች ሆነዉ በሕሊና ዉስጥ የተተከሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

እነዚህ ሁሉ በሕልም ፣ በሕሊና ብክነት ወይም ሰዉ ልቡ እስከተቀበላቸዉ ድረስ በቁም ቅዠቱ ውስጥ የሚያመላልሳቸው ሆነዉ ሊገለጡ ይችላሉ። ልብ ካልተቀበላቸዉ ግን ሊቆሙ ስለሚችሉ ሰዉየዉ

ወደማንነቱ ሊመለስ ይችላል፥
አሳቦች ወደ ሕሊና እንዲገቡ የሚፈቅደዉ ሁነኛ
ተቆጣጣሪ የሰዉ ፈቃድ ነው። አንድ አሳብ ተሸሽጎ
ቢገባም እንኳ የሰዉ ፈቃድ እንዲቆይ ወይም
እንዲወጣ ማዘዝ ይችላል።
ዲያቢሎስ ያለ ሰዉ ፈቃድ በሕሊና ዉስጥ አንድ
አሳብ ሊያስተዋውቅ
ይችላል። ይሁን እንጂ አሳብ ወደ ሕሊና እንዲገባ
ኀላፊነቱን ባትወስድም ልትቀበለዉ ኀላፊነቱን
የምትወስደው አንተ ነህ።
ከፈለግህ እንዲህ ያለዉን አሳብ ልታጠፋዉ ወይም
ላትሟገተዉ እንኳን ደህና መጣህ ብለህ ላትቀበለዉ
ትችላለህ። ይህን የኀጢያት አሳብ ከተቀበልህ ግን
በአንተ ዉስጥ ያደረዉን መንፈስ ቅዱስንና
የእግዚአብሔርን ፍቅር ትክዳለህ። በዚህ ምክንያት
የእግዚአብሔርን ትእዛዛትና የልብህን ቅድስና
መጠበቅ ያልቻልህ ሰው ሆነህ ትቆጠራለህ ማለት
ነዉ።
የኀጢያት አሳብ በሕልም ወደ አንተ ሊመጣ
ይችላል። ሙሉ ለሙሉ ንፁሕ ሰው ከሆንህ ግን
በህልምህ እንኳ ላትቀበለዉም
ትችላለህ። ይሁን እንጂ እዚህ ደረጃ ላይ
ካልደረሰህ ትቀበለዋለህ። ቢሆንም ግን ከነቃህ
በኀላ ከፍተኛ ከፍተኛ ኀዘን ይሰማሃል። ይህ ኀዘን
በዉስጣዊዉ ሕሊናህ ዉስጥ ጥልቀት ስለሚኖረዉ
ወደፊት ይህን የመሰለ ሕልም እንዳትመለከት
ይረዳሃል። ይህ በቀጥታ ባይሆንልህም
ውስጣዊሕሊናህ ንፅሕናዋን እስክታገኝ ድረስ ቀስ
በቀስ ለከናወንልህ ይችላል።
ስለዚህ ሌሊት በእንቅልፍ ዉስጥ ሳለህ የኀጢያት

አሳብን ለመቃወም ትችል ዘንድ ቀን በዉንህ ሳለህ
የኀጢያት አሳቦችን ተቃወም።
አሳቦችህ እንዳይቆጣጠሩህ በፈቃድህ እና በአንተ
ዉስጥ ባለዉ ፀጋ ልታሸንፋቸው ትችላለህ። አንተ
ካልታዘዝካቸዉ በስተቀር የኀጢያት አሳቦች
ንፅሕናህን ሊያሳጡህ አይችሉም።
ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "ሰዉ እራሱን
ከሚጎዳው የበለጠ ማንም ሊጎዳዉ አይችልም!"
በማለት የተናገረዉ ቃል ምንኛ እውነት ነው!
ስለሆነም የአሳብሕ ቸገዢ አትሁን። አሳብሕ እንዴት
እንደሚጀምር ፣ እንደሚዳብርና በሕሊና ዉስጥ
እንደሚመላለስ እያንዳንዱ ሰው ሊያውቅና ብልህ
ሊሆን ይገባዋል። አሳብ በገርነትና በዝግታ ከጀመረ
በኀላ መጨረሻዉ በኀጢአት እንደሚጠቃለል ሁሉም
ሰው ይወቅ። አሳብ የበለጠ እንዳይበረታ ዕድሉን
እንዳይሰጠዉ እያንዳንዱ ሰው የራሱ ዘብ ይሁን።
ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ሽኖዳ ሦስተኛ የግብጽ ኦርቶዶክስ
ፓትሪያሪክ
ከጻፏቸው መጽሐፍት "መንፈሳዊ ውጊያዎች" ከሚለው
በጥቂቱ የወሰድኩት።
በዚህ አገጋጣሚ ሁሉም ሰው እንዲያነባቸው እመክራለሁ
ቅዱስነታቸው የጻፏቸው መጽሐፍቶች ቢያነቧቸው አጥንትን
ያለመልማሉ መልካም ፍሬም ያፈሩበታል።
የቅዱስነታቸው በረከት ይደርብን!!!!!!

Tsion Berhanu.

## 33/ † "ያከበሩኝን አከብራለሁ" †

ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ክብር ይግባውና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድውያነ ሥጋን በተአምራት ደውያነ ነፍስም በትምህርት ሲፈውስ "ይህ ሰው ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህስ በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል፤ ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአትን ሊያስተሠርይ የሚችል ማን ነው፤ ይህ ሁሉ ጥበብና ኃይል ከወዴት አገኘው" እያሉ ይሳለቁበት ነበር። ከሚያዩትና ከሚሰሙት ሁሉ መለወጥ ሲገባቸው እየባሰባቸው ይሄዱ ነበር። ቸሩ መድኃኔ ዓለምም እነዚህ እንዲህ የሚሰድቡትንና የሚሳለቁበትን ሰዎች በዐይን ጥቅሻ ሊያጠፋቸው ሲችል ዝም ይላቸዋል፤ ይታገሣቸዋል። እንደውም ፀሐይ ያወጣላቸዋል፤ ዝናቡን ያዘንብላቸዋል፤ መግቦቱን ይሰጣቸዋል፤ ጠብቆቱን ሳያጓድልባቸው ይጠብቃቸዋል።

"ይህን ሁሉ ያደረገው ስለምንድነው?" ያልን እንደሆነ እኛን ሲያስተምረን ነው። የሚስቁብንን፣ የሚሳለቁብንን፣ የሚሰድቡንን በትሕትና ሆነን ልንጸልይላቸው፣ ልንመክራቸው፣ ልንገስጻቸው እንጂ እንደ በረሃ አውሬ ሆነን በቁጣ ነደን እንዳንናገራቸው ሲያስተምረን ነው። እነዚህ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ጌታችንን ስለ ሰደቡት፣ ስለ ተሳለቁበትና ስለ ገረፉት አንዳች ነገርን አልቀነሱበትም። ጌታችን እንዲህ ዐይነቱን አሳፋሪ ነገር ከተቀበለ እኛማ በሚስቁብንና በሚሳለቁብን በፍጹም ልንቈጣ አይገባንም። ለእነዚህ ሰዎች የሚያስፈልጋቸው ዕንባ ነው። እንዲህ ለታመመ ሰው ከትዕግሥት ውጪ ምንም ሊያድነው አይችልም። ይህቺ ትዕግሥት ከቡጢ በላይ ኃይለኛ ነች።

የተሰደበው እርሱ በብሉይም በሐዲስም እንደምን እንዳስተማረ አስተውሉ። "የእግዚአብሔርን ክርክር ስሙ! ሕዝቤ ሆይ! ምን አድርጌሃለሁ? በምንስ አድክሜሃለሁ?" /ሚክ.6፥3/፤ "ሳውል ሳውል ስለምን ታሳድደኛለህ?" የሚል ነው /ሐዋ.9፥4/። ቅ.ጳውሎስም "ምናልባት እግዚአብሔር እውነትን ያውቁ ዘንድ ንስሐን ይሰጣቸዋልና ፈቃዱን ለማድረግ በዲያብሎስ ሕያዋን ሆነው ከተያዙበት ወጥመድ ወጥተው ወደ አእምሮ ይመለሳሉ ብሎ የሚቃወሙትን በየዋህነት ይቅጣ" ብሏል /2 ጢሞ.2፥25/። ደቀ መዛሙርቱ መጥተው ከሰማይ እሳት ወርዶ እንዲያጠፋቸው በለመኑ ጊዜ ጌታችን "ምን ዓይነት መንፈስ እንደሆነላችሁ አታውቁም" ብሎ ነበር /ሉቃ.9፥55/። ዳግመኛም በዚህ በዛሬው አንቀጽ "በልባችሁ ይህን ስለምን ታስባላችሁ" አላቸው እንጂ "እናንተ ከፉዎች፣ እናንተ ርጉማን፣ እናንተ ጠንቋዮች፣ እናንተ ቅናተኞች፣ እናንተ የሰው ልጅ ጠላቶች" አላላቸውም።

እንግዲያውስ እኛም እንዲህ የታመሙትን ሰዎች ስናክም እንደ አባታችን መሆን አለብን። የሚሰማን ሰውን የሚፈራ ከሆነ ከክፋቱ ይመለሳል። ጌታችን እንክርዳዱ እንዳይነቀል ያዘዘው ስንዴውን እንዲያበላሽ ፈልጎ ሳይሆን የንስሐ ዕድሜን እንዲያገኝ ነው። ደግሞም እንዲህ በማድረጉ እጅግ ብዙ ሰዎች ተጠቅመዋል፤ ከክፋታቸው ተመልሰዋል። ቅዱስ ጳውሎስ፣ ቀራጮች፣ አመንዝሮች፣ በቀኝ በኩል የተሰቀለው ወንበዴ ከቀድሞ እንክርዳድነታቸው ተለውጠው ንጹ ስንዴ ሆነዋል። በአዝርእት ዘንድ እንክርዳድ ስንዴ መሆን ባይቻለውም በሰው ዘንድ ግን ይቻላል። የሚያስፈልገው ፈቃድ ብቻ ነውና።
ስለዚህ እውነትን የሚያጣምሙና የሚጠሉ ሰዎችን ስትመለከቱ ጠብቅዋቸው፤ ተጠንቀቁላቸዋ፤ መልካሙን መንገድ አሳይዋቸው። ሐዋርያው እንዳለው ስለ እኛ የሚናገሩትን መጥፎ ነገር ሲያጡ እንዲያፍሩና እንዲጸጸቱ በነገር ሁሉ መልካምን በማድረግ ምሳሌ የሚሆን ራሳችንን እናሳይ፤ በትምህርትም በየዋኅነትን ጭምትነትን ጤናማና የማይነቀፍ ንግግርን እንግለጥ /ቲቶ.2፥8/። ይህን ከሐኪሞች መማር እንችላለን። አንድን አስቸጋሪ በሽታ ለማከም አስቀድመው ቀለል ያለ መድኃኒትን ያዛሉ፤ ካልተሻለ ከቀድሙ ጠንከር ያለ ሌላ መድኃኒት ይጨምራሉ። አሁንም አልሻል ካለ ወደ ቀዶ ጥገና ያመራሉ። እኛም የታመሙትን ነፍሳት ለማከም እነዚህን ሐኪሞች ልንመስል ይገባል። ጌታ እንዳስተማረን ያለንን አማራጭ ሁሉ አሟጠን መጠቀም አለብን። እንዲህ ስናደርግ ታማሚዎቹም እናድናቸዋለን፤ እኛም እንጠቀማለን። እግዚአብሔርን እናስከብራለን። እግዚአብሔርን በማክበራችንም እንከብራለን። እግዚአብሔር ሲናገር “ያከበሩኝን አከብራለሁ” ብሏልና /1 ሳሙ.2፥30/። እንግዲያውስ በሚመጣው ዓለምም ይሁን በዚሁ ዓለም እግዚአብሔር ያከብረን ዘንድ እርሱን ደስ የሚያሰኘውን እናድርግ። ይህን እንድናደርግ ሰውን በመውደዱ ሰው የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይርዳን።

Hareg Taye .

34/ ብሒለ አበው!

1 <ራስህን በሐሰት አትውቀስ ራስን መክሰስ ትህትና አይደለም ታላቁ ትህትና ሰዎች ሲወቅሱህ መታገስ ነው።>> /ቅዱስ ስራፕዮን/

2 <<የማታምንበትን ነገር ለሰው ስትል አትስራው ከሰራኸው እንደምትጠፋበት እወቅ።>> /መጽሐፈ ምክር/

3 <<እንደበቱን ከቧልት ከሐሜት ያየውንም ሚስጥር ከመናገር የሚከለከል ሰው ልቦናውን ከኀልዮ ኃጥያት ያርቀዋል።>> /አረጋዊ መንፈሳዊ/

4 << ጸጋ ቢሰጥህ በተሰጠህ ጸጋ አመስግን ያልተሰጠህን እሻለሁ በማለት የተሰጠህን እንዳታጣ።>> /ማር ይስሐቅ/

5 <<ራሱን የሚንቅ የሚያቃልል ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ እውቀትን ያገኛል አዋቂ ነኝ የሚል ሰው ከፈጣሪው <ጥበብ ይለየዋል።>> /አረጋዊ መንፈሳዊ/

6 <<እግዚአብሔር ሆይ አፈርና ትቢያ ሆኜ ሳለ ጻድቅ አድርገው ከሚቆጥሩኝ ሰዎች አድነኝ።>> /አባ እንጦንስ/

7 <<ፍጡራንን መርምሮ ማወቅ ካልተቻልን ሁሉን የፈጠረ እርሱን መርምሮ ማወቅ እንደምን ይቻልናል።>> /ቅዱስ አትናቴዎስ/

8 <<ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን ሁሉ የክርስቶስንም ፀጋና ክብር ሳይፈተኑ ማግኘት አይቻልም የዚህ ዓለም ፈተናና እሳት ቶሎ ያልፋል ይጠፋል ኃጢያተኞች የሚገቡበት የገሀነም እሳት ግን ለዘላለም እንደ ነደደ ይኖራል።>> /ቅዱስ ሚናስ/

9 <<በማንም ላይ ክፋትን አትስሩ አትፍርዱ ይህንን ከጠበቃችሁ ርስቱን ትወርሳላችሁና።>> /ታላቁ አባ

መቃርስ/

10 <<ብዙ ጊዜ ብዙ እናገራለሁ በመናገሬም አዝናልሁ በዝምታዬ ግን ያዘንኩበት ጊዜ የለም።>> /ቅዱስ አርሳንዮስ/

11 <<ቤተክርስትያን መጠጊያችን ነች ቤተክርስትያን የኖኅ መርከብ ነች በውስጧ እንጠለላልን ከውጭዋ ግን ማዕበልና ቀላያት ተከፍተዋል።>> /ቅዱስ እንድርያስ/

12 <<ልባችንን ጠፊና በስባሽ ከኾነው ከምድራዊው ምኞት አርቀን ከበደል በንስሐ ነጹሕ ካደረግነው በጸጋ መንፈስቅዱስ የተሞላን እንሆናለን።>> /አባ አብርሃም መፍቀሬ ነዳያን/

13 <<ስጋዊ ፍላጎቶችን ማሸነፍ ለአክሊለ ህይወት የሚያበቃ ሰማዕትነት ነው።>> /ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ/

14 <<የቤተክርስቲያን ህይወት በመስቀል ላይ ስለሆነ ፈተና ይበዛበታል ስለዚህ ከግል ህይወታችሁ ይልቅ የቤተክርስቲያናችሁን አቋም አጠንክሩ።>> /ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ/

15 <<ከመኝታህ በፊት የምታደርገውን ፀሎት ትተህ እንድትተኛ መንፈስህ ሲገፋፋህ እሺ ብለህ አትቀበለው። እንዲያውም መዝሙረ ዳዊትን ጨምርና ሌሊቱን በሙሉ ስትፀልይ እደር።>> /ቅዱስ ይስሐቅ ሶርያዊ/

16 <<ኃጥያታችንን እኛ እያሰብን የምንፀፀት ከሆነ እግዚአብሔር ይረሳልናል ኃጥያታችንን እኛ እረስትን የምንፅናና ከሆነ እግዚአብሔር ያስብብናል።>> /ቅዱስ እንጦስ/

iacon Ankets Tekola and 73 others.

35/ የዔሊ. ቸልተኝነት

© በመልካሙ በየነ

ጥር 30/2008 ዓ.ም

ደብረማርቆስ፣ ኢትዮጵያ

ካህኑ ዔሊ. አፍኒንና ፊንሐስ የሚባሉ ሁለት ምናምንቴ ልጆች ነበሩት። ዔሊ. ክህነት ከምስፍና ጋር አስተባብሮ ለ40 ዘመን አስተዳድሮ ስለደከመ እነዚህን ልጆቹን ከበታቹ ሾማቸው። እነዚህ የዔሊ. ልጆች ግን ሦስት ዐበይት ኃጢውእ ሠሩ።

1. ሙሴና አሮን በሠሩት ሥርዓት መሠረት በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት በርቶ በቀዳማይ ሰዓተ መዓልት ይጠፋ የነበረውን ፋና ከባዶ ቤት ሲበራ ቢያድር ምን ይጠቅማል? ብለው አስቀሩ፣

2. እስራኤላውያን መሥዋዕት በሚሠዉ ጊዜ ገና ስቡ ሳይጤስ የወደዱትን ሥጋ እየነጠቁ ይበሉ ነበር፣

3. ሴቶችን በቤተመቅደስ ውስጥ ያስነውሩ ነበር።

ካህኑ ዔሊ. ልጆቹ ይህን ሁሉ ሥራ እንደሚሠሩ ሲያውቅ ልጆቼ ሆይ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ኃጢአተኛ በማድረጋችሁ ስለእናንተ የደረሰኝ ወሬ መልካም አይደለምና ይህ አይሆንም። ሰውስ ሰውን ቢበድል እግዚአብሔር ይፈርድለታል ሰው ግን እግዚአብሔርን ቢበድል ስለእርሱ የሚለምን ማን ነው? አላቸው። ነገር ግን ምክሩ ቸልተኛ ምክር ነበር። እንደዚያ ያለ የከፋ ኃጢአት እየሠሩ እያለ ከስልጣን ልሻራቸው አለማለቱ ቸልተኝነቱን ያሳያል።ካህኑ ምክሩ ከእኔ ይውጣልኝ እንጅ ቢመለሱ ባይመለሱ የሚል የቸልተኝነት አስተሳሰብ ተጠቂ ነው። ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት ዐበይት ኃጣውእ ልጆቹ ማድረጋቸውን (መሥራታቸውን) እያወቀ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለልጆቹ አድልቶ ከበታቹ እንደሾማቸው ልሻራቸው ሳይል ቀረ። እነርሱም አባታቸው በቸልተኝነት የመከራቸውን ምክር ቸል አሉት አልተቀበሉትም። የቸልተኛ ልጆች ናቸውና እንደአባታቸው እነርሱም ቸልተኞች ሆኑ። እግዚአብሔር ሊገድላቸው ወዷልና የአባታቸውን ቃል አልሰሙም እንዲል። በዚያን ጊዜ ታቦተ

ጽዮንን ያገለግል የነበረው ብላቴናው ሳሙኤል ተኝቶ ሳለ "ሳሙኤል ሳሙኤል!" ብሎ ጠራው። ሳሙኤል ግን ካህኑ ኤሊ የጠራው መስሎት ወደ ዔሊ ሄዶ "እነሆኝ የጠራኸኝ" አለ።ዔሊም ""ሂድና ተኛ እኔ አልጠራሁህም" አለው። አሁንም ለሁለተኛ ጊዜ እንዲሁ ሆነ ዔሊም "ሦስተኛ የሚጠራህ ከሆነ ተናገር ባሪያህ ይሰማል በል" አለው።ሳሙኤልም ለሦስተኛ ጊዜ እግዚአብሔር ሲጠራው ዔሊ እንዳዘዘው አደረገ። እግዚአብሔርም ለሳሙኤል "ልጆቹን አፍኒንና ፊንሐስን ከበደል አልከለከላቸውምና እንድፈርድበት የነገርኹትን በዔሊ ላይ እፈጽምበታለሁ" አለው። በተጨማሪም የእስራኤልን መሸነፍ (መመታት)፣ የታቦተ ጽዮንን መማረክ፣ የአፍኒንና ፊንሐስን የዔሊንም ሞት ነገረው። ሲነጋ ዔሊ እግዚአብሔር የነገረህን አንዲት ሳታስቀር ንገረኝ ብሎ ሳሙኤልን ጠየቀው። ሳሙኤልም አንዲት ሳያስቀር ነገረው። ዔሊ ግን እርሱ እግዚአብሔር ነውና የወደደውን ያድርግ አለ። አሁንም ይመጣብሃል የተባለውን መቅሰፍት በቸልታ ተመለከተው። ከመመለስ ይልቅ ቸልተኝነትን መረጠ። የወደደውን ያድርግ እንጅ እኔ አልመለስም ልጆቼንም አልሽራቸውም አለ።እግዚአብሔርም እንደተናገረው እስራኤላውያን በፍልስጥኤማውያን ተመቱ 4 ሽህ የሚያህሉ ሰዎችም ተገደሉባቸው። ይህ የሆነብን ታቦተ ጽዮንን ስላልያዝን ነው ብለው ታቦተ ጽዮንን እንዲልክላቸው ወደ ካህኑ ዔሊ መልእክተኛ ላኩ። የዔሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ ታቦተ ጽዮንን ይዘው መጡላቸው። እስራኤላውያን ታላቅ ደስታ አደረጉ እልልታቸውም ደመቀ። ፍልስጥኤማውያንም እስራኤላውያን የሚደሰቱት በታቦተ ጽዮን መምጣት ምክንያት መሆኑን ሲያውቁ ወዮልን ወዮታ አለብን አሉ በግብጽ የሠራችውን ተአምር ያውቃሉና። ነገር ግን ተጽናንተው አስራኤላውያንን ገጠሙ አሸነፉም። አፍኒንና ፊንሐስን ገደሉ ታቦተ ጽዮንን ማረኩ። አንድ ብንያማዊ ልብሱን ቀድዶ አመድ ነስንሶ ወደ ከተማ ተመልሶ የሆነውን ሁሉ ለዔሊ ነገረው። ዔሊም የዘጠና ዓመት ሽማግሌ ነበርና ደንገጦ ከመንበሩ ወድቆ አንገቱ ተሰብሮ ሞተ። /1ኛ ሳሙ 4÷1-18/ ለዚህ ሁሉ ከባድ ችግር ዋናው ምክንያት የዔሊ ቸልተኝነት ነበር። እግዚአብሔር በግልጥ እየነገረው ቃሉን ቸል ማለቱ ይህን መቅሰፍት አምጥቷል። እግዚአብሔር እንድትሠራው ያዘዘህን አለመሥራት አትሥራ ያለህንም መሥራት ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ተመልከት። ስለዚህም እንዲህ አይነቱን የዔሊን መሰል ቸልተኝነት ልታስወግደው ይገባል። ከዚያ ውጭ ግን በአንድም በሌላም ነገር ተመክረህ ካልሰማህ ተዝቆ የማያልቀውን መከራ እግዚአብሔር ያሸክምሃል።

Getu Temesgen - (ጌጡ ተመስገን) added 6 new photos .
36/ የኢየሩሳሌም በሮች : The Old City of Jerusalem today is surrounded by a great wall, but there are only eight gates into the city.

- (እነሆ በእግዚአብሔር ፈቃድ ቅድስት አገር ኢየሩሳሌም - ደማስቆስ በር ላይ ቆሚያለሁ። ተመስገን!)

ጥንታዊ ኢየሩሳሌም ከተማ (Old City) ዙሪያ የግንብ አጥር አራት ኪሎ ሜትር ነው። በዘመነ እሥራኤል (ከ 1967 ዓ.ም ወዲህ) የከተማው ሠፈር በአራት ተከፍሏል።

- የአይሁድ ሠፈር
- የክርስቲያን ሠፈር
- የአርመን ሠፈር
- የሙስሊም ሠፈር በመባል ይታወቃል።

- የኢየሩሳሌም በሮች - 8 - ናቸው።

- ሸአር ያፎ በር (The Jaffa Gate) - በምዕራብ የሚገኝ የከተማው ዋነኛ በር ነው። በዘመኑ ከኬብሮን (ኸሊል) የሚመጡ አረቦች የሚገቡትም፤ የሚወጡትም በሸአር ያፎ ነበር።
- አዲሱ በር (The New Gate) - በምዕራብ አቅጣጫ ይገኛል። ወደ ደብረ ገነትና ወደ አዲሱ ከተማ ያወጣል።
- የደማስቆስ በር (The Damascus Gate) - ይህ በር ወደ ሰሜን በኩል የሚያስወጣ ትልቅ በር ነው። (ለምሳሌ የሶሪያ ነጋዴዎች በደማስቆስ በር ይጠቀሙ ነበር)። የመጀመሪያው የሄሮድያን ግንባታ ነበር።
- የሄሮድስ በር (The Herod’s Gate) - ጥንት የገሊላ ሰዎች ከጥብርያዶስ የመጡ ዓሣ ነጋዴዎች መግቢያ ነበር። አረቦቹ <<ባብ እል ዛህራ>> - የአበቦች በር ብለው ይጠሩታል። የሄሮድስ በር እስከ እ.ኤ.አ 1875 ዓ.ም ድረስ በሩ ዝግ ነበር።

- የአንበሶች በር (The Lion’s Gate) - ይህ በር የምሥራቅ በር ነው። ከከተማው ወደ ጌቴ ሴማኒ መውረጃ ላይ ይገኛል። በዘመነ ብሉይ የበጎች በር ይባል ነበር። ፈረንጆች በመስቀል ዘመቻ ዘመን የእስጢፋኖስ በር (St. Stephen’s Gate) ብለውታል። አረቦች በበኩላቸው <<ባብ እስትና ማሪያም - (የእመቤታችን በር) ብለው ይጠሩታል።
- የሔኖና በር (The Dung Gate) - ይህ በር ወደ ደቡብ ሰሊሆም ያስወጣል። ጠባብ በር ነው። ይህ በር ለአይሁድ ምኩራብ (Western wall) ለሚባለው በጣም የቀረበ ስለሆነ ለመኪናና ለእግረኛ መግቢያና መውጫቸው ሆኖ ይጠቀሙበታል።
- የዳዊት በር (The Zion Gate) ይህ በር ወደ ደቡብ ያስወጣል። በጽርሐ ጽዮን በኩል ይገኛል። አረቦቹ <<የነቢዩ ዳዊት በር>> ብለው ሰይመውታል። ፈረንጆቹ <<የጽዮን በር>> ብለው ይጠሩታል። ከአይሁድ ሠፈር የሚያያዝ ስለሆነ <<የአይሁድ መንደር በር>> እየተባለ ይጠራበትም ነበር።
- ወርቃማው በር (The Golden Gate) - ይህ በር በሰባተኛው ክፍለ ዘመን የነበረ የባይዛንቲን ግንባታ ነው። ጥንት ቤተ መቅደሱ አሁን <<አል አስካ ሞስክ - (Al Aqsa Mosque) ይባላል። በሩ ገና አልተከፈተም። እ.ኤአ. በ 1530 ዓ.ም እንደተዘጋ (እንደተደፈነ) ይነገራል። የድህነት በር(<ነ>ን አላልተው ያንቡቧት) (Gate of Mercy) እያሉ ይጠሩታል።

እንደ አይሁዳዊያን እምነት መሠረት <<መሢሁ - ይህንን በር ከፍቶ ወደ ኢየሩሳሌም ይመጣል - ይገባል>> …

- ሻሎም! … (Shalom Salam)

Getu Temesgen - (ጌጡ ተመስገን) added 15 new photos .
37/ የመከራ መንገድ - (The Via Dolorosa)
Good Friday and Holy Saturday: The Easter Triduum

continues

- <<ኦ - አምልክ!>> ... (ይህ ቦታ በኢትዮጵያውያን እጅ የተያዘ ነው)።
- <<ቆሸሻለሁ - እጠበኝ!>>

ኢየሱስ ተያዘ። ሌሊቱን 6,666 ጊዜ በጅራፍ ተገረፈ። ይህንን ግርፋት እናቱ ማሪያም ብታይማ እንዴት ትሆን ነበር። የካህናቱ አለቆች ከሽማግሌዎችና ከጻፎች ጋር ተመካከሩ። ኢየሱስን አስረው ወስደው ለጲላጦስ አሳልፈው ሰጡት።

የኢየሱስ የመከራ መንገድ (14 ቱ ጸዋትወ መከራ (ከምዕራፍ 1-14) የሚጀምረው በጌቴሴማኒ ነው። <<ጌት>> መጥመቂያ ፤ <<ሴሜን>> ዘይት ነው። ከዘይት መጥመቂያ ሠፈር ...

የመከራ መንገድ በዕብራይስጥ <<ርሆቭ>>፣ በላቲን <<ቪያ ዶሎሮዛ>>፣ በዓረብ <<ጠሪቅ እልዓለም>> ይባላል። በሁሉም ቋንቋ የመከራ፤ ስቃይ፤ የጭንቀት መንገድ ነው። ርዝመቱ አንድ ኪሎ ሜትር ተኩል ይሆናል። 14 ምዕራፎች አሉት። የመከራው መንገድ ዘጠኙ ማለፊያቸው በውጭ ነው። 5 ቱ በጎልጎታ ውስጥ ናቸው።

o ምዕራፍ አንድ - 1st Station: Jesus is Condemned to Death (በአሁኑ ጲላጦስ አደባባይ) ጲላጦስ በግሪክ <<ለቶስጥራ>>፣ በዕብራይስጥ <<ገበታ/ገበጣ>> ከፍተኛ ቦታ ተቀምጦ ፈረደ። <<Ecce Homo ... እነሆ ይህ ሰው ... >> ብሎ ኢየሱስ እንዲሰቀል ለአይሁድ አሳልፎ ሰጥቷቸዋል። <<ይሰቀል! ... ይሰቀል!>> ጩኸት በረከተ። ኢየሱስም ከተፈርደበት በኋላ 28 ደረጃዎችን ወረደ። (ኪርያላይሶን! እግዚኦ መሃረነ ክርስቶስ)

o ምዕራፍ ሁለት - 2nd Station: Jesus Carries His Cross (የግርፋትና ፍርድ ቤት) ሦስት እስር ቤቶች አሉ። አንዱ ጥንት ነቢያት፣ ካህናት ታስረውበት የነበረ ነው። ዛሬ <<የጽዮን እትማማች ገዳም>> ይባላል። ሁለተኛው የሽፍታ የወንበዴ እስር ቤት ነበር። አይሁዶች <<ይፈታልን!>> ያሉት በርባንና በጌታ ግራና ቀኝ የተሰቀሉት ጥጦስና ደርክስስም የታሰሩት በዚህ ቦታ ነበር። ኢየሱስ ሁለት እግር ገብተውበት የነበውን የጉድጓድ ምልክት እና እነበርባንም ታስረውበት የነበረውን ቦታ ያሳያል።

በፍርዱ መጨረሻ ኢየሱስን መሬት ለመሬት ጎትተው የገረፉበት የመከራ መንገድ ነው። ከዚህ ሥፍራ <<አክሊለ ሦክ>> ደፍተውበታል። <<የአይሁድ ንጉሥ ሰላም ላንተ ይሁን>> እያሉ ተሳልቀውበታል። (... ኤሎሄ ... ክራለይሶ ... ኦ - አምላክ!)

o ምዕራፍ ሦስት - 3rd Station: Jesus Falls the First Time

(ኢየሱስ መስቀሉን ተሸክሞ እንደተንበረከከ ከበሩ ላይ ተስሎ ይታያል) ይህም ቦታ ከመስቀሉ ክብደት፣ ከልፋቱ፣ ከስቃዩ ጽናት የተነሳ <<የመጀመሪያ የወደቀበት ቦታ>> ነው።

o ምዕራፍ አራት - 4th Station: Jesus Meets His Holy Mother በዚህ ቦታ ማሪያም ወደ አደባባይ እንዳትሄድ አይሁድ በጠባቂ አስከልክሏት ስታለቅስ፣ ስትወድቅ፣ ስትነሳ የዋለችበት ቦታና ከልጇ ጋር የተያየችበት ቦታ ነው። የአርመን ካቶሊኮች በ 1858 ዓ.ም ቦታውን ገዝተው አሁን ያለውን ቤተ ክርስቲን አሰርተው (Our Lady of the Spasm - <<የድንግል ሥቃይ>>) ብለው ሰይመውታል። ... ማሪያም የቆመችበት የሰንደል ጫማዎች በወለሉ ላይ በሞዛይክ ተሰርቶ ይታያል።

o ምዕራፍ አምስት - 5th Station: Simon of Cyrene Helps Jesus to Carry His Cross ይህ ቦታ በፍራንሲስካኖች እጅ ነው። በስምኦን ቀሬና የተሠራ ቤተ ክርስቲያን አለ። ስምኦን ከእርሻ፤ ከበረሃ ሲመጣ አይሁዶች ያዙት። አስገድደው መስቀሉን ያሸከሙት ከዚህ ሥፍራ ነው። ኢየሱስም መስቀሉን ተሸክሞ ሲያልፍ ደክሞት የተደገፈው ድንጋይ አለ።

o ምዕራፍ ስድስት - 6th Station: Veronica Wipes the Face of Jesus ይህ ቦታ በግሪክ ካቶሊክ መለካውያን እጅ ነው። በቬሮኒካ (Veronica - <<ሰራጽታ>>) ስም ቤተ ክርስቲያን ሰርተውበታል። ይህቺም ሴት አብሮቅላ(የጲላጦስ ሚስት) እንደሆነች ይታመናል። <<በዚህች ሌሊት በህልሜ በእርሱ ምክንያት ብዙ ስቃይ ሳይ አድሬአለሁና በዚህ ንጹህ ሰው ክፉ እንዳትሰራ ተጠንቀቅ>> ብላ ለባሏ መልዕክት ልካበታለች። ለሦስተኛ ስትጠይቅ ሊሰቅሉት እንደሆነ ተረዳች። ከቤቷ ስትወጣ ከደጃፏ ደርሶ አገኘችው። ኢየሱስ በላብ ተጠምቆ ፤ በደም ተሸፍኖ ብታየው በያዘችው መሀረም ፊቱን ጠረገችው። በቸርነቱ መልኩ ተስሎ ተመልሶላታል። <ቬሮኒካ>> ተብላለች። <<ቬሮ ኢኮን>> ማለት በላቲን ቋንቋ <<የእውነት መልክ የእውነት ስዕል>> ማለት ነው።

o ምዕራፍ ሰባት - 7th Station: Jesus Falls the Second Time የፍርድ በር (Judgment Gate) ላይ ደርሰናል። በሩም የከተማ መጨረሻ ነበር። ኢየሱስ ከመንገዱ እርቀት ፤ ከመስቀሉ ክብደት ከመከራው ጽናት የተናሳ ለሁለተኛ ጊዜ የወደቀበት ነው ተብሎ ይታመናል።

o ምዕራፍ ስምንት - 8th Station: Jesus Meets the Women

of Jerusalem (የኢትዮጵያ ቦታ፤ በኢትዮጵያውያን እጅ ነው)። በኢየሩሳሌም ያሉ ህዝቦች፣ ሽማግሌዎች፣ ሴቶች ልጆች ተሰብስበው እንደሀገራቸው ልማድ እያለቀሱ፤ ዋይ ዋይ እያሉ፤ ሙሾ እያወጡ ተከትለውታል። ኢየሱስም መስቀሉን እንደተሸከመ ዘወር ብሎ እንዲህ አላቸው። ሉቃ 23-27 <<እናንተ የኢየሩሳሌም ልጆች ለኔ አታልቅሱልኝ፤ ነገር ግን መካኖችና ያልወለዱ ሙኀፀኖች፤ ያላጠቡ ጡቶች ብፁዓን ናቸው የሚሉበት ጊዜ ተራሮች እንዲወድቁባቸው ኮረብቶች እንዲሸፍኑዋቸው ይመኛሉ። ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ አልቅሱ>> ብሎ የተነገረው እዚህ ቦታ ነው።

o ምዕራፍ ዘጠኝ - 9th Station: Jesus Falls a Third Time

የኢትዮጵያ ገዳም ዴር ሱልጣን ትልቁ በር ነው። ኮፕቶች (ግብፆች) ያለ አግባብ ስለያዙብን ጉዳዩ በክርክር ላይ ነው። ኢየሱስ ከመስቀሉ ክብደት፣ ከልፋቱ፣ ከስቃዩ ጽናት የተነሳ ለሦስተኛ ጊዜ የወደቀበት ቦታ ነው። ዘጠነኛውን ምዕራፍ የሚያመለክት ትልቅ የደንጋይ ሀውልት አለ። ይኸውም የመጀመሪያ ጎልጎታ ምሥራቃዊ በር ነበር። ለረዥም ዘመናት ተዘግቶ ቆይቷል።

ይሁንና ጎልጎታ ትልቁ በር መክፈቻ ቁልፍ በአረቦቹ ዘንድ ይገኛል። ከሁለቱ ወንድማማቾች በቀር ቁልፉን ማንም አይዝም። አይሰጡም። (አልፎ አልፎ ግጭት ይከሰታል)

ምዕራፍ አሥር - 10th Station: Jesus is Stripped of His Garments በአረማይክ <<ጉልጎሌት>፣ በግሪክ <<ቀራንዮ>>፣ በላቲን <<ካልቫሪዮ>> ተብሏል። በሦስቱም ቋንቋዎች <<የራስ ቅል>> ማለት ነው። ምክንያቱም የአዳም ራስ ስለተቀበረበት ነው።

- ወይንና ሐሞት ያጠጡት በዚህ ሥፍራ ነው።

በኢትዮጵያ ገዳም ትልቁ በር ትክክል በውስጥ በኩል ሲገቡ የተዘጋ በር ይገኛል። አሥረኛው ምዕራፍ ከበሩ አጠገብ ነው። ከዚህ ሥፍራ ሲደርሱ ጭፍሮች ልብሱን (ስፍ የሌላት) ገፈው ተካፍለውታል። በቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ ተጽፏል <<እንቁረጠው እጣ እንጣጣልና ለደረሰው ይድረሰው>> ብለው እጣ ተጣጥለውበታል። ዮሐ. 19፤23

የኢየሱስ ቀሚስ ተአምራት እየሠራች ስለአስቸገረቻቸው አይሁድ ከመስቀሉ ጋር ቀብረዋት ነበር። እሌኒ ንግሥት በ 326 ዓ.ም መስቀሉን በአወጣች ጊዜ አብራ አግኝታት በወርቅና በመስታወት ሳጥን አድርጋ በጀርመን አገር በትርያል ቤተ ክርስቲያን በክብር አስቀምጣታለች <<ይባላል>>።

o ምዕራፍ አሥራ አንድ - 11th Station: Jesus is Nailed to the Cross ከአሥረኛው ምዕራፍ ጥቂት አልፎ በመስታወት የተሸፈነ የሀውልት ጉርድ ድንጋይ አለ።

ኢየሱስ በምስማር እንዴት እንደተቸነከረ የሚያሳይ ከስዕለ ስቅለቱ አጠገብ በካቶሊኮች መሰዊያ ላይ በግድግዳው ተስሎ ይታያል።

o ምዕራፍ አሥራ ሁለት - 12th Station: Jesus Dies on the Cross (Calvary) ይህ ቦታ የአዳም መቃብር ነው። ከአዳም መቃብር ላይ ትልቅ ዛፍ በቅሎ ነበር። ከመካከሉ ቆርጠው፤ እንደሙቀጫ፤ የኢየሱስን እግረ መስቀል አሹለው ከተፈለፈለው ውስጥ አግብተው በብረት ጠርቅመው ኢየሱስን ሰቅለውታል።

o ምዕራፍ አሥራ ሦስት - 13th Station: Jesus is Taken Down from the Cross በጎልጎታ ዋና በር ፊት ለፊት ከወለሉ በላይ በአራት መዕዘን የተቀረፀ ድንጋይ ይገኛል። ይህም ድንጋይ <<ጌታ ኢየሱስ የተገነዘበት ነው>>። ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ከመስቀል አውርደው <<ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው>> እያሉ የገነዙበት ቦታ ነው።

(ለእናንተ ሳይሆን ለእርሱ በተገነዘበት ሥፍራ ተንበርክኬ ጸሎቴን አድርሻለሁ። <<ቆሽሻለሁ - እጠበኝ!>> ብየዋለሁ።)

የኢየሱስ ደቀ መዝሙር የነበረውና የአርማትያሱ ዮሴፍ አይሁድን ስለፈራ የኢየሱስን ሥጋ ለመውሰድ ጲላጦስን ለመነ።

Good Friday and Holy Saturday

- - የጉዞ ማስታዋሻው - ይቀጥላል

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን !

«ወዮልኝ»

የእግዚአብሔር ሰዎች «ወዮልኝ፤» እያሉ ራሳቸውን ገሥጸው ይኖራሉ። ጌዴዎን የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦ ፊት ለፊት ስላየው ፥ ቃል በቃል ስላነጋገረው፦ «አቤቱ አምላኬ ሆይ፥ ወዮልኝ፤ የእግዚአብሔርን መልአክ ፊት ለፊት አይቻለሁና፤» ብሎ ነበር። እግዚአብሔርም፦ «ሰላም ለአንተ ይሁን፥ አትፍራ፥ አትሞትም፤» ብሎታል። (መሳ ፮፥፳፪)። ነቢዩ ኤርምያስም፦ «በሆድ ሳልሠራ አውቄሃለሁ፥ ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ፥ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ፤» በተባለ ጊዜ፦ «ወዮ ጌታ እግዚአብሔር፥ እነሆ፥ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም፤» ብሏል። (ኤር ፩፥፬)። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ፦ «ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ፤ » ብሏል። (፩ኛ ቆሮ ፱፥፲፮)።

እነዚህ «ወዮልኝ፤» ማለታቸው ለእኛ አብነት ነው። ታላላቆቹ እንዲህ ካሉ ከእኛ ከታናናሾቹ የብዙ ብዙ ይጠበቃል። ዕለት ዕለት «ወዮልኝ፤» እያልን ደረታችንን ልንደቃ፥ እንባችንን ልናፈስስ ይገባል። ሥጋችንን ደስ ከማሰኘት በስተቀር እግዚአብሔርን ደስ አሰኝተን አናውቅምና። ሰውን ደስ ለማሰኘት በሰውም ዘንድ ለመወደድ (ለውዳሴ ከንቱ) እግዚአብሔርን እናሳዝናለንና። እንኳን መንፈሳዊ መሆን መምሰሉ እንኳ አቅቶናልና። ሃያ፥ ሠላሳ ዓመት ቃለ እግዚአብሔር ዘር ተዘርቶብን፦ ሠላሳ፣ ስድሳ፣ መቶ፤ ማፍራት የተሳነን ዘረ ቆርጥሞች ነንና። መቁረባችን ማቁረባችን፣ መቀደሳችን፣ ማስቀደሳችን፣ ማሳለማችን፣መሳለማችን፣ መናዘዛችን፣ ማናዘዛችን፣ መዘመራችን፣ ማዘመራችን፣ መስበካችን፣ መሰበካችን፤ ሁሉ ከንቱ ሆኖብናልና። ስለሆነም «እገሌ ሳይገባው ነው፤» የሚለውን ትተን፦ «እኔ ሳይገባኝ ነውና ወዮልኝ፤» እንበል። የእግዚአብሔር ሰዎች፦ «ወዮላችሁ፤» እስኪባሉ አይጠብቁምና።

«ወዮላችሁ»

የዓለም ሰዎች፦ «ወዮላችሁ፤» እስኪባሉ ይጠብቃሉ፤ ተብለውም አይመለሱም፤ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቃሉን ትምህርት ሰምተው፥ የእጁን ተአምራት አይተው ያልተመለሱትን ጸሐፍት ፈሪሳውያንን በአንድ ምዕራፍ ላይ ብቻ ስምንት ጊዜ «ወዮላችሁ፤» ብሏቸዋል።

* «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፦ መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ ወዮላችሁ።»

* «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፦ በጸሎት ርዝመት እያመካኛችሁ የመበለቶችን ቤት ስለምትበሉ ወዮላችሁ።»

* «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፦ አንድ ሰው ልታሳምኑ በባሕርና በደረቅ ስለምትዞሩ፥ በሆነም ጊዜ ከእናንተይልቅ ሁለት እጥፍ የባሰ የገሃነም ልጅ ስለምታደርጉት፥ ወዮላችሁ።»

* «ማንም በቤተመቅደስ የሚምል ምንም የለበትም፤ ማንም በቤተመቅደስ ወርቅ የሚምል ግን በመሓላው ይያዛል የምትሉ፥ ዕውሮች መሪዎች ወዮላችሁ።»

* «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፦ ከአዘሙድና ከእንስላል ከከሙንም አሥራት ስለምታወጡ፥ ፍርድንና ምሕረትን፥ ታማኝነትንም፥ በሕግ ያለውን ዋና ነገር ስለምትተዉ ወዮላችሁ።»

* «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፦ በውስጡ ቅሚያና ስስት፦ ሞልቶ ሳለ የጽዋውንና የወጭቱን ውጭስለምታጠሩ ወዮላችሁ።»

* «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፦ በውጭ አምረው የሚታዩ በውስጥ ግን የሙታን አጥንት ርኵሰትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትመስሉ፥ ወዮላችሁ።»

* «እናንተ ግብዞች ጻፍችና ፈሪሳውያን፦ የነቢያትን መቃብር ስለምትሠሩ ፥ የጻድቃንንም መቃብር ስለምታስጌጡና በአባቶቻችን ዘመን ኖረን በሆነስ በነቢያት ደም በአልተባበረናቸውም ነበር ስለምትሉ፥ ወዮላችሁ።»

አይሁድ «ወዮላችሁ፤» ተብለውም አልተመለሱም፥ ጌታም እንደማይመለሱ ያውቃል። ስለሚያውቅም «እንግዲያስ የነቢያት ገዳዮች ልጆች እንደሆናችሁ በራሳችሁ ትመሰክራላችሁ። እናንተ ደግሞ የአባቶቻችሁን መስፈሪያ ሙሉ። እናንተ እባቦች፥ የእፉኝት ልጆች፥ ከገሃነም ፍርድ እንዴት ታመልጣላችሁ?» ብሏቸዋል፤ (ማቴ ፳፫፥፲፫-፴፪)። ከእነርሱም በፊት የኮራዚንና የቤተ ሳይዳ ሰዎች «ወዮላችሁ»፤ ብሏቸው ነበር፤ (ማቴ ፲፩፥፳፩)። ይኸውም ንስሐ ባለመግባታቸው ነው።

የሰዶምና የጎመራ ሰዎች እነርሱ ያገኙትን ዕድል አግኝተው ቢሆን ኖሮ፦ ማቅ ለብሰው፥ ዓመድ ላይ ተኝተው ንስሐ ይገቡ እንደነበር ነግሯቸዋል። እኛም ያገኘነውን ዕድል ያላገኙ ብዙ ሕዝቦች እንዳሉ ማስተዋል አለብን። ጌታችን፦ «ወዮ ለዓለም ማሰናከያ፤ ማሰናከያ ሳይመጣ አይቀርምና፥ ነገር ግን በእርሱ ጠንቅ ማሰናከያ ለሚመጣበት ለዚያ ሰው ወዮለት።» ያለበትም ጊዜ አለ፤ (ማቴ፲፰፥፯)። ያ ሰው

የተባለ ለጊዜው ይሁዳ ሲሆን ለፍፃሜው የሁላችንንም ሕይወት ይመለከታል። በአንድም ይሁን በሌላ የእኛም ሕይወት ለሌላው መሰናክል እንቅፋት እየሆነ ነውና። ንጹሐ ባህርይ ኢየሱስ ክርስቶስ፦ «ወዮላችሁ፤» ቢል የባህርይ አምላክ በመሆኑ ነው። ቅዱሳንም፦ «ወዮላችሁ» ቢሉ፤ ከኃጢአት ርቀው፣ ከበደል ተለይተው፣ ሃይማኖት ይዘው፤ ምግባር ሠርተው ነው። እኛ ግን እምነታችን ደካማ፣ ጸሎታችን የማይሰማ፣ ምግባራችን ጐዶሎ መሆኑን እያወቅን ሌሎችን «ወዮላቸው» እንላለን። ከምዕመናን፣ ከዲያቆናት፣ ከቀሳውስት፣ ከመዘምራን፣ ከሰባክያን፣ ከጳጳሳት፤ የማንፈርድበት የለም። አንድም ቀን በራሳችን ፈርደን፥ «ወዮልን፤» ብለን አናውቅም። ስለዚህ ኃጢአታችን እንዲሠረይልን፣ በደላችንም እንዲወገድልን፣ የዘወትር ጸሎታችን «ወዮልኝ፤» የሚል ይሁን። በሌላ በኩል ግን ሃይማኖት፣ ሥርዓት፣ ትውፊት ሲጠፋ ተመክረው፣ ተገሥፀው፣ የማይመለሱትን «ወዮላችሁ፤» ብሎ ማስጠንቀቅ፤ መፍረድም ይገባል። እንግዲህ እንደ ፈሪሳዊያን ከመሆን የእግዚአብሔር ቸርነት፥ የድንግል ማርያም አማላጅነት ይጠብቀን፤ አሜን!።

ሐና የማርያም ልጅ

39/ መንፈሳዊነት ምንድነው ?

በዲያቆን ዳንኤል ክብረት

===================

ለመሆኑ መንፈሳዊነት ምንድን ነው። ረዥምቀሚስ መልበስ ነው? ፀጉርን በአሮጌ ሻሽ መሸፈን ነው? ገላን ያለመታጠብ ነው? አንገትን መድፋት ብቻ ነው? ቀስ ብሎ መናገር ነው? ኋላ ቀርነት ነው? አይመስለኝም። ቴሌቭዥን አለማየት፣ኢሜይል አለመጠቀም ነው? ከጸሎት መጻሕፍት በቀር ሌላ ነገር አለማንበብ ነው? መንፈሳዊነትኮ በመንፈስ ቅዱስ መመራት ነው። ራስን ማሸነፍ ነው። አእምሮን እና

ልቡናን ቀና እና ሰላማዊ ማድረግ ነው። ለመሆኑ የውስጡ መንፈሳዊነት አይደለም እንዴ ወደላይ መገለጥ ያለበት። ስለ ሐዋርያት ስንናገርኮ የነፍሳቸው ቅድስና ለሥጋቸው፣ የሥጋቸው ቅድስና ለልብሳቸው፣ የልብሳቸው ቅድስና ደግሞ ለጥላቸው ተረፈ ነው የምንለው። መንፈሳዊነቱ ከውስጥ ወደ ውጭ እንጂ ከውጭ ወደ ውስጥ አልነበረም። አንዳንድ ጊዜ «መንፈሳዊነት» ከ «መንፈሳይነት» ጋር እየተመሳሰለ የምንቸገር ይመስለኛል። ዲያቆን ኤፍሬም እሸቴ ነው ይህችን ቃል ያመጣት። ከሁለት ቃላት «መንፈሳዊ» እና «መሳይ» ከሚሉ ቃላት ቆራርጦ «መንፈሳይ» የሚል ቃል ፈጠረ። ትርጉሙም «መንፈሳዊ መሳይ» ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች መንፈሳውያን ይመስላሉ እንጂ አይደሉም።

አባ ኤፍሬም ሶርያዊ ባስልዮስን ለማየት በሄደ ጊዜ ስለ ክብረ ወንጌል ሲል ከላዩ የወርቅ ልብስ ለብሶ ፣ የወርቅ ወንበር ዘርግቶ፣ የወርቅ ጫማ ተጫምቶ በጉባኤው ላይ ባየው ጊዜ «ደገኛ መምህር የተባለው ባስልዮስ ይኼ ነውን?» ብሎ ነበር። በኋላ ግን ተአምራቱን አይቶ አድንቆታል። አንዳንድ ጊዜ የውጭ ገጽታ ውስጥን ሊገልጥም ላይገልጥም ይችላልና። ልክ ነው ክርስቲያናዊ አነጋገር፣ አለባበስ፣ አረማመድ፣ ገጽታ ያስፈልጋል። ይህ ማለት መንፈሳዊነት ጅልነት፣ ከርፋፋነት፣ ኋላ ቀርነት ወይንም ደግሞ፣ ንጽሕናን አለመጠበቅ ማለት ግን አይደለም። በመንፈሳዊነታቸው የሚደነቁት የቤተ ክርስቲያን ከዋክብት እነ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ባስልዮስ ዘቂሳርያ በዘመኑ በነበረው የግሪክ ፍልስፍና እና ዕውቀት የበለጸጉ ነገር ግን ዕውቀታቸውን እናሥልጣኔያቸውን በወንጌል የቃኙ ነበሩ።

ብዙዎቻችን ከውስጥ ለሚመነጩ ትእግሥትን፣ ደግነትን፣ ታዛዥነትን፣ ትኅትናን፣ አርቆ ማሰብን፣ ኀዘኔታን፣ ፍቅርን፣ ትጋትን ለመሰሉ ነገሮች ትኩረት አንሰጥም። ከዚያ ይልቅ ተዋንያን ሊያደርጉት የሚችሉትን የውጭ ገጽታን ብቻ በማየት መመዘን እንመርጣለን። እውነተኛው መንፈሳዊነት ግን ከመንፈሳይነት መለየት አለበት። መንፈሳይ ሰዎች የራሳቸው መለያ ባሕርያት አሏቸው። እነዚህ ሰዎች ከውስጣዊ መንፈሳዊነት ይልቅ ለውጫዊ ነገሮች ትልቅ ትኩረት ይሰጣሉ። አንዳንድ ጊዜ ውስጣዊ ማንነታቸውን ለመሸፈን ሲሉ ሕግ ከሚፈቅደው በላይ ለውጫዊ ገጽታ ይጨነቃሉ። ቤተ ክርስቲያን ስለ የፀጉር አያያዝ የራስዋ ባህል አላት። እነርሱ ግን ፀጉር መታጠብን ኃጢአት ያደርጉታል። ክርስቲያኖች የሚለብሱት ልብስ ራሳቸውን የማያጋልጥ እንዲሆን ትመክራለች። እነርሱ ግን ልብስ ሁሉ መሬት ካልጠረገ ይላሉ። ያደፈ በመልበስ፣ የአእምሮ ችግር ያለባቸው ይመስል እጅግ ቀሰስ ብለው በመናገር፣ ሰው

መሆናቸውን ረስተው ምንም ነገር እንደማይበሉ እና እንደማይጠጡ በማሳመን፣ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ በመልበስ፣ ሰንሰለት በመታጠቅ፣ ትልልቅ መቁጠርያ እጃቸው ላይ በመጠቅለል። ይበልጥ መንፈሳዊ ሆነው መታየት ይፈልጋሉ።
ቀሲስ ደጀኔ ሺፈራው በዱርዬ እና በሴተኛ አዳሪዎች ዘንድ ያለውን ያህል ፈሪሃ እግዚአብሔር በአገልጋዮች ዘንድ የለም ይል ነበር።
አንዳንዶች በአገልግሎት እየበረቱ ሲሄዱ ከመንፈሳዊነት ወደ መንፈሳይነት ስለሚለወጡ።ጋሽ ግርማ ከበደ ከሚያስተምረው ነገር የማልረሳው ቃል አለ። «ሰው የሚጠላውን ኃጢአት ደጋግሞ ይሠራዋል» ይላል። ለምንድን ነው ደጋግሞ ይሠራዋል ያለው? እኔ እንደ ተረዳሁት መጀመርያውኑ ይህ ሰው ውስጡ ያላመነበትን እና ሊያደርገው የማይፈልገውን ነገር ነው ለማስመሰል ሲል እያወራ ያለው። ስለዚህም በውስጡ ያንን የጠላውን ነገር ላለማድረግ መንፈሳዊ ተጋድሎ ስለማያደርግ ደጋግሞ ሲሠራው ይገኛል። እንዲያውም አንዳንዶች መንፈሳያን ስለ አንድ
ሰው መንፈሳዊነት ደጋግመው በጥላቻ ወይንም በንቀት፣ ወይንም ደግሞ በመመጻደቅ የሚያወሩ ከሆነ ያንጊዜ አንዳች ነገር ተረዱ። ሳያስቡት እየተናገሩ ያሉት ስለ ራሳቸው ነው። መንፈሳውያን ሰዎች ስለሌሎች ውድቀት ሲያነሡ ከርኅራኄ እና ከኀዘኔታ ጋር ነው። የደስታ ስሜት አይሰማቸውም። እንደ ጀብዱም አይቆጥሩትም። ለዚህም ነው በቅዳሴ አትናቴዎስ ሊቁ ስለ አዳምና ሔዋን አንሥቶ «እኛስ እናንተን ልንወቅሳችሁ አንችልም» በማለት የተናገረው። መንፈሳውያን ይነበባሉ፤መንፈሳያን ግን ይታያሉ። መንፈሳውያን ይቀመሳሉ፣ መንፈሳያን ግን ይላሳሉ። መንፈሳውያን ያዳምጣሉ፤ መንፈሳያን ግን ይለፈልፋሉ። መንፈሳውያን ያስተውላሉ፤ መንፈሳያን ግን ይቸኩላሉ፤ መንፈሳውያን ያጠግባሉ፣
መንፈሳያን ግን ያቁለጨልጫሉ። መንፈሳውያን ይመዝናሉ፤ መንፈሳያን ግን ያፍሳሉ። መንፈሳውያን ያርማሉ፤ መንፈሳያን ግን ይተቻሉ። መንፈሳውያን ጠላቶቻቸውን አንድ ሺ ዕድል ይሰጣሉ፤ መንፈሳያን ግን ወዳጆቻቸውን ጠላቶቻቸው ለማድረግ አንድ ሺ በር ይከፍታሉ። መንፈሳውያን ይጾማሉ፣ መንፈሳያን ይራባሉ፤ መንፈሳውያን ይጸልያሉ፣ መንፈሳያን ግን ይናገራሉ/ያነባሉ። መንፈሳውያን ሱባኤ ይይዛሉ፣ መንፈሳያን ግን ስለ ሱባኤያቸው ያወራሉ። መንፈሳውያን ይሰጣሉ፣ መንፈሳያን ግን ሲሰጡ ያሳያሉ። መንፈሳውያን ቃለ እግዚአብሔርን ያስተምራሉ፣ መንፈሳያን ግን በራሳቸው ቃላት ይጠበባሉ፤ መንፈሳውያን ወደ ውስጥ፣ መንፈሳያን ወደ ውጭ ያያሉ። መንፈሳውያን የነገን፣ መንፈሳያን የዛሬን ያያሉ። መንፈሳውያን ምክንያቱን፣ መንፈሳያን ድርጊቱን

ያያሉ። መንፈሳውያን ራሳቸውን፣ መንፈሳያን ሌላውን ያያሉ። መንፈሳውያን ከመፍረዳቸው በፊት ይመክራሉ፤ መንፈሳያን ከፈረዱ በኋላ ይመክራሉ። መንፈሳውያን ዘጠኝ ጊዜ ለክተው አንድ ጊዜ ይሰፋሉ፣ መንፈሳያን ግን ዘጠኝ ጊዜ ሰፍተው አንድ ጊዜ ይለካሉ። መንፈሳውያን ከመናገራቸው በፊት ያስባሉ፣ መንፈሳያን ከተናገሩ በኋላ ያስባሉ። መንፈሳውያን ይወስናሉ፣ መንፈሳያን አስተያየት ያበዛሉ። መንፈሳውያን ሰው እንዳይሞት በችግሩ ጊዜ ይረዳሉ፣ መንፈሳያን ግን ሰው ሲሞት የልቅሶ ትርኢት ያሳያሉ። መንፈሳውያን ስለ ሌሎች በጎ መናገርን ያዘወትራሉ፣ መንፈሳያን ስለ ራሳቸው በጎ መናገርን ይፈልጋሉ። መንፈሳያን ነጭ እና ጥቁር ብቻ ያያሉ፣ መንፈሳውያን ግን ግራጫንም ጨምረው ይመለከታሉ። መንፈሳዊ ሰው አንድ ሰው ነው። መንፈሳይ ሰው ግን ሁለት ሰው ነው። ውጩ ሌላ ውስጡ ደግሞ ሌላ ነው። ገና ያልተሸነፈ፣ እንዲያውም እየገነገነ እና እየገነተረ የሚሄድ ክፉ ጠባይ አለባቸው። አይጋደሉትም። አይጸየፉትም። ሊያሸንፉት አይፈልጉም። አይቃወሙትም። በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ጥሩ ተዋናይ በአለባበስ፣ በአነጋገር፣ በአረማመድ፣ በመቅለስለስ፣ በመሽፋፈን እና ለሰው መስለው በመታየት ሊገልጡት የሚፈልጉት ሌላ ማንነት ደግሞ አላቸው። ይህ የውስጥ ማንነት አንድ ቀን ያሸንፍና እንደ ዴማስ ያስኮበልላቸዋል። ያን ጊዜ በሰው ይፈርዱ የነበሩትን ነገር ሁሉ አብዝተው ያደርጉታል። ወጣ ወጣ እና እንደ ሸንበቆ ተንከባለለ እንደ ሙቀጫ የተባለው ይደርስባቸዋል። አንዳንዴ መንፈሳይነት ሕይወት ሳይሆን በሽታ ነው ማለት ይቻላል። ያውም የአእምሮ መዛባት/ mental disorder/። በሁለት ማንነቶች መካከል እየተምታቱ መኖር። መንፈሳዊ ሰው ኃጢአት ቢሠራ እንኳን ንስሐ ይገባበታል። ያርመዋል። ይጋደልበታል። ኃጢአቱን በመሸፈን እና በማስመሰል ሳይሆን በመጋደል እና በማስወገድ ያምናል። መንፈሳይ ሰው ግን ሌሎች እንዳያዩት እንጂ እግዚአብሔር እንዳያየው አይጨነቅም። አሁን እኛ እስኪ ራሳችንን እንየው መንፈሳዊ ነን ወይስ መንፈሳይ?

Milli Milli

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን ።

40/ ዘወትር አስታውስ (ብጹዕ አቡነ ሺኖዳ፤ Always Remember)
† † ደካማነትህን አስታውስ ፣ ያን ጊዜ በጣም ጠንቃቃ ትሆናለህ፣ ሊጎዱህ በሚችሉ በትምክህትና በውዳሴ ከንቱም አትሸነፍም።
† † የተሰጠህን በፍቅር የተሞላ የእግዚአብሔርን ቸርነት አስታውስ ፣ ይህም በምስጋና የተሞላ ሕይወት እንድትመራ ያደርግሃል። በእግዚአብሔር ፍቅርና ሥራ ላይ ስትታመን ፍጹም የሆነ እምነት በልብህ እያደገ ይመጣል። ከእግዚአብሔር ጋር ያሳለፍከው ጊዜ ደግሞ በእምነት እንድትኖር ያበረታታሃል።
† † የሰዎችንፍቅርናካንተ ጋር ያሳለፉትን መልካም ጊዜ አስታውስ ። የሰዎችን ቀናነት ትጠራጠር ዘንድ ወይም ያደረጉብህን ክፉ ነገር ታስብ ዘንድ ይገባሃልን? የቀደመ ፍቅራቸው ስለ እነርሱ ይማልዳል ያንተንም ቁጣ ያበርዳል።
ሞትእንዳለ አስታውስ ፣ እንዲሁ በዓለም ያለ ፈተናም እንደሚያልፍ።"ሁሉ ከንቱ ነው፣ ነፋስንም እንደመከተል ነው።" መክብብ 1፥14 ማለትን ትረዳለህ።
† † በእግዚአብሔርፊት መቆምህንና እርሱም እንደሚመለከትህ አስታውስ ፣ ያኔ ኃጢአት አትሰራም እግዚአብሔርን ታየዋለህና።
† † የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን አስታውስ ፣ በዚህ ከጭንቀቶችህ ሁሉ ትጽጽናናለህ። ከዘነጋሃቸው ግን፣ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት እንዲህ ያለውን አስብ"ለባሪያህ ተስፋ ያስደረግኸውን ቃልህን አስብ። ቃልህ ሕያው አድርጎኛልና፥ ይህች በመከራዬ ደስ አሰኘችኝ።" መዝ. 118፥49-50
† † ስለአንተየፈሰሰውን የክርስቶስን ክቡር ደም አስታውስ ። በዚህም ሕይወትህ ያለውን ዋጋ በእርግጥ ታውቃለህ፤ በዓይኖችህ ፊት የከበረ ይሆናል፣ ስለዚህም

በከንቱ በመኖር አታጠፋውም፣ "በዋጋ ተገዝታችኋልና" 1 ኛ
ቆሮ.6:20 እንዳል ቅዱስ ጳውሎስ።
† † በወላጆችህእምነት በተጠመቅህባት ቦታ
ለእግዚአብሔር የገባኸውን ቃል አስታውስ ፤ ዲያብሎስን፣
ሥራዎቹን ሁሉ፣ ሐሳቦቹንና ጥበቡን፣ ኃይሉንም ትክድ
ዘንድ ።
† † በዚህዓለምእንግዳመሆንህንና ወደ ሰማያዊው
ቤትህ እንደምትመለስ ዘወትር አስታውስ ። ያን ጊዜ በዚህ
ዓለምና በደስታው ተስፋ ማድረግን ትተዋለህ።
† † በጠባቡ በር መጓዝ ወደ መንግስተ ሰማያት
እንደሚያደርስህ አስታውስ ። ሰፊው ደጅ ፊት ለፊትህ
ተከፍቶ ብታየው፣ አልፈኸው ሂድ ከእሱም ራቅ፣ በእርሱ
የሄዱ እንዳሉ አልቀዋልና።
† † ዘላለማዊውን ሕይወትህን አስታውስ ፣ ሁልጊዜም
ስለዚህ ትጋ።
† † የእግዚአብሔርልጅ መሆንህንና እርሱን መምሰል
እንዳለብህ አስታውስ ። እውነተኞች ከሆኑት
ከእግዚአብሔር ልጆች ጋር አካሄድህን አስተካክል።
† † የመንፈስቅዱስ ቤተ መቅደስ መሆንህን አስታውስ
። በውስጥህ ያለውንም ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ
አታሳዝን። ዘወትርም ቅዱስ የእግዚአብሔር ማደሪያ ሁን።
† † † † † † በዚህ ገጸ ንባብ ላይ የተዘረዘሩት
ሁሉ አስታውስ ። ዘንግተሃቸው ከሆነም ደግመህ
አንብባቸው።

Miku Ze Tewahedo

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን!!!

41/ የአባታችን ሆይ ጸሎት አንድምታ ትርጓሜ ፍቺ

፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲፲
አቡነ ዘበሰማያት፦
ሐዋሪያት ወደ ጌታችን ቀርበው የምንጸልየውን ጸሎት አስተምረን አሉት። ጌታችንም " እናንተስ ስትጸልዩ የሰማይ አባታችን በሉኝ " በማለት ማንም ቢሆን ሲቆምና ሲቀመጥ: ሲተኛና ሲነሣ ዘወትር ሊጸልየው የሚችለውን አጭር ጸሎት አስተማረ። ማቴዎስ 6:9-14 ይኸንንም ጸሎት " ኪዳነ ጽድቅ የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል ማብራሪያ " ከሚለው መጽሐፍ ላይ ያገኘሁትን ከታች አቅርቤዋለሁ ያንብቡት።
* አባታችን ሆይ :-
ጌታችን ከግብርናተ ዲያብሎስ / ከዲያብሎስ ባርነት / ነፃ እንዳወጣን: አጥተነው የነበረውን ልጅነት እንዳገኘን ሲያጠይቅ አቡነ / አባታችን / በሉኝ አለ። ጌታ ሎሌውን: መምህር ደቀመዝሙሩን ምን ቢወደው ያበላዋል: ያጠጣዋል: የልቡናውን ምስጢር ያጫውተዋል እንጂ ርስቱን አያወርሰውም። ርስቱን የሚያወርሰው ለልጁ ነው። እርሱ ግን ጌታችን እና አምላካችን ሲሆን የማታልፍ ርስት መንግሥተ ሰማያትን የሚያወርሰን ስለሆነ ' አቡነ ' በሉኝ አለ። አባት ለወለደው ልጁ እዲራራ የሚራራልን ስለሆነ አቡነ በሉኝ አለ።
* በሰማያት የምትኖር :-
እንዲህ ማለቱ ራሱን ከምድራዊ አባት ሲለይ ነው። ምድራዊ አባት ሲወልድ በግዙፍ ሲያሳድግ በግዙፍ ነው። ኃላም ሓላፊ ርስቱን ያወርሳል። እርሱ ግን ሲወልደን በረቂቅ: ሲያሳድገን በረቂቅ ነው። ኃላም የማታልፍ ርስቱን መንግሥተ ሰማይን ያወርሰናል። በተጨማሪም ጌታ በሁሉ ምሉዕ ሲሆን ስለ ልዕልናው በሰማይ የምትኖር ይባላል። 1ኛ ጴጥሮስ 1:8-10 ዮሐንስ ራዕይ 21:2-6።
*ስምህ ይቀደስ :-
ይኸም " ስሜ መሐሪና ይቅር ባይ ነው። " ያልኸው ይጽናልን: መላእክት ቅዱስ: ቅዱስ: ቅዱስ ብለው ስምህን አመስግነው ቅድስናህን ተሳትፈው እንዲኖሩ: እኛም ቅዱስ: ቅዱስ: ቅዱስ ብለን አመስገንህ ቅድስናህን ተሳትፈን እንድንኖር አድርገን በሉ ሲለን ነው። ኢሳያስ 6:3 ዮሐንስ ራዕይ 4:8።
*መንግሥትህ ትምጣ :-
መንግሥተ ሰማይ ትምጣልን: ልጅነትን ትሰጠን በሉ ሲል ነው። እንዲህም ማለቱ መንግሥተ ሰማይ ከወዲያ ወዲህ የምትመጣ: ከወዲህም ወዲያ የምትሄድ ሆና ሳይሆን ትገለጽልን በሉ ማለቱ ነው። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን

ፈሪሳውያን ቀርበው " የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ ትመጣለች? " ብለው በጠየቁ ጊዜ " የእግዚአብሔር መንግሥት በመጠባበቅ አትመጣም: ከዚህ አለች ከዚያ የለችም አትባልም: የእግዚአብሔር መንግሥት እንሆ በመካከላችሁ ናት " ብሏቸዋል። ሉቃስ 10:20-21።
*ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነ እንዲሁም በምድር ትሁን :-
መላእክት ከሰማይ ሲያመሰግኑህ ፈቃድህ እንደ ሆነ እኛም በምድር ያለን ደቂቀ አዳም እናመስግንህ ዘንድ ፈቃድህ ይሁን። ኋላ ሞተን ተነሥተን እናመስግንህ ዘንድ ፈቃድህ ይሁን በሉ ሲል ነው። እንዲሁም አቤቱ ፈቃደ መዓትህን ትተህ: ፈቃደ ምሕረትህን አድርግልን ብላችሁ ብትለምኑኝ አደርግላችኋለሁ ሲልም ነው።
*የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ :-
በዚህ ዓለም ሳለን ለዕለት የሚሆነንን ምግብ ስጠን በሉ ሲል ነው። በሰማይ ያሉ መላእክት ስብሐተ እግዚአብሔር ተመግበው / በሰማይ አመስግነውህ ያው ምስጋናቸው ምግብ ሆኗቸው / እንዲኖሩ እኛም በምድር እህል ምግባችንን አትንሣን ብላችሁ ብትለምኑኝ አልነሣችሁም ሲል ነው።
*በደላችንን ይቅር በለን: የበደሉንን ይቅር እንደምንል :-
ማረን: ይቅር በለን:በደላችንን ደምስስልን: መተላለፋችንን ሁሉ ይቅር በለን: ይቅርታን እናገኝ ዘንድ እኛም የበደሉንን ሁሉ ይቅር እንላለን ሲል ነው። ለዚህም ነው ጌታ " ከሰዎች ኀጢአታቸውን ይቅር ብትሉ የሰማይ አባታችሁ ደግሞ ይቅር ይላችኋል: ለሰዎች ግን ኀጢአታቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም ኀጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም " ብሏል። ማቴዎስ 6:13-15። እንዲሁም " አበሳ " የዓመት ነው: " ጌጋዬ " / በደል / የዕለት ነው። አበሳ የዓመት ያለውም ነፍስ መግደል: ቋንጃ መቁረጥ: ቤት መስበርና ይኸንን የመሳሰለው ሁሉ ነው። ይኸን ያደረገም ጠላቱን ሲርበው ቢያበላ: ሲጠማው ቢያጠጣው: ሲታረዝ ቢያለብሰው: በደለኛ ሲክሰው ዋስ ጠበቃ ቢሆነው: ንስሓ ቢገባ: ስለክፉ ሥራው ቢያዝን ቢጸጸት ቢያለቅስ ይድናል እንጂ ያለዚያስ አይድንም። ፊያታዊ ዘየማን / በቀኙ የተሰቀለው/ ሲድን: ፊያታዊ ዘጸጋም / በግራ የተሰቀለው / አለመዳኑ ንስሓ ባለመግባቱ ነው። ጌጋየ ዕለት ያለው ደግሞ ሰው ሆኖ በተለያየ ምክንያት መጣላት መጋጨት አይቀርምና: ቂም በቀል ሳይዙ ዕለቱን ስለ እግዚአብሔር ይቅር መባባል ነው። ለዚህም ነው ሐዋርያው " በቁጣችሁ ፀሐይ አይግባ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት " ያለው። ኤፌሶን 4:27
*አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን :-

ከክፉ አድነን ወደ ኀጢአት: ወደ ክህደት: ወደ መከራ: ወደ ገሃነም አታግባን: ከዚህ ሁሉ አድነን እንጂ በሉኝ ሲል ነው።
*መንግሥትህ ያንተ ናትና :-
መንግሥተ ሰማያት ያንተ ገንዘብ ናትና በሉኝ ሲል ነው።
*ኀይል ምስጋናም ለዘላለሙ :-
ከሃሊነት: ጌትነት: ለዘላለሙ ገንዘብህ ናትና አሜን በእውነት በሉኝ ሲል ነው። የእግዚአብሔር ኃይል የባሕርይ በመሆኑም ነው ጻድቁ ኢዮብ " ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆንህ አሳብህም ይከለከል ዘንድ እንደማይችል አወቅሁ " በማለት የገለጸው ኢዮብ 42:2
ማጠቃለያ: በዚህ የጸሎት ክፍል ውስጥ ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከ 81 አህዱ መጽሐፍት የተገኙ አምስት ቁም ነገሮችን አስተምሯል እነሱም :-

1. ሃይማኖት
2. ተስፋ
3. ፍቅር
4. ትሕትና
5. ጸሎት ናቸው።

ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸሎታችንን ይቀበልልን አሜን።
ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል
ወለመስቀሉ ክቡር!!!

Deyakon Kifle Maryam
42/ ምክርን ከመቀበል ይልቅ መስጠት እጅግበጣም ቀላል ነው። ሁላችንም ለጓደኛ ወይም ለቤተሰብ
አባል ምክራችንን የለገስንባቸው ሁኔታዎች ውስጥ አልፈናል፤
ነገር ግን ለዚህ ውለታችን ምክራቸውን በምላሹ ሲለግሱን
አብዛኛውን ጊዜ ደስተኞች አንሆንም። "ከሚቀበል ይልቅ

የሚሰጥ የተባረከ ነው።" የሚለውን አባባል ሰምተናል። ነገር ግን ምክርን በተመለከተ አባባሉ በተለየ መንገድ ይሠራል። አንዳንዶች የምንናገረውን የሚመጥን ማለትም በእጥፍ መስማት እንድንችል እግዚአብሔር ሁለት ጆሮዎችና አንድ አፍ ሰጥቶናል ይላሉ። ምክርን እንድንሰማና ተግሳፅን እንድንቀበል የሚገራ መንፈስና ትህትና ያስፈልጋል። እናም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚስማማ አምላካዊ ምክርን የምንሰማ እንዲሁም ተግሳፅን የምንቀበል ከሆን በጥበብ ማደግንና ጥበብን ያስገኝልናል። እግዚአብሔር በተለያዩ መንገዶች ይናገረናል። እግዚአብሔር በቃሉ፣ በሰዎች፣ በሁኔታዎች እና በእውነተኛ የሕይወት ተሞክሮዎች ይናገረናል። የእግዚአብሔርን ምክር ለመስማትና ተግሳፅን ለመቀበል ጆሮዎቻችን ከተከፈቱ፣ ውሎ አድሮ ጥበበኞች እንሆናለን።

Deacon Ephrem Seyfu

+++++ክርስትና+++++

43/ ክርስትና_ህይወት_ናት-የሚያምኑባትን ለዘለአለማዊ ህይወት ታበቃለችና።

# ክርስተና_እረፍት_ናት - የሚያምኑባት በምድርም ይሁን በሰማይ በክርስቶስ በኩል ባላቸው እምነት ያርፋሉና።

# ክርስትና_ፍቅር_ናት - ለእኔ የሚያስፈልገኝ ለወንድሜም አስፈላጊው ነው ብላ ታስተምራለችና።

# ክርስትና_እውነት_ናት - ከአንዱ ከእውነተኛው አምላክ ከእግዚአብሔር ተገኝታለችና፤ ነቀና ጥርጥረ አይገኝባትም።

# ክርስትና_ንጹህ_ናት - ከአለም እርኩሰት ተለይታ ትኖራለችና።

# ክርስትና_ልዩ_ናት - በስራዋ የሚስተካከላት በህይወቷም የሚወዳደራት የለምና ።

# ክርስትና_ብርሃን_ናት - በጨለማ ላሉ የወንጌልን ብርሃን ታበራለችና። በብርሃን ላሉት ደግሞ መብራታቸው የበለጠ እንዲበራ ዘይትን ትጨምርላቸዋለችና ።

# ክርስትና_ፍትህ_ናት - በሐብትና በመልክ በስልጣንና በጉልበት ሳይሆን ለሁሉ እንደየስራው ትከፍላለችና።

# ክርስትና_ትሁት_ናት - የእውቀትና የስልጣን ሁሉ ምንጭ አንዱ እግዚአብሔር ነው ብላ ታስተምራለችና።
# ክርስተና_ምንጭ_ናት - የተጠሙ ሁሉ ወደ እርሷ መጥተው ቃሉን ጠጥተው ይረካሉና
# ክርስተና_እሳት_ናት - ከሀዲያን ; አስመሳዮችንና ስሟን የሚያጠፉትን በመጨረሻ ለመቃጠል ትሰጣቸዋለችና
# ክርስትና_ሰላም_ናት - በእርሷ ዘንድ ጸብና ጭቅጭቅ የለምና
# ክርስተና_ፈተና_አላት -ሰይጣን በልዩ ልዩ መንገድ በእየ ቀኑ ይፈትናታልተና ::
# ክርስትና_የዛሬ_ናት - ነገ የት እንደምትሆን ምን እንደሚያገኝህ አታውቅም የመዳን ቀን ዛሬ ነው ብላ ታስተምራለችናለ።

---

---

ይህች የክርስቶስ የሆነችዋ # ቤተ_ክርስቲያንም /ክርስትና

---

---

# አንዲት_ናት - አቻና ወደር የላትም ብቻዋን ትኖራለች እንጂ
# ቅድስት_ናት - ወደ እርሷ የሚመጡትን በሙሉ በትምህርቷ ትቀድሳለችና
# የሁሉም_ናት - የተወሰነ ዘር ወይም ህዝብ አይደለችም ወደ እርሷ የሚመጡትን ሁሉ ያለምንም ወገናዊ አድልኦ ትቀበላለችና
# ዓለም_አቀፋዊት_ናት - በዚህ ቦታ ብቻ የተወሰነች ናት አይባልም የእግዚአብሔር መንፈስ ባለበት የእግዚአብሔር ሰዎች ባሉበት ቦታ ሁሉ አለች እንጂ
# ጥልቅ_ናት - በስጋዊ ህይወት በስጋዊ እውቀት አትመረመርም። በመንፈስ የሆኑ ያውቋታል ይሄዱባትል እንጂ
# የገሃነም_ደጆች_አይችሏትም - የሐሰት ትምህርት፤ ስጋዊያን ሰዎችም ሊያጠፉት አይችልም። ይልቁንም እነርሱ ከእርሷ እየራቁ ይሄዳሉ እንጂ
# በፈተና_የጸናች_ናት - የተፈተነ ሊቀ ካህናት ስላላት በፈተና ሁሉ ይረዳታልና

---

---

ቤተ ክርስቲያን ባህረ ጥበባት /2/
አትመረመርም /2/ እጂግ ጥልቅ ናት

Enat Mulatu

44/ ብሒለ አበው!

1 <ራስህን በሐሰት አትውቀስ ራስን መክሰስ ትህትና አይደለም ታላቁ ትህትና ሰዎች ሲወቅሱህ መታገስ ነው።>> /ቅዱስ ስራፕዮን/

2 <<የማታምንበትን ነገር ለሰው ስትል አትስራው ከሰራኸው እንደምትጠፋበት እወቅ።>> /መጽሐፈ ምክር/

3 <<አንደበቱን ከቧልት ከሐሜት ያየውንም ሚስጥር ከመናገር የሚከለከል ሰው ልቦናውን ከኀልዮ ኃጥያት ያርቀዋል።>> /አረጋዊ መንፈሳዊ/

4 << ጸጋ ቢሰጥህ በተሰጠህ ጸጋ አመስግን ያልተሰጠህን እሻለሁ በማለት የተሰጠህን እንዳታጣ።>> /ማር ይስሐቅ/

5 <<ራሱን የሚንቅ የሚያቃልል ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ እውቀትን ያገኛል አዋቂ ነኝ የሚል ሰው ከፈጣሪው <ጥበብ ይለየዋል።>> /አረጋዊ መንፈሳዊ/

6 <<እግዚአብሔር ሆይ አፈርና ትቢያ ሆኜ ሳለ ጻድቅ አድርገው ከሚቆጥሩኝ ሰዎች አድነኝ።>> /አባ እንጦንስ/

7 <<ፍጡራንን መርምሮ ማወቅ ካልተቻለን ሁሉን የፈጠረ እርሱን መርምሮ ማወቅ እንደምን ይቻልናል።>> /ቅዱስ አትናቴዎስ/

8 <<ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን ሁሉ የክርስቶስንም ፀጋና ክብር ሳይፈተኑ ማግኘት አይቻልም የዚህ ዓለም ፈተናና እሳት ቶሎ ያልፋል ይጠፋል ኃጢያተኞች የሚገቡበት የገሀነም እሳት ግን ለዘላለም እንደ ነደደ

ይኖራል።>> /ቅዱስ ሚናስ/

9 <<በማንም ላይ ክፊትን አትስሩ አትፍርዱ ይህንን ከጠበቃችሁ ርስቱን ትወርሳላችሁና።>> /ታላቁ አባ መቃርስ/

10 <<ብዙ ጊዜ ብዙ እናገራለሁ በመናገሬም አዝናልሁ በዝምታዬ ግን ያዘንኩበት ጊዜ የለም።>> /ቅዱስ አርሳንዮስ/

11 <<ቤተክርስትያን መጠጊያችን ነች ቤተክርስትያን የኖኅ መርክብ ነች በውስጧ እንጠለላልን ከውጭዋ ግን ማዕበልና ቀላያት ተከፍተዋል።>> /ቅዱስ እንድርያስ/

12 <<ልባችንን ጠፊና በስባሽ ከኾነው ከምድራዊው ምኞት አርቀን ከበደል በንስሐ ነጹሕ ካደረግነው በጸጋ መንፈስቅዱስ የተሞላን እንሆናለን።>> /አባ አብርሃም መፍቀሬ ነዳያን/

13 <<ስጋዊ ፍላጎቶችን ማሸነፍ ለአክሊለ ህይወት የሚያበቃ ሰማዕትነት ነው።>> /ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ/

14 <<የቤተክርስቲያን ህይወት በመስቀል ላይ ስለሆነ ፈተና ይበዛበታል ስለዚህ ከግል ህይወታችሁ ይልቅ የቤተክርስቲያናችሁን አቋም አጠንክሩ።>> /ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ/

15 <<ከመኝታህ በፊት የምታደርገውን ፀሎት ትተህ እንድትተኛ መንፈስህ ሲገፋፋህ እሺ ብለህ አትቀበለው። እንዲያውም መዝሙረ ዳዊትን ጨምርና ሌሊቱን በሙሉ ስትፀልይ እደር።>> /ቅዱስ ይስሐቅ ሶርያዊ/

16 <<ኃጥያታችንን እኛ እያሰብን የምንፀፀት ከሆነ እግዚአብሔር ይረሳልናል ኃጥያታችንን እኛ እረስትን የምንፅናና ከሆነ እግዚአብሔር ያስብብናል።>> /ቅዱስ

እንጦስ/